በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲክስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮምኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአተራረክ ቴክኒክ በ "ዐዌ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" እና በ"ዐዌ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ውስጥ

በይታገሱ ጌትነት

2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# የአተራረክ ቴክኒክ በ "ዐዔ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" እና በ"ዐዔ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ውስጥ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲክስ፣ የቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ፎክሎር
ትምህርት ክፍል

የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ዮናስ አድማሱ (ዶ/ር)

በይታገሱ ጌትነት

2005 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲክስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና
የኮምኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃመርሐ ግብር

# የአተራረክ ቴክኒክ በ "ዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" እና በ"ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ውስጥ

በይታገሱ ጌትነት

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ______________ ፊርማ ______________

የፈታኝ ስም ፊርማ

የውስጥ ______________ ______________

የውጭ ______________ ______________

ILS LIBRARY

## አበርክቶ

ይህ የመመረቂያ ወረቀቴን በትምህርት ቤት ቆይታዬ ውስጥ ለሥነ-ጽሑፍ የተለየ ፍቅር እንዲኖረኝ ረድተውኛል ብዬ ለማስባቸው ሁለት መምህራኖቼ መታሰቢያ እንዲሆን አበርክቻለሁ። በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቆይታዬ መንገዴን ለቀየሰልኝ መምህሬ ደራሲና ጋዜጠኛ አብርሐም ረታ አለሙ እና ይሔን ጥናት እያማከሩኝ ለነበሩት የሥነ-ጽሑፍ ምሁር ዶ/ር ዮናስ አድማሱ።

## ምስጋና

ከሁሉም በላይ ሁሉን ለሚያከናውን አምላክ ምስጋናዬ ታላቅ ነው፡፡ በመቀጠል ይህን የጥናት ወረቀት በማማከርና አቅጣጫ በማመላከት ፊር ላስያዙልኝ ለአማካሪዬ ዶ/ር ዮናስ አድማሱ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡ ምንም እንኳ ወረቀቱ ሲጠናቀቅ በአጸደ ሥጋ ባይኖሩም ከህመም ጋር እየታገሉም ቢሆን እስከመጨረሻው ኃላፊነታቸውን መወጣት እንደቻሉ መመስከር ግዴታዬ ይመስለኛል፡፡ በመጨረሻም የዶ/ር ዮናስን አደራ ወስዶ ይህ ጥናት ከዳር እንዲደርስ ትልቅ እገዛ ያደረገልኝን መምህሬን አቶ ቴዎድሮስ ገብሬን "አመሰግናለሁ" ለማለት ቃሉ አንሶብኛል፡፡

ከዚህ ባሻገር ይህን ትምህርት እንድማር ያመቻቹልኝን የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ሳላመሰግን ማለፍ "በልቶ ካጅ" ያሰኛልና፤ አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ ጋርም እንደ ማኅበር ኃላፊም እንደ ቅርብ ወዳጅና አባትም ጋሽ ደረጀ ገብሬ ላደረክልኝ ድጋፍ ሰው አያሳጣህ ብያለሁ፡፡ ጊዜያችሁን ስነጥቃችሁ ትምህርት እና ቤተሰብ በአንድ ላይ ሸክም እንዳይሆኑብኝ ለዓላማዬ ለተዋችሁኝ ምስራቅ ማርቆስ፣ አሜን ይታገሱና ሮሃ ይታገሱ ፍቅር የሞላበትን ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ፡፡ ወዳጅ-ብዙ ብሆንም ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ ጓደኝነት ምን እንደሆነ ላስተማራችሁኝ ኡመር ሸኩራላ፣ እስማኤል ከሊፋ፣ መአዛ ታከለና ሚካኤል ሚሊዮን ብድሩን አምላክ በእጥፍ ይክፈልልኝ፡፡

የዛሬን ሲያስታውሱ የትናንት እንዳይዘነጋ እኔ አሁን የሆንኩትን እንድሆን እናቴ መነን እሸቴ፣ የቀድሞው ህጻናት አምባ መምህራንና ማህበረሰብ እንዲሁም ጓደኞቼ ቦታችሁ ትልቅ ነውና በዚህ አጋጣሚ ማመስገኔ ቢያንስ እንጂ አይበዛም፡፡

## አጠቃሎ

ለዚህ "የአተራረክ ቴክኒክ በ"ዐዌ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" እና በ"ዐዌ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ውስጥ" የሚል ርዕስ ላለው ጥናት መነሻ የሆነኝ አንዱ ምክንያት በቀደምት ኢትዮጵያዊ ሥነ-ጽሑፎች ላይ ያተኮሩ ጥናታዊ ሥራዎች ውስን ሆነው ማግኘቴ ነው። በተለይ ከአክሱም ስልጣኔ በኋላ ታላቅ የጥበባት እና የሥነ-ጽሑፍ መነቃቃት በተፈጠረበት በመካከለኛው ዘመን ውጤቶች መካከል በብዙ የሥነ- ጽሑፍ አጥኚዎች ትኩረት ያላገኙትን ዜና መዋዕሎችን ለማጥናት መርጫለሁ። በዚህም መሰረት "የዐዌ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" እና "የዐዌ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል"ን የምመረምር ሲሆን የምርምሬም ዋና ነጥብ የዜና መዋዕላቱን የአተራረክ ብልሀት መፈተሽ ነው።

ይሄን ምርምር ከግብ ለማድረስ እንድችል የዜና መዋዕላቱን ተራኪ ማዕከል በማድረግ ቴክስቱን በአተኩሮ /focalization/ እና በበይነ-ቴክስታዊነት /intertextuality/ እይታዎች እፈትሻለሁ። በምርምር ወቅትም ቴክስታዊ ትንተናን ተጠቅሜያለሁ። በዚህም መሰረት በአተኩሮ ክፍል የተራኪውን የመተረኪያ አካያ ለመመርመሪያ መሳሪያነት በመጠቀም የተራኪውን አንጻር፣ ርዕዮተ ዓለሙን እና አላማውን ተመልክቻለሁ። በዚህም መሰረት ለመመርመር የመረጥኳቸው ዜና መዋዕላት የተራኪዎቻቸው አንጻር/መደብ የተለያዩ መሆናቸውን እንዲሁም ድብልቅ የተራኪ አንጻርን በተወሰነ ደረጃ የሚጠቀሙ መሆኑን ለማመላከት ሞክሬያለሁ። የተራኪዎቹ ርዕዮተ አለም ምንጭ በአብዛኛው የክርስትናው አስተምህሮ መሆኑን፣ አላማቸው የባለታሪኩን ምድራዊ ልዕልና ማላቅና ሰማያዊ ብጽዕናን መጎናጸፍ እንዲሁም አቃቤ ሥርዐትነት መተረክ መሆኑን አሳይቻለሁ።

በሌላም በኩል በይነ-ቴክስታዊነትን ስመረምር አብዛኞች ቀደምት አጥኚዎች ዜና መዋዕላቱ ገድላዊ ናቸው ከማለት ያለፈ የትኞቹ ነጥቦች ወደዚህ መዳረሻ ሊያቃርቧቸው እንደሚችሉ ሲያብራሩ አላጋጠሙኝም። በመሆኑም የእነሱኑ ዳና በመከተል ሆኖም የዜና መዋዕላቱን ቴክስት በመመርመር ከገድላት ጋር የሚገናኙባቸውን ነጥቦች ተመልክቻለሁ። በርግጥ አንድ ቴክስት ሲፈጠርም ሆነ ከተፈጠረ በኋላ ለብቻው የሚቆም ባለመሆኑ፤ ቴክስቶቹ ሲፈጠሩ በተገናኙበት፣ በተዋዋሱት አሊያም በፍካሬ አንባቢው በሚረዳበት ገጽ መመርመር ይቻላል። የኔ ምርምርም የአተራረክ ቴክኒክን የሚያተኩር በመሆኑ ቴክስቱ ሲፈጠር በሚኖረው በይነ-ቴክስታዊነት ላይ አተኩሬያለሁ። በዚህ መሰረት ዜና መዋዕላቱ ከመጽፍ ቅዱስ ጋር በመጥቀስ እና በማስታከክ በይነ-ቴክስታዊነትን የፈጠሩ ሲሆን ከገድላት ጋር ደግሞ በታሪክ መፋሰሻ ሥርዐት እና በመባያ ጉዳዮች በይነ-ቴክስታዊነትን ይፈጥራሉ። በሌላ በኩልም ገድላቱ እና ዜና መዋዕላቱ በአቻነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ቴክስትን ስበው በማካተት የጋራ ጸባይን ይጋራሉ ወደሚል መደምደሚያ መድረስ ችያለሁ።

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ አላማ ........ 2
1.2 የአጠናኑ ዘዴ ........ 2
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.4 የምርምር ጥያቄዎች ........ 3
1.5 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 3
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.7 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ........ 4
1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 4

ምዕራፍ ሁለት ........ 6

2.1 ክለሳ ድርሳን ........ 6
2.2. ንድፈ-ሐሳባዊ ዳራ ........ 14
2.2.1 ተረክ ምንድን ነው? ........ 14
2.2.2 ስነ ተረክ ምንድን ነው? ........ 19
2.2.2.1 አተኩሮ ........ 24
2.3.2.2 በይነ-ቴክስታዊነት ........ 27

ምዕራፍ ሦስት ........ 33

ዜና መዋዕል ........ 33

ትንተና ........ 35

3.ሀ. "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ........ 35
3.1 አተኩሮ በዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ........ 35
3.1.1 አንጻር (ተራኪው፣ መደብ እና የዕይታ አቅጣጫ) ........ 35
3.1.2 ርዕዮተ ዓለም ........ 41
3.1.3 አላማ ........ 45
3.1.3.1 ምድራዊ ልዕልና መስጠት ........ 45
3.1.3.2 ሰማያዊ ብጽዕና ማጎናጸፍ ........ 55
3.2 "የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" በይነ-ቴክስታዊነት ........ 60
3.2.1 "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" በይነ-ቴክስታዊነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ........ 61
3.2.1.1 መጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሽ በይነ-ቴክስታዊነት ........ 61
3.2.1.2 መጽሐፍ ቅዱስን የማስታከክ በይነ-ቴክስታዊነት ........ 63
3.2.2 በይነ-ቴክስታዊነት ከገድላት ጋር ........ 64

3.2.1.2 መጽሐፍ ቅዱስን የማስታከክ በይነ-ቴክስታዊነት ....63
3.2.2 በይነ-ቴክስታዊነት ከገድላት ጋር ....64
3.2.2.1 የታሪክ ተፋሰስ ....65
3.2.2.1.1 አጀማመር በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ....66
3.2.2.1.2 የተረኩ ዋና አካል (ታሪክ) በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ....67
3.2.2.1.3 አፈጻጸም በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ....70
3.2.2.2 የታሪክ ተፋሰስ በይነ-ቴክስታዊነት ....71
3.2.2.3 ተአምራዊነት ....73
3.2.2.4 ጸሎት/ ምልጃ ....75
3.ለ. "የዐዔ ዘርአ ያቆብ ዜና መዋዕል" ....77
3.2 አተኩሮ "በዐዔ ዘርአ ያቆብ ዜና መዋዕል" ውስጥ ....77
3.2.1 አንጻር (ተራኪው፣ መደብ እና የዕይታ አቅጣጫ) ....77
3.2.2 ርዕዮተ ዓለም ....78
3.2.3 አላማ ....80
3.2.3.1 አቃቤ ሥርዐት ....80
3.2.3.2 ቀናዒ ሃይማኖት ....83
3.3 በይነ-ቴክስታዊነት በዐዔ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ውስጥ ....85
3.3.1 ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ....85
3.3.1.1 መጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሽ በይነ-ቴክስታዊነት ....86
3.3.1.2 መጽሐፍ ቅዱስን የማስታከክ በይነ-ቴክስታዊነት ....87
3.3.2 "የዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" በይነ-ቴክስታዊነት ከገድላት ጋር ....88
3.3.2.1 የታሪክ ተፋሰስ ....88
3.3.2.1.1 አጀማመር ....88
3.3.2.1.2 የተረኩ ዋና አካል (ታሪክ) በ "ዐዔ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ....90
3.3.2.1.3 አፈጻጸም በዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ....91
3.2.2.5 የታሪክ ተፋሰስ (story line) በይነ-ቴክስታዊነት ....92
3.3.2.2 ተአምራዊነት ....93
3.3.2.3 ፀሎት/ ምልጃ ....94
ምዕራፍ አራት ....95
ማጠቃለያ ....95
ዋቢ. መጻሕፍት ....98

## ምዕራፍ አንድ

### መግቢያ

በሥነ-ጽሑፍ የአንድ ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍናው፣ ታሪኩ እና የአኗኗር ሥርዐቱ ይገለጻል። በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ጽሑፋዊ ሀብት ያለው ማኅበረሰብ ይሁንኝ ብሎም ወይም ይሁንኝ ሳይል ስላለበት ዘመን ሁኔታዎች ጥቆማ የሚሰጡ ነጥቦችን መዝግቦና ከትቦ ያልፋል። ከዚህም የተጻፈ ሰነድ ላይ በመነሳት የተለያዩ የምርምር ዘርፎች ሊመረምሩ ከሚሹት ነጥብ አኳያ ይመለከቱታል። ከነዚህ የጥናት መስኮች መሐል የሥነ-ጽሑፍ ምርምር ዘርፍ አንዱ ነው። ይህም በመሆኑ የሥነ-ጽሑፍ ምርምር ጥንታዊ ጽሑፎችን የሥነ-ጽሑፉን ታሪክ ለማጥናት፣ ቴክኒካዊ ብቃቱን ለመለየት አሊያም ደግሞ ያለውን ወይም መጪውን የሥነ-ጽሑፍ ሀብት ለመመርመር በማነጻሪያነት ሊጠቀምባቸው ይችላል።

ከላይ ካየነው ነጥብ አንጻር የኢትዮጵያን የሥነ-ጽሑፍ ታሪክን ለማጥናት ስንነሳ በቅጡ ተጠንቶ የምናገኘው ጥቂቱን ነው። ለዚህም በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። ከዚህም መካከል ቀደምት የሀገሪቱ ጽሑፋዊ ሐብት ላይ አትኩሮት ሰጥተው ጥናት እና ምርምር ለማድረግ ዝንባሌ ያሳዩ የመስኩ ባለሙያዎች ማነስ አንዱ ተጠቃሽ ምክንያት ይሆናል። ስለሆነም ጥንታዊ ጽሑፋዊ ሀብታችንን ከሥነ-ጽሑፍ ጥናት መስክ አኳያ ሊያጠኑ የሚችሉ ተመራማሪዎችን ማፍራት ተገቢነት ይኖረዋል። በተለይም በኢትዮጵያ የሥነ-ጽሑፍና የኪነ-ጥበብ ታሪክ ውስጥ ሰፊ አሻራውን ትቶ ባለፈው የመካከለኛው ዘመን ላይ ትኩረት ያደረጉ ሰፊ ጥናቶች ቢከወኑ የሀገሪቱ የሥነ-ጽሑፍ ታሪክ አሁን ከሚባልለት በላይ ማለት የሚያስችል እድል አለ[1] (ባርትኒስኪ, 2003፡56)።

ይልማ ዴሬሳ የኢትዮጲያ መካከለኛው ዘመን ኪነ-ጥበባዊ ሁኔታ እጅግ በጣም ጥሩ ሊባል የሚችል እንደነበረ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ</u> በሚለው መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ በማለት ይጠቅሳሉ።

> ከ1264 እስከ 1500 ዓ.ም በኢትዮጵያ የነበረው እንቅስቃሴ የሚያስደንቅ ነበረ። ከዮዲት ብዝበዛ በኋላ ድርሰት ለመጀመሪያ ጊዜ በብዛት መጻፍ ጀመሩ። [...] በዚህ ዘመነ ታሪክ ውስጥ ኢትዮጵያ በስልጣኔ ርምጃ ያደረገችው በአክሱሞች ዘመንና ታሪክ ከተደረገ የሚያንስ ነው ማለት አይቻልም። (1964፡ 5)

[1] አንድርዜይ ባርትኒስኪ እና ዮዓና ማንቴል-ኒየችኮ ከአክሱም ዘመነ መንግስት ቀጥሎ የሥነጽሑፍ ማበብ የታየበት ሁለተኛው የኢትዮጵያ የሥነ-ጽሑፍ ምዕራፍ ይሔው የመካከለኛው ዘመን እንደነበረ ይመሰክራሉ /56/፡፡

በዚህም መነሻነት የዚህ ጥናት አዘጋጅ ብዙ ሲሠራባቸው ይችላል ብሎ ካመነባቸው የዚህ ዘመን የሥነ-ጽሑፍ ሀብቶች ውስጥ ሁለቱን ማለትም "የዐዔ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል"ን እና "የዐዔ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል"ን በመምረጥ የአተራረክ ቴክኒካቸውን ለይቶ ጥናቱን አከናውኗል።

## 1.1 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ አላማው ጥንታዊ የሥነ-ጽሑፍ ውጤት የሆኑ ዜና መዋዕሎች እንደምን ባለ ሁኔታና ቴክኒክ አንድን ታሪክ መተረክ እንደሚችሉ መመርመር ነው። ይህንንም ከግብ ለማድረስ ከዜና መዋዕላቱ ውስጥ ሁለቱን በመምረጥ ከአተራረክ ቴክኒኮች መካከል ውስን ነጥቦችን በመያዝ ጥናቱን ያከናውናል። ይህ አጠቃላይ የጥናቱ አላማ ሲሆን ንዑስ አላማዎቹም ከዚህ በታች የተጠቀሱት ናቸው።

1.1.1 የዜና መዋዕላቱ አተራረክ ከሌሎች ዘመነኛ ጽሑፋዊ ሥራዎች በተለይም ከገድላት አተራረክ ጋር ያለውን ግንኙነት በተወሰነ ደረጃ መመርመር፤

1.1.2 ዜና መዋዕላቱ ከአተኩሮ /focalization/ እና ከበይነ-ቴክስታዊነት /intertextuality/ አንጻር የአተራረክ ቴክኒኮችን በእንደምን ያለ ሁኔታ እንደሚጠቀሙ መመርመር።

## 1.2 የአጠናኑ ዘዴ

በዚህ ጥናቱ ውስጥ ለማጥናት የመረጥኩት ዋንኛ ጉዳይ ዜና መዋዕላቱ እንደምን ባለ ሁኔታና ቴክኒክ አንድን ታሪክ መተረክ እንደሚችሉ መመርመር ነው። በመሆኑም የቤተ መጽሐፍትን ንባብ መሰረት ያደረገ ጥናት ነው። ለዚህም አላማዬ መሳካት እንዲረዳኝ አተኩሮ እና በይነ-ቴክስታዊ የሚሉትን ሀሳቦችን በማጠንጠኛነት ተጠቅሜያለሁ። ሁለቱም የመመልከቻ ነጥቦቼ መነሻቸውም ሆነ መድረሻቸው ቴክስቱ ነው። በዚህ ውስጥ ለምርምሬ አጋዥነት የመረጥኩትን አተኩሮ በምተነትንበት ወቅት የተራኪውን አኳያን በጥልቀት እመለከታለሁ። በዚህ ውስጥም የተራኪውን አኳያዎች ማለትም የዕይታ አቅጣጫን (አንጻር)፣ ርዕዮተ-ዓለሙን እና አላማውን ለያይቼ እመለከታለሁ። በይነ-ቴክስታዊነትን በምተነትንበት ወቅት ደግሞ ዜና መዋዕሎቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ የወሰዱትን ጉዳዮች እንዲሁም ከገድላት ጋር ያላቸውን በይነ-ቴክስታዊነት በመተንተን ለማስረዳት እሞክራለሁ።

በዚህ ጥናት ላይ ያሉትን መረጃዎች በምተነትንበት ጊዜ አስቀድሜ በንድፈ ሐሳብ ክፍል ላይ የማተኩርባቸውን የአተራረክ ቴክኒኮችን (አተኩሮ እና በይነ-ቴክስታዊነት)ን በመያዝ ዜና መዋዕላቱ ከእነዚህ የመተረኪያ ቴክኒኮች አኳያ ያላቸውን መልክ አስረጂ

ምሳሌ በማንሳት ይሆናል፡፡ በትንታኔዬ ወቅት አንዳንዱን ሐሳብ በቀጥታ በመግለጽ ወይም በማሳየት ብቻ ማስረዳት የምችል ሲመስለኝ ይሔንኑ መንገድ የምከተል ሲሆን በሌላ ሁኔታ መተርጎምና ማነጻጸር ሲያስገድደኝ ተገቢውን መንገድ እከተላለሁ፡፡ በየትኛውም መንገድ ትንታኔዬን ሳደርግ ተጨባጭ እና በቂ ማስረጃዎችን ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ነባር ሥነ-ጽሑፍ በተለይም ከዜና መዋዕላቱ አኳያ በሚደረጉ ትንተናዎች እና ምርምሮች ላይ ካሉ ክፍተቶች መካከል ለጥቂቶቹ መልስ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሰረት የዜና መዋዕላቱ ተራኪዎች እንደምን ባለ ቴክኒክ ታሪኩን ሊነግሩን እንደሚጥሩ እንዲሁም የአተራረክ ተለምዷቸውን በከፊል ያሳያል፡፡ ከዚህም ባሻገር የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ላይ ምርምራቸውን ለሚያደርጉ አጥኚዎች የተወሰነ መረጃዎችን ማቀበል ይችላል፡፡ በሌላም በኩል ለሌሎች አጥኚዎች መነሳሳት የበኩሉን አስተዋጽዖ ያበረክታል ብዬ አምናለሁ፡፡

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት በመሠረታዊ ደረጃ የተነሳበትን አላማ ማሳካት ይችላሉ ተብለው በአጥኚው የታመነባቸውና የሚያነሳቸው ሶስት የምርምር ጥያቄዎች አሉት፡፡ እነዚህም

- የሚመረመሩት ዜና መዋዕሎች የአተራረክ ቴክኒክ እንዴት ነው?
- ዜና መዋዕላቱ ከነርሱ አስቀድሞ ከነበሩትና ከዘመነኛ ጽሑፎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው?
- በዜና መዋዕላቱ ውስጥ የጋራ የሚባል የአተራረክ ቴክኒክ ይታይ ይሆን? የሚሉትን ነጥቦች ነው፡፡

## 1.5 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት ከአደረጃጀት አንጻር አስቀድሞ በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ላይ ትኩረት ያደረጉ ቀደምት አጥኚዎችን በመውሰድ የክለሳ ድርሳን ክፍሉን የሚያስቀድም ሲሆን በዚህም ክፍል ላይ አትኩሮት የተሰጣቸው ሥነ-ጽሑፋዊ ለሆኑ ጥናቶች ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም በማነሳቸው ዜና መዋዕላት ላይ ከታሪክ ምርምር አንጻር በርካቶች በጥናታቸው ያካተቷቸው ቢሆንም የእኔ ጥናት ትኩረት የአተራረክ ቴክኒክ ብቻ በመሆኑ ከምርምሬ ትኩረት ይርቃሉ በሚል እምነት ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል የንድፈ ሐሳብ ዳሰሳ የማደርግ ሲሆን ከአተራረክ ቴክኒክ አንጻር ያሉ መሰረታዊ ብያኔዎችንና ለምርምሩ ይጠቅማሉ ብዬ ያመንኩባቸውን ነጥቦች በማትኮር በዘርፉ ያሉ ተመራማሪዎችን ንድፈ-ሐሳብ እያነሳሁ ለማስረዳት እሞክራለሁ፡፡

በመቀጠል የኢትዮጵያን ዜና መዋዕል ምንነትና በምን መልኩ ይጻፉ እንደነበር ካስተዋወቅሁ በኂላ፤ በትንታኔ ክፍሌ ላይ ሁለቱንም ዜና መዋዕሎች ለየብቻቸው ሊመረመሩ ይገባቸዋል ብዬ በመረጥኳቸው መመርመሪያ ነጥቦች እየላካሁ አብራራለሁ፣ እተነትናለሁ። እዚህ ላይ ሰፊ ድርሻ በመውሰድ አስረጂ ምሳሌዎችን እየጠቀስኩ ማብራሪያዬን የምሰጥ ሲሆን ከዜና መዋዕሎቹ እና ከሚነሱት መመርመሪያ ሐሳቦች አንጻር አስረጂዎች በዝተው ሳገኝ ናሙናውን በማሳየት ሌሎቹን ያሉበትን ገጽ በማመላከት አልፋቸዋለሁ። በመቀጠልም ትንተናዬን በማጠናቀቅ ማጠቃለያዬን አስቀምጣለሁ።

### 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት "የዐፄ ዐምደ ጽዮን" እና "የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን" ዜና መዋዕሎች የአተራረክ ቴክኒክ የሚመረምር ሲሆን የአተራረክ ቴክኒኮችን ማጥኛ መንገዶች ከሆኑት ነጥቦች መካከል ሁለቱን ማለትም አተኩሮ /focalization/ና እና በይነ-ቴክስታዊነትን /intertextuality/ ብቻ ነጥሎ ለመመልከት ይሞክራል። በመሆኑም አጠቃላይ ጥናቱ በተጠቀሱት ዜና መዋዕሎች ላይ ብቻ በማተኮር ከመመርመር ውጪ የታሪክ /history/ እና የእውነታን /reality/ ተጠየቆችን አይመለከትም።

### 1.7 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይሄን ጥናት ለማካሄድ አነሳሽ ከሆኑ ምክንያቶች መካከል አንዱ በቀደምት የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፋዊ ታሪኮች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ውስን ሆነው ማግኘቴ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ለታሪካዊና ሃይማኖታዊ ለሆኑ ጽሑፋዊ ሥራዎች ያለኝ ቅርበት ሌላው ነጥብ ነው። በሌላ መልኩም የአንድ ሀገር የሥነ-ጽሑፍ እድገትና ባህሪ እንደ ጎርፍ ደራሽ ድንገት የሚከሰት ሳይሆን በነባሮቹ የሥነ-ጽሑፍ እርሾዎች የሚጠነሰስ ነው። አሁን ያለውን ስናጠና የተነሳንበትንም መመርመር ግድ በመሆኑ ያቅሜን ያክል ክፍተቱን የሚሞላ አንዳች ነገር ማበርከትን በመመኘት ነው ይሔን ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት የተነሳሁት።

### 1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ይሔን ጥናት ለማከናወን በተነሳሁበት ወቅት ያጋጠሙኝ ችግሮች በርካታ ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ የምፈልጋቸውን ዜና መዋዕላት በቀላሉ ማግኘት አለመቻሌ እጅግ አሳሳቢ ከመሆን ባለፈ ጥረቱም ትዕግስት አስጨራሽ ነበር። ይሔም ማለት የምፈልጋቸውን ዜና መዋዕላት በምፈልገው ጊዜ ለማግኘት ያለመቻል አንዱ ችግር ሲሆን፤ ዜና መዋዕላቱ ያልታተሙ ማለትም በእጅ ጽሑፍ /በማንስክሪፕት ደረጃ/ ያሉ በመሆኑ በጥብቅ ስፍራዎች ላይ ብቻ ከበርካታ ክልከላዎች ጋር የሚገኙ መሆናቸው አስቸጋሪነቱን

አግዝፎታል፡፡ ዜና መዋዕላቱ የሚገኙት በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተመጻህፍት እና በብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት የጥንታዊ ሰነዶች አርካይቭ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ ሁለቱም አብያተ መጽሐፍት የሚሰሩት በመደበኛ የሥራ ሰአት ብቻ ነው፡፡ እንዲሁም ሰነዶቹን ፈጽሞ ኮፒ ማድረግም ይሁን መገልበጥ የተከለከለ ስለሆነ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮብኛል፡፡ ያለኝ አማራጭ አብዛኛውን ጊዜ በአብያተ መጻሕፍቱ ውስጥ በመቀመጥ ጽሑፎቹን ማንበብና በተቻለ መጠን ትኩረት ሰጥቶ ማስታወሻዎችን በመያዝ ሌላ መፍትሔ ማፈላለግ ነበር፡፡

በዚህም መሰረት ጊዜዬን ካለብክነት ለመጠቀም እንዲሁም ለጥናቱ የሚረዱ ሌሎች ደጋፊ መረጃዎችን በማገኝበት በኢትዮጵያ ጥናት እና ምርምር ቤተ መጻሕፍትን በመምረጥ ጥናቱን ማከናወን ችያለሁ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

### 2.1 ክለሳ ድርሳን

ይህ የጥናት ወረቀት በማዘጋጅበት ወቅት ለምርምር ባነሳኋቸው ዜና መዋዕላት ላይ ትኩረት ያደረጉ ምርምሮችን ለማግኘት ጥረት አድርጊያለሁ። በቀጥታ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተቀራረበ ሁኔታ ጥናት ያደረጉ አጥኚዎች ያን ያህል ብዙ ሆነው ማግኘት ግን አልቻልኩም። በተወሰነ ደረጃ የኔን የጥናት አቅጣጫ የተመለከቱ፡ ሪቻርድ ፓንክረስት The Ethiopian Royal Chronicles፣ ሞልቬር "The Tragedy of Emperor Libne-Dingil of Ethiopia (1508-1540)"፣ ሃንቲንግፎርድ The Glorious Victories of 'Amda Ṣeyon, King of Ethiopia፣ አምሳሉ አክሊሉ "አጭር የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ታሪክ"፣ ዘሪሁን አስፋው "የዜና መዋዕል አጻጻፍ ስልት ናሙናዊ ምልከታ"፣ ስርግው ገላው "የንጉሥ ተክለ ኃይማኖት መጽሐፈ ስንክሳር ይዘቱና የአጻጻፍ ስልቱ" በአንድ ጎን የምጠቅሳቸው ናቸው።

ቀዳሚዎቹ ሁለቱ አጥኚዎች ከሥነ-ጽሑፋዊ መልኩ ይልቅ የታሪክ ምርምር አቅጣጫን ይዘው ያጠኑ ከመሆኑ ባሻገር ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና በእጅጉ ስስ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በተወሰነ ደረጃ ሃንቲንግፎርድ በጥናቱ ላይ ስለአጠቃላይ "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ጸሐፊ እና የጽሑፉን ሥነ-ጽሑፋዊ ብቃትና ደረጃ በማንሳት ያለውን ሐሳብ ማስቀመጥ ችሏል። እንደ ሃንቲንግፎርድ አስተሳሰብ "የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል"ን የጻፈው ሰው ለንጉሡ እጅግ ቅርብ የሆነ ክህነት ያለው ጸሐፊ ነው ሲል የራሱን ማስረጃዎች በዝርዝር ያስቀምጣል። የዜና መዋዕሉንም ሥነ-ጽሑፋዊ ብቃት እማኝ እየቀጠረ እና እርሱ የታዘበውን እንዲህ ሲል በአድናቆት ይገልጸዋል።

> Though no more than part of a general chronicle, 'The glorious victories' the most unusual production quite unlike a normal Ethiopian historical record. The outhor was probably a Priest attached to the court who accompanied the king throughout the campaigns of 1329, for none but an eyewithenss could have described them with so much detail or with such simplicity and freshness, so different form the dry style of the usual run of chronicles which, however valuable, historically, do not hold the readers interst in the same way. /1965፡ 33/

ከዚህ በዘለለ ዜና መዋዕሉን ተርጉሞ በማስቀመጥ እና ከሌሎች ሰነዶች እና ጽሑፋዊ መረጃዎች ላይ እያመሳከረ የዘመኑን አጠቃላይ ስዕልና መንፈስ ከታሪካዊ ፋይዳ አንጻር በጥልቀት ይመረምራል። በመሆኑም ከዚህ ጥናት አንጻር ተቃርቦው ውሱንና መጠነኛ ነው ማለት ይቻላል። ቢሆንም ግን ከላይ የደራሲውን ማንነት ሲያነሳ

የተጠቀመበትን የተራኪው የአተራረክ አቅጣጫ የምመለከት በመሆኑ የምንጋራቸው ውስን ጭብጦች ይኖሩናል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን በዚህኛው ምድብ ከጠቀስኳቸው ቀደምት አጥኚዎች መካከል አምሳሉ፣ ዘሪሁን እና ስርግው በተሻለ ደረጃ ለጥናቴ ቅርብ ናቸው፡፡

የአምሳሉ ጽሑፍ ዋና አላማ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍን መዳሰስ ሲሆን የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያን ሥነ-ጽሑፍ በዳሰሰበት ክፍሉ በዚህ ጥናት ላይ የተመለከትኳቸውን ዜና መዋዕሎች (የዐምደ ጽዮንን እና ዘርዐ ያዕቆብን) በማንሳት ተምልክቷቸዋል፡፡ ይልቁንም የዐፄ ዐምደ ጽዮንን ዘመን በዳሰሰበት ክፍሉ ዜና መዋዕሉን በማንሳት ሰፊ ድርሻ ሰጥቶ ተመልክቶታል፡፡ እንደ አምሳሉ አገላለጽና እምነት የዜና መዋዕሉ ጸሐፊ የቤተ-ክህነት ሰው ነው /39/፡፡ ይህም መሰረታዊ መላምት አስቀድሞ በሃንቲንግፎርድ መነሳቱን ልብ እንላለን፡፡ አጥኚው ለምን እዚህ ነጥብ ላይ እንደደረሰ ምክንያት አልሰጠም፡፡ ይሔንን ለማረጋገጥ የዜና መዋዕሉን አተራረክ ቴክኒክ በመመርመር ግምቱን ማጽናት አሊያም ግምቱን ማፍረስ ስለሚቻል የዚህ ጥናት መዳረሻ ይሔንኑ ሊያመላክት ይችላል፡፡

በሌላም በኩል አምሳሉ ሐገሪቱ (ኢትዮጵያ) ከዛ ቀደም አለማዊ የሥነ-ጽሑፍ ልምድ የላትም ነበር ለሚለው ማስረጃው አድርጎ ያቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስና ገድላዊ አጻጻፍ ስልት /39/ በእኔ ጥናት ላይ በይነ-ቴክስታዊነት በሚለው ክፍል ውስጥ የምመለከተው በመሆኑ በሌላ የስነ ተረክ ምርምር አቅጣጫ ጉዳዩን እናያለን ብዬ አምናለሁ፡፡ ከላይ ለማንሳት እንደሞከርኩትና ከጽሑፉ ለመረዳት እንደሚቻለው የአምሳሉ ዋንኛው አላማ ሥነ-ጽሑፋዊ ታሪክን መዘገብ እንጂ ለተወሰኑ ነጥቦች ትኩረት የሰጠ ሥነ-ጽሑፋዊ ሂስ ማድረግ ባለመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይራራቃሉ፡፡ ሆኖም በአንድም ሆነ በሌላ መልክ ሲለው ጠበቅ አንዳንዴም ላላ እያደረገ እኔ ላነሳቸው የምችላቸውን ነጥቦችን ዳስሷቸዋል፡፡

ሌላው ከእኔ ጥናት አንጻር የማነሳው ዘሪሁንን ነው፡፡ በርግጥ ዘሪሁን "የዜና መዋዕል አጻጻፍ ስልት ናሙናዊ ምልከታ" (1984) ሲል ባጠናው ጥናት ላይ ዋና መመልከቻ ናሙናው የዐፄ ገላውዲዮስ ዜና መዋዕል ነው፡፡ በአንጻሩ የኔ የጥናት አቅጣጫ እርሱ ካጠናበት ወይም እንደ ናሙና ከተጠቀመው ዜና መዋዕል የተለየ ነው፡፡ በሌላም በኩል ዘሪሁን አንዱን ናሙና ወስዶ ለአጠቃላይ እንደማሳያ የተጠቀመ ሲሆን በእኔ ጥናት ላይ ግን በዘመናት ቅደም ተከተል ከገላውዲዮስ አስቀድሞ የነበሩ ሁለት ዜና መዋዕሎችን በውስን ነጥቦች በመመልከት የጋራ የምላቸውን አንድነትና ልዩነት አሳያለሁ፡፡

ያም ቢሆን ግን በሁለታችንም የጥናት አቅጣጫዎች ላይ መሰረታዊ የርዕስ ጉዳይ ግንኙነትና መቀራረብ ይስተዋላል፡፡ በመጀመሪያ ሁለታችንም ዜና መዋዕሎችን ለመመልከት በመቻላችን ያመሳስለናል፡፡ በሌላ አቅጣጫም የአተራረክ ስልትን ለመመልከት በመነሳታችን ያቀራርበናል፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ ዘሪሁን በበርካታ ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን በእኔ ጥናት ላይ ግን ወደ አጠቃላይ መልክ ሊያንደረድሩ በሚችሉ ሁለት ነጥቦች (አተኩሮ እና በይነ-ቴክስታዊነት) ላይ ብቻ ማተኮሬ ሌላው ልዩነታችን ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የማነሳው አጥኚ ስርግው ገላውን ነው፡፡ ስርግው "የንጉሥ ተክለ ኃይማኖት መጽሐፈ ስንክሳር ይዘቱና የአጻጻፍ ስልቱ" የሚለው ጥናቱ ላይ መሰረታዊ ነጥቡ በመጸሐፈ ስንክሳር የተካተተውን የንጉሥ ተክለ ኃይማኖትን ታሪክ አጻጻፍ ስልት እና ይዘትን መመርመር ነው፡፡ ይህ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር በተወሰኑ ነጥቦች መለያየትና መቀራረብ ይታይበታል፡፡ ከልዩነቱ ጀምረን እንመልከት፡፡

በመጀመሪያ እኔ የምመለከተው የንጉሥን ዜና መዋዕል ነው፡፡ በመሆኑም ከቅድስና ይልቅ ሰው መሆናቸው ይጎላል፡፡ የስርግው ጥናት ግን ባለታሪኩ ንጉሥ ቢሆንም ቤተ-ክርስቲያን በቅድስና ማዕረግ የተቀበለችው ነው፡፡ ስለዚህም በራሱ የሚጠናው ሰነድ ምንነት ልዩነታችንን ይፈጥራል፡፡ ስንክሳር በቅድስና ቤተ-ክርስቲያን ያወቀቻቸው በዓመት ውስጥ ካሉ ቀናት ሰጥታቸው ታሪካቸውን መዝግባ ዘግባ የምታነሳቸው የቅዱሳን የመላዕክትና የሰማዕታት ታሪክን የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ ዜና መዋዕል ደግሞ ነገሥታቱ በቀጠሯቸው ቀለብ በሰፈሩላቸው ጸሐፍተ ትእዛዛት አሊያም በሌሎች ወዳጆች የቅርብ ሰዎች የሚጻፉ የታሪክ ዘገባዎች ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ ስርግው የአጻጻፍ ስልትን እና ይዘትን በሚመረምርበት በዚህ ጥናቱ በማመሳከሪያነትም ሆነ በማረጋገጫነት ከያዘው ስንክሳር በመውጣት ሌሎች የታሪክ እና ሃይማኖታዊ ሰነዶችን ይመለከታል፡፡ በኔ ጥናት ውስጥ ራሳቸው ዜና መዋዕላቱ እስካልጠሯቸው (አንድም ቀጥታዊ በሆነ መልክ ጠቅሰው አሊያም በማይታለፍ የመንገሪያ የመተረኪያ መንገድ ምክንያት በማስረጃነት እስካልተመሳሰሉ) ድረስ ትኩረቱ የማጠናው ቴክስት ላይ ይሆናል፡፡ በሌላም አቅጣጫ ስርግው የንጉሥ ተክለ ኃይማኖትን የስንክሳር ታሪክን እውነታነትንም ሲጠይቅና ሲያነጻጽር እናገኛለን፡፡ በእኔ ጥናት ውስጥ የታሪኩን እውነትነት ወይም ሐሰተኝነት ፈጽሞ አልመረምርም፡፡ በንባብ ጊዜዬ ውስጥ ያየኋቸው ነጥቦች እንኳን ቢኖሩም በትንተናዬ ላይ ሆን ብዬ እገድፋቸዋለሁ፡፡

በስርግውና በእኔ ጥናት መካከል ያሉ የጋራ ነጥቦች የአጻጻፍ ስልትን ለመመርመር መነሳታችን አንዱና ዋንኛው ጉዳይ ነው፡፡ እኔ ያነሳኋቸው የመመርመሪያ አቅጣጫዎች

ማለትም አተኩሮና በይነ-ቴክስታዊነት በቀጥታ በስርግው ጥናት ውስጥ አልተነሱም። በመሆኑም በጥናቶቹ መካከል ልዩነት አለ ማለት ነው።

በሌላ በኩል ከላይ ካነሳናቸው ቀደምት አጥኚዎች በተጨማሪ ከኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የተቀራረበ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት የሰሩ አጥኚዎችን ለማግኘት አሰሳ አድርጊያለሁ። በቀጥታ ሥነ-ጽሑፋዊ ምርምር ያደረጉ በብዛት ማግኘት ያዳገተኝ ቢሆንም ዜና መዋዕሎችን ተንተርሰው ምርምር ማድረግ የቻሉ የስነ ልሳን ጥናቶችን አግኝቻለሁ። እነዚህ ጥናቶች ምንም እንኳን ዜና መዋዕላትን የሚመረምሩ ቢሆም ካገኘኋቸው ሶስት ጥናቶች መካከል ሁለቱ በስነ ልሳን የመመርመሪያ መንገዶች እና በዜና መዋዕላቱ ጸሐፍትና ባለታሪኮች ላይ መሰረታቸውን አድርገዋል። የመንግሥቱ ከበደ “A historical and philological analysis of the chronicles of Emperor Sarsa Dingil (1563 — 1597)፣ 2007” እና የበለጠ መርድ “historical and philological analysis of the chronicles of Iyasu I (1682 — 1706)፣ 2008” እነዚህ ጥናቶች ስነልሳናዊ ምርምር ከመሆናቸው የተነሳ በርካታ ነጥቦቻቸው ተመሳሳይ ሆነው ማግኘት ችያለው።

መንግሥቱ ከበደ በመሰረታዊ ደረጃ ከዜና መዋዕሉ ውስጥ የማዕረግ ስሞችን፣ የቦታን እና የሰዎችን ስም ለይቶ ለመመርመር ይሞክራል። በመቀጠልም በዜና መዋዕላቱ ውስጥ ያጋጠሙትን የቃላትን ስህተትና የአገባብ ለውጥ ይተነትናል። በሌላም በኩል በዚህ ጥናት ላይ ዜና መዋዕሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመውሰድ ወደራሱ ያካተታቸውን ቴክስቶች ለይቶ ለማመላከት ጥረት አድርጓል።

ይህ ጥናት በመሰረታዊ ነጥብ አብዛኛው የመመልከቻ አቅጣጫው ስነ ልሳናዊ ምርምር በመሆኑ ልዩነታችንን የሚያሳይ ነው። ቢሆንም በተለይ ዜና መዋዕሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመውሰድ ወደራሱ ያካተታቸውን ቴክስቶች ለመመልከት የሞከረበት ሂደት በእኔ ጥናት ውስጥ በዋናነት ከምመረምረው የዜና መዋዕል የመተረኪያ ቴክኒኮች መካከል አንዱ በመሆን የሚጠና ስለሆነ የምንገናኝበት ትልቁ ነጥብ ነው። በተቀረ አጥኚው ዜና መዋዕሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመውሰድ ወደራሱ ያካተታቸውን ቴክስቶች ሲመረምር በግርድፉ ጠቅሶ ከማለፍ የዘለለ ነገር ያልነገረን በመሆኑ የተረኩ /የዜና መዋዕሉ/ ሁነኛ የመባያ መንገድ መሆኑን መግለጽ አልቻለም።

በሌላ በኩል በለጠ መርድ 3ት የኢያሱ ዜና መዋላትን በመምረጥ ይዘታቸውን በመዘርዘር አጥንቷል። የዜና መዋዕላቱ ጸሐፊዎች እነማን ናቸው? የሚለውን ጥያቄ ከዜና መዋዕላቱ ውስጥ መርምሮ ለማሳየት ፣ የተጻፉበትን ዘመን፣ የዜና መዋዕላቱ አንድነት እና ልዩነትን ለመተንተን ይሞክራል። አጥኚው የኢያሱን ታሪካዊ ማንነት እና ታሪካዊ ዳራውን

ያነሳል፤ የንጉሡን ባህርይ ይተነትናል። እንዲሁም ንጉሡ ለዘመኑ ያለውን አስተዋጽዖ ለማብራራት ይሞክራል። ግብርን ባሞሌ ማስጀመሩን፣ የኪነ-ህንጻ ማሠራቱን፣ ጽድቁን፣ ጽሑፋዊ አስተዋጽዖውን ያትታል። ከስነልሳን ምርምር አቅጣጫም በዜና መዋዕሉ ትርጎማና መሰል ነጥቦች ላይ በመነሳት ያጋጠሙትን ስህተቶች እና ግድፈቶች እንዲሁም ለውጦች መርምሯል። ይህ ጥናት ከመጀመሪያው ጥናት ጋር የጋራ የሆነ ስነልሳንን መሰረት አድርገው ያጠኗቸው ነጥቦች ላይ መመሳሰል ሲኖራቸው ከኔ ጥናት ጋር ግን በእጅጉ የተራራቀ ሆኖ ይገኛል።

ታዲዎስ ሲሳይ "A study of narrative techniques in the chronicle of Yohannes I (?aðlaf Sägäd) 2009" ሌላው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በዜና መዋዕል ላይ ትኩረታቸውን አድርገው ከተሰሩ ጥናቶች መካከል ይገኝበታል። ይህ ጥናት በቀጥታ የተረክ ቴክኒክን የሚመረምር ሲሆን የተረክ መዋቅር፣ ገጸ ባህርይ፣ የተረክ አላባዎች እና የተረክ ጊዜ የምርምር ትኩረቱ ናቸው።

አጥኚው የመረመረውን ዜና መዋዕል በድርጊያዎች ቅደም ተከተል የተደረደረ አተራረክ ሳይሆን በዘፈቀደ የሚተረክ ነው ሲል የሚደመድም ነው። መስፈሪያ አድርጎ የሚነሳበት መሰረቱ ግን ታደሰ /1970/ ለገድላት ትንታኔ በሰጠበት ክፍሉ ያስቀመጠውን የታሪክ መዋቅርን በመመርኮዝ ነው። በበኩሌ የአጥኚውን መደምደሚያም ይሁን በመደምደሚያው መንደርደሪያ ፊጽሞ አልስማማም። ምክንያቱም አጥኚውን እዚህ መደምደሚያ ላይ ያደረሰው ለገድላት መዋቅር የተሰጠው የትንታኔ አቅጣጫ ነው። ገድላት እና ዜና መዋዕላት በሁለት መሰረታዊ ነጥቦች የመለየት እድል አላቸው ብዬ አምናለሁ። የመጀመሪያው መለያቸው ገድላቱ የቅዱሱን ሰው ታሪክ የሚዘግብ ሲሆን ዜና መዋዕላቱ ግን አብዛኛውን ጊዜ የነገሥታትን ልዕልና የሚያውጅ ነው። ሁለተኛው የመለያ ነጥባቸው ደግሞ የጸሐፊዎቻቸው ማንነት ነው። ገድላቱ በአብዛኛው በቅዱሱ ሰው ደቀ መዛሙርት ወይም በቀዱሱ ሰው ገዳም ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች የሚጻፍ ሲሆን ዜና መዋዕላቱን ግን ነገሥታቱ ወይም የነገሥታቱ ልጆች ወይም ወገኖች የቀጠሩላቸውና እህል የሰፈሩላቸው ጸሐፍተ ትእዛዛት ወይም ሌሎች ናቸው።[2] ገድላቱን ቅዱሱ ሰው የማረም እና የማስተካከል እድል አብዛኛው ጊዜ የሌለው ሲሆን በአንጻሩ ዜና መዋዕላቱ ለንጉሡም ሆነ ቤተሰቡ ጣልቃ ገብነት የተጋለጠ ነው። በመሆኑም በገድላት የመዋቅር ብያኔ ዜና መዋሎችን ለመለካት መሞከር ለስህተት ያጋልጣል ብዬ አምናለሁ።

[2] በአንዳንድ ሁኔታ እንደ ቅዱስ የሚቆጠሩ ነገሥታትን ገዳማውያኑ ሊጽፉ ችንደሚችሉ ስለዜና መዋዕላት በተሰጠው ማብራያ ላይ ተጠቅሷል።

በተረፈ አጥኚው በዜና መዋዕሉ አተራረክ ውስጥ የተጋነነ ተረክ፣ ተተኳሪነት፣ መንፈሳዊ ዕውቀት፣ ጉዞ፣ የጦርነት ዘገባዎች፣ ተካተውበታል ሲል ይዘረዝራል። በተረክ አላባዊነት ገጸ ባህርይ፣ መቼት፣ አንጻር፣ ግጭትን ጠቅሶ የተነተነ ሲሆን አንጻርን ከተራኪው አካላዊ የእይታ አቅጣጫ በመመልከት በአንደኛ መደብ እና በሁለተኛ መደብ ድብልቅ ተጽፏል ይለናል። አጠኚው የዜና መዋዕሉ ተራኪ ራሱን ሲገልጽ በብዙ ቁጥር እኛ እያለ እንደሆነ ያስረዳል (27)። እዚህም ላይ በተወሰኑ ነጥቦች ጥናቶቻችን መጠነኛ ግንኙነት እንዳላቸው ለመረዳት ችያለሁ። እነዚህም የሚገናኙበት ነጥቦች የተጋነነ ተረክ፣ ተተኳሪነት፣ መንፈሳዊ ዕውቀት፣ ጉዞ፣ የጦርነት ዘገባዎች የሚሉት እኔ በማጠናቸው ተረኮች ውስጥ በጉልህ የሚታዩ ባህርዮች ሲሆኑ በአለፍ ገደምም በትንተናዬ ላይ ማንሳቴ አይቀርም። ከዚህ ባለፈ የማጠናቸውን ዜና መዋዕላት የተራኪ አኳያዎች በምመለከትበት ጊዜ አንጻርን በዋነኝነት ከማነሳቸው ነጥቦች መካከል አንዱ መሆኑ በሁለታችን ጥናቶች ውስጥ በጋራ የሚነሳ ጭብጥ ይሆናል።

ከዚህ ባሻገር በቅርብ ርቀት ላይ በገድላት እና ተአምራት ላይ ጥናቶችን መሥራት የቻሉ ጥቂት አጥኚዎችን ለማየት ሞክሬያለሁ። በቅድሚያ እነዚህ ጥናቶችን በተዛማጅነት እንድመለከታቸው ያደረጉኝን ነጥቦች ልጥቀስ።

በመጀመሪያ ደረጃ እኔ ለማጥናት የተነሳሁባቸው ዜና መዋዕላት የተጻፉበት ዘመንና በአጥኚዎቹ የተመረመሩት ጽሑፎች የተጻፉበት/የተተረጎሙበት ዘመን የተቀራረበ መሆን አንደኛው ነጥብ ነው። ምክንያቱም የዘመኑን የአጻጻፍ ስልትና ብልሐት መረዳት ያስችላልና። በሁለተኛ ደረጃ ባነበብኳቸው ቀደምት ጥናቶች ውስጥ (አክሊሉ፣ዘሪሁን) በዜና መዋዕላቱ ውስጥ የገድላትና መንፈሳዊ መጻሕፍት ተጽዕኖ በጉልህ እንዳለባቸው የተገለጠ መሆኑ ሌላኛው ምክንያቴ ነው። በመጨረሻም አነዚህ ሁለቱ ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው ጥናቶቹ ትኩረት ያደረጉት የስነ ተረክ አካል በሆኑ የመመልከቻ አቅጣጫዎች መሆኑ በተዛማጅነት እንዳያቸው የሚያስገድደኝ ሌላው ነጥብ ነው።

በዚህ መሰረት በዚህ ዙሪያ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የሰሩ አጥኚዎች ኤፍሬም እሸቱ፣ ሰለሞን ያለው፣ ዘነበ ደስታ እና አንተነህ አወቀ ሲሆኑ አራቱም የተለያየ መንፈሳዊ ደረጃ ያላቸውን መጻሕፍት ነው ለመመርመር የተነሱት[3]፤ እንደየቅደም ተከተላቸው ገድለ ቅዱሳን፣ ተአምረ መላዕክት፣ ተአምረ ማርያምን እና በድብልቅ መንፈሳዊ የግዕዝ መጻሕፍትን። በመሆኑም በተወሰነ ደረጃ ከእኔ ጥናት ጋ ያላቸውን ልዩነት እና ግንኙነት መመልከት እንሞክር።

---

[3] አንተነህ በድብልቅ የመንፈሳዊ መጻሕፍትን ከቀደምት የአማርኛ ዝርው ጽሑፎች ጋር በማነጻጸር ማጥናቱን ሳንዘነጋ።።

ኤፍሬም እሸቴ "The narrative techniques of three selected Ethiopian Hagiographys" በሚል ርዕስ ባጠናው ጥናት ላይ ትኩረት ያደረገባቸው ገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ገድለ ገብረ ክርስቶስ እና ገድለ ክርስቶስ ሰምራ ናቸው። አጥኚው የአተራረክ ብልሐትን ለማየት ሲነሳ ለመመልከቻ የተጠቀመባቸው ነጥቦች ተረካዊ መዋቅር /narrative structure/፣ ገጸ-ባህርይ አሳሳል /characterization/ እና ተረካዊ ጊዜን /narrative time/ ነው። በነዚህም ነጥቦች ላይ በማተኮር ጥናቱን ሰርቷል።

ሌላኛው አጥኚ ሰለሞን ያለው ሲሆን የጥናቱ ርዕስ "narrative structure of tammare mela'akt" የሚል ነው። ሰለሞን ለዚህ ጥናቱ የተጠቀመባቸው ድርሳናት ድርሳነ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ኡራኤልና ራጉኤልን ሲሆን አትኩሮቱንም ተረካዊ መዋቅር ላይ በማድረግ በምን በምን ደረጃ ተዋቅረው አጠቃላይ ድርሳናቱ እንደቆሙ ለማየት ሞክሯል።

በሦስተኛነት ደረጃ የምንመለከተው አጥኚ ዘነበ ደስታ ሲሆን አጥኚው "narrative time analysis in Ta''ammer Mariyam" በሚል ርእስ በሠራው በዚህ ጥናቱ ከስነ ተረክ የጥናት መመልከቻዎች በአንዱ በተረክ ጊዜ ላይ አትኩሮት አድርጓል። የሚመረመረው ተአምረ ማርያምን ሲሆን በተረክ ጊዜ ሐሳብ ስር የድርጊያ ቅደም ተከተል ማለትም ምን መቼ ተደረገ? ለምን ያህል ጊዜ ተደረገ? ምን ያህል ጊዜ ተደረገ? የሚሉትን ነጥቦች በጥልቀት ተመልክቷቸዋል።

ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የተሰሩት ጥናቶች በምናጠናው የሰነድ አይነት ፍጹማዊ ልዩነት ይስተዋልብናል። ምናልባትም ይሔ ልዩነት ለጥናታችን መዳረሻም የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ይኖረው ይሆናል። በሌላም በኩል ተደጋግሞ የሚነሳውን የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ የአተራረክ መንገድ 'ገድላዊ' መሆን አለመሆን ላይ መረጃን ይሰጣል ብዬ አስባለሁ።

ከዚህ ባሻገር ግን እነዚህን ጥናቶች ማየት እንደሞከርነው ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ ሊመለከቱ የሞከሩት የስነ ተረክ ጥናት ክፍሎችን ነው። እንደ አጠቃላይም የሚያጠኑት ሰነድ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሦስቱም የተነሱትን ነጥቦች ስንጨምቃቸው ተረካዊ (ኤፍሬምና ሰለሞን)፣ ገጸ-ባህርይ አሳሳል (ኤፍሬም) እና ተረካዊ ጊዜን (ኤፍሬምና ዘነበ) ናቸው። ከነዚህ ስነ ተረክን የማጥኚያ አቅጣጫዎች አንጻር የኔን ጥናት ስቃኘው ሦስቱም አጥኚዎች ባልተመለከቱት የስነ ተረክ ጥናት አቅጣጫ ትኩረቴን በማድረግ አተኩሮ እና በይነ-ቴክስታዊነት የሚሉትን ስለምዳስስ ሌላው የልዩነታችን አቅጣጫ ይሆናል ማለት ነው።

ከላይ ካነሳናቸውና ከተነጋገርንባቸው የኢትዮጵያን የመካከለኛው ዘመን ሥነ-ጽሑፍንና የስነ ተረክ ጥናት አቅጣጫን አንስተው ካዩ አጥኚዎች መካከል አንተነህ አወቀ "The roles of narrators in geez narratives and early Amharic didactic prose fiction" 1993 ልንጠቅሰው የምንችለው ነው። አጥኚው በዚህ ጥናት ውስጥ አትኩሮት ሰጥቶ ለግዕዝ ተረክ ማሳያ የተጠቀመው ድርሳነ ሚካኤል፣ ገድለ ተክለ ኃይማኖት፣ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ክርስቶስ ሳምራ፣ ገብረ ክርስቶስ፣ ተአምረ ማርያም እና ተአምረ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን ቀደምት የአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ በሚል ከአፈወርቅ ገ/ኢየሱስ ጀምሮ ከስምንት ያላነሱ ደራስያንን ሥራዎች ለጥናቱ ተጠቅሟል።

አጥኚው ይህን ጥናት ባጠናበት ወቅት የግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ አካል የሆኑትን ዜና መዋዕሎችን የገደፋቸው ሲሆን ያንንም ያደረገበት ምክንያት "ደረቅ እውነቶች ስለሆኑ ነው" የሚል ነው። እንደኔ እምነት የተራኪን ሚና ለማጥናት የተነሳ አጥኚ ከዜና መዋዕሎቹ ውስጥ የተራኪውን ሚና እንዲሁም በቀደምት የአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ላይ ያለውን አሻራ ማሳየት ሊዘለል የሚገባው ነጥብ አይመስለኝም። ምናልባትም አጥኚው ዜና መዋዕላቱን አካቶ ተመልክቷቸው ቢሆን የጥናቱ መደምደሚያ ሌላ ሊሆን ይችላል ወይም የደረሰበትን ግኝት የሚያጠናክር ነጥቦችን ማግኘት ይችል ነበር። ምክንያቱም ከዚህ አስቀድሞ ለመመልከት እንደሞከርነው ገድላቱና ተአምራቱ በአጠቃላይም መንፈሳዊ መጽሐፍት ከኗላ በመጡት ላይ ብቻ ሳይሆን በዘመነኞቻቸው መጽሐፍት ላይ ተጽዕኖ ማሳረፍ ችለዋል ብለው የሚያምኑ በርካታ ምሁራን አሉና (ዘሪሁን፣አምሳሉ)።

ያም ሆነ ይህ የአንተነህ አወቀ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያገናኘው አንድ የጠበቀ ጉዳይ አለው። ይህም እኔ በማጠናቸው ዜና መዋዕላት ውስጥ የምመለከተው የአትኩሮ ርዕሰ ጉዳይ በቀጥታ አንተነህ "የተራኪው ሚና" እያለ ከሚጠቅሰው ነጥብ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። ሁለታችንም የአተራረኩን አኳያ እንዲሁም የተራኪውን ርዕዮተ ዓለም ለይተን ስለምንመለከት እንገናኛለን። ሆኖም በሌሎቹ ነጥቦች ማለትም የጥናት አቅጣጫችንን ጨምሮ የምናያቸው መጻሕፍት ፈጽሞ የተለያዩ ናቸው።

## 2.2. ንድፈ-ሐሳባዊ ዳራ

ከሁሉ አስቀድመን ስለ ስነ ተረክ /narratology/ ከማንሳታችንና ከመተንተናችን በፊት የተረክን እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ምንነት አጥርተን ማለፍ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ነጥቦች በማንሳት አንድ መደምደሚያ ላይ እንድረስና በቀጥታ የስነ ተረክ ምንነትን በይነን ወደዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ ማለትም የአተራረክ ዘዴን ወደማየት እናመራለን፡፡ አስቀድመን ተረክ ምንድን ነው? የሚለውን ነጥብ ለይተን እንመልከት፡፡

### 2.2.1 ተረክ[4] /Narrative/ ምንድን ነው?

ተረክን በብያኔ ደረጃ ምንነቱን ከመተንተናችን አስቀድሞ እዚህም ላይ ቃሉን መረዳት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ተረክ የሚለው ቃል 'ተረከ' ከሚለው ግስ የወጣ ይመስላል፡፡ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ‹‹ተረከ፡ በቁሙ፡ ታሪክ ተረከ ጣፈ አወራ›› (1948፡ 903) ማለት ነው ሲሉ ይተረጉሙታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ "ተረከ፡ ስላለፈ ነገር ዘርዝሮ ተናገረ፤ አወራ፤ አወጋ፤ አተተ" (1993፡ 255) ሲል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል <u>የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u> ይፈታዋል፡፡ ከዚህ በተለየና በጥቂቱም በተብራራ መልክ 'ተረክ' የሚለውን ቃል ለመፍታት የሞከረው የተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው <u>የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u> ደግሞ

> ተረከ ፤ (መተረክ) በእየ መንግሥቱ በእየ ሀገሩ የተሠራውን የጥንቱን ነገር በእየ ጊዜውም የተሠራውን የመንግሥት ሥራን ወይንም የተደረገውን የጦርነት ወሬ ለተከታዩ ትውልድ ተረከ ወይም ያለፈውን ወግን፣ ታሪክን፣ ወሬን ነገረ ወይም ታሪከ ነገሥትን ጽፎ ለታሪክ አኖረ ፡፡
>
> ተረከ፡ አንድ መጽሐፍ ከተጻፈ በኋላ መጽሐፉ የተጻፈበትን ምክንያት ወይም በመጽሐፉ ውስጥ ምን ዐይነት ቃሎችና ልዩ ልዩ ምዕራፎች ክፍሎች ምስጢሮችም አገባቦች እንዳሉት በመቅድሙ ተርኮ ጻፈ ወይንም በልዩ ልዩ የትርጓሜ መጻሕፍትን አባባል (አፈታት) ምሥጢርን ተረጕመ ተረከ፡፡ (2002፡ 563)

ሲል ያብራራል፡፡ የተሰማ ሀብተሚካኤል ግጽውን ፍቺ ስንመለከት በሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ለይቶ 'ተረክ' የሚለውን ቃል ለመፍታት ይሞክራል፡፡ የመጀመሪያ ፍቺ

[4] በመጠሪያው "ተረክ"ን የ"narrative" አቻ አድርጎ ሲገለገል የገጠመኝ ተመራማሪ ዮናስ አድማሱ ነው፡፡ በአማርኛ መዛግብተ ቃላት ውስጥ በቀጥታ ተረክ የሚል ቃል ማግኘት አልቻልኩም፡፡ በመሆኑም በስርወ ቃል ርቢ ትርጉሙን መረዳት የሚቻል በመሆኑ በዚሁ መንገድ በመጠቀም ቃሉን በመፍታት ወደ ነጥቡ ለመድረስ ችያለሁ፡፡

ብሎ ያስቀመጠው በተለይ የመንግሥትን እና የታሪክን ዘገባ ወይም ተረክ ሲሆን በሁለት አይነት መንገድ ሊተላለፍ እንደሚችል በግልጽ አስረድቷል፤ በቃልና በጽህፈት ሲል፡፡

በመሆኑም ተረክን በቃል ሲል ለምሳሌ ተረት ተረት፣ ሐተታ ተፈጥሮ፣ የዘመን ታሪኮችና ተጋድሎዎች፣ የዘር ቆጠራና ሌሎች መሰል ጉዳዮች በተለያዩ ማህበረሰብ ውስጥ በቃል እንደሚተላለፉት ማለቱን መረዳት የምንችል ሲሆን፤ በእሳት ዳር በጉባዔ መካከል አሊያም በመስክና በአደባባይ ወዘተ የሚነገሩትን አጠቃሎ ይይዛል፡፡ በሌላም በኩል በጽህፈት ሲልም አጭር ልቦለድ፣ ረዥም ልቦለድ፣ ግጥም፣ ግለ ታሪክ፣ ጽሑፈ ተውኔት እንዲሁም በቃሉ ፍቺ ላይ እንደተጠቀሰው የታሪክና የትርጓሜ መጻሕፍት አካቶ የሚይዘውን ጽሑፋዊ አቅርቦትን ያመላክታል፡፡

ተሰማ በመጀመሪያው ትርጉም አሰጣጡ ታሪካዊ የሚባሉትን እና የታላላቆችን እሱም እንደገለጸው የነገሥታትን እና የመንግሥታትን ታሪክ መተረክና መጻፍን ነው ትኩረት ያደረገበት ነጥብ፡፡ እዚህ ላይ የታናናሾች የተገገርዎችና የግለሰቦች ታሪክ የፌጠራና ሌሎች አይነት ተረኮችን የት እንመድባቸው? ሊያስብል ይችላል፡፡ የነዚህን ጥያቄ መልሶች በመዝገበ ቃላዊ ብያኔ ለመመልከት ከመሞከር ይልቅ ከታች በዘርፉ /በትረካ/ ላይ ጥናት ያደረጉ ሰዎችን ትርጉምና ምርምር ስናይ የሚመለስ ይሆናል፡፡

በሁለተኛነት ደረጃ ተሰማ 'ተረክ' ለሚለው ቃል የሰጠውን ትንታኔ ለመዳት ትኩረት የሚሻ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህም አፈታት ውስጥ ሀቲትን፣ ፍካሬን፣ ሄስን የመተረክ አካል አድርጓቸዋል፡፡ ይህ ነጥብም ነው ኋላ ለምናነሳው የስነ ተረክ ምንነት መንደርደሪያ የሚሆነን፡፡ በአጠቃላይ መልኩ በሁለተኛው የቃሉ አፈታት ክፍል ላይ የተረኩን አፈጣጠር የሚንተራስ ሳይሆን ተረኩ ከተፈጠረ በኋላ ስለ አፈጣጠሩ ስለምክንያቱ እና ስለምስጢሩ የሚደረግን ትንታኔ ሄደት የሚያስረዳ ነው፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በተራዛሚ /በቃል እርባታ/ ለቃሉ የተሰጡ መዝገበ ቃላዊ ፍቺዎችን ነው፡፡ ተረክ ለብዮና እጅግ አዳጋች ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት በርካታ የዘርፉ ምሁራን የተለያየ ብያኔዎችን ሰጥተውት እናገኛለን፡፡ በመሆኑም በተረክ ምንነት እና ንድፈ ሐሳብ ላይ ትኩረት አድርገው ምርምር ያደረጉ እንዲሁም ተመራማሪዎችን መሰረት አድርገው ተረክን ለመበየን የሞከሩትን ደግሞ ከመዝገበ ቃላዊ ብያኔ በመነሳት ከዚህ በማስከተል እንመልከት፡፡

ኤ ኤች አብራምስ ተረክን ሲበይን "A narrative is a story, whether told in prose or verse, involving events, characters, and what the characters say and do." (Abrams 1999 :173) በማለት ነው። በዚህ የአብራምስ ገለጻ ውስጥ ልብ ልንላቸው የሚገቡን ነጥቦች የመቅረቢያ መንገዱን እርሱ ስንኝ እና ዝርው ሲል የገለጸውን ነጥብ እንዲሁም በነዚህ መቅረቢያዎች ውስጥ የሚኖሩትን አላባውያንን ነው። እርሱ ድርጊትና ንግግር ያለውን ማለት ነው።

አብራምስ ዝርው ሲል ግጥማዊ ያልሆነ ጽሑፋዊም ሆነ ቃላዊ አተራረክን ሲሆን ይህም በተረት ትረካ፣ በአጭርና ረዥም ልቦለዶች፣ በግል ታሪኮችና ሌሎችንም ሊያካትት የሚችል ነው። በስንኝ ሲል ደግሞ ተረኩ የሚቀርብበት መንገድ ዜማዊ ሆኖ ለኪነቱ ጣዕምና ለታሪኩ አይረሴነት ወዘተ በመጨነቅ የሚጻፈውን ሥነ-ጽሑፋዊ ተረክን ያካትታል። ለምሳሌ "የዱባ ፍሬና የሾላ ፍሬ"፣ "አዝማሪና የውሀ ሙላት" እና ሌሎች የከበደ ሚካኤልን ቀደምት ግጥማዊ ተረቶችን[5] ማንሳት እንችላለን (ተረትና ምሳሌ 1ኛ መጽሐፍ 1999)።

ሱዛና ኦንጋ እና ጆሲ ኤንጅል ተረክ በስፊ አቅጣጫ ሊበየን እንደሚገባ ገልጸው፤ በትዕምርታዊ ውክልና ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶች ትርጉም ባላቸው መንገዶች ግንኙነታቸውን በቅደም ተከተልና ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ማስቀመጥ እንደሆነ ያብራራሉ። "A narrative is the semiotic representation of a series of events meaningfully connected in a temporal and causal way." (Herman 2005 :13) አጥኚዎቹ የተቆራረጡ ትርጉም የማይሰጡ የተረክን ቅንጣቶችን ሳይሆን የተቀናጁና አንድ የተሟላ ታሪክን ከሚነግሩት አረፍተ ነገሮች አንስቶ ተረክ እንደሚፈጠር ያብራራሉ። እዚህም ላይ የተነሳው መሰረታዊ ነጥብ አወቃቀር እና ምክንያታዊነት ነው። አወቃቀር ስንል በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን። የመጀመሪያው ሀሳብ የአረፍተ ነገርን አወቃቀርን የሚያሳየን ነው። ይህም ሁነቶች ወይ ድርጊቶች በቅደም ተከተል የመደርደራቸውን ምን ከምን ቀጥሎ ይመጣል? መጀመሪያ የተከወነ ክዋኔ ሁለተኛ ሶስተኛ . . . የሚለውን አደራደር ይመለከታል። በሌላም አገላለጽ መግቢያ ዋና አካልና መደምደሚያው[6] የሚቀመጡበት ሂደት ማለት ነው። ምክንያታዊነት ሲባልም ከቋንቋ ሥርዐት ጀምሮ በተረኩ ውስጥ ምን ለምን ከማን ቀጥሎ ተቀመጠ ተነገረ የሚለውን ነጥብ የሚመልስ መሆን እንዳለበት የሚያስረዳ ነው።

---

[5] ምናልባትም ተረታዊ ግጥሞችም ልንላቸው እንችል ይሆናል።
[6] የታክ ተፋሰስ/ story line ለማለት ጭምር ነው።

እዚህ ላይ ምክንያታዊነት ሲነሳ ሀሳቡ አንጻራዊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የአንዱ ተራኪ አተራረክ ከሌላው የሚለይበትም ትልቁ ነጥብ የአደራደር ምክንያቱ ነው ማለት እንችላለን፡፡ አንድ ተረክ በሚተረክበት ጊዜ ድርጊቶች የሚደረደሩበት ሂደት ከጽሑፉ መሰረታዊ አላማ አንጻር ምክንያት ሊኖረው መቻሉን ከግምት ማስገባት ይኖርብናል፡፡ አንድ ተራኪ አስቀድሞ የባላንጣውን (ጸረ አቀንቃኝ) ታሪክ ነግሮን ትረካው በመጀመር ወደባለታሪኩ (አቀንቃኝ) ትኩረት ተመልሶ ሊገባ ይችላል፡፡ ወይም በግልባጩ ትረካውን ሊያከናውን ይችላል፡፡ የእነዚህ የሁለቱም የታሪክ ድርጊያ ቅደም ተከተል አደራደር በተራኪው አላማና ምክንያት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል በነሱዛና ኦንጋ ገለጻ ላይ የምናገኘው ነጥብ ከነርሱ አስቀድሞ ስነ ተረክን ያጠኑትን አጥኚዎች ጠቅሰው ‹‹ትዕምርታዊ ውክልና›› /semiotic representation/ ሲሉ የገለጹትን ነጥብ ነው፡፡ በተረክ ምንነት ላይ ከሚነሱ ነጥቦች መካከል መገለጫ ወይም መተረኪያ መንገዱ ምንድን ነው? አሊያም እንዴት ነው? የሚለው ሀሳብ ተጠቃሽ ነው፡፡

እነኦንጋ ትዕምርታዊ ውክልና ያሉት ነገር ምንድን ነው? ብለን በመጠየቅ እንነሳ፡፡ አስቀድመንም አገላለጹን ስንመለከት የስነልሳን አስተሳሰብን አቅጮ ይዟል፡፡ የአረዳድ መንገዱም ጽሑፋዊ ተረኮችን ታሳቢ ያደረገ ይመስላል፡፡ ከዚህም አንጻር አስቀድሞም የቴክስቹዋል ጥናቱ ጀማሪዎች የስነ ልሳን ተመራማሪዎች በመሆናቸው የተነሳ የተለመደ አገላለጽ እንደሆነ ምሁራኑ ይገልጻሉ (Kindt 2003፡ 333)፡፡ ሆኖም ግን ከዚህ በዘለለ የተረክን መተረኪያ መንገድ ከጽሑፍ ባሻገር ድርጊያም ጭምር እንደሆነ የሚያስረዱ አጥኚዎች አሉ፡፡ ትወና፣ ፋክራ ወይም ሌሎች በድርጊት የመተረኪያ ዘዴዎች ናቸው ሲሉ ይሟገታሉ፡፡ ከዚህም ዘለል ሲል ፍጹም ቃላት የማይገኙበት እንደ ንግግር አልባ ተውኔት አይነቶቹን ስንመለከት ትዕምርታዊ ውክልና የተባለው ጉዳይ እስከምን ሰፍቶ ሊተነተን እንደሚገባ እንረዳለን (ዝኒ ከማሁ)፡፡

ከለይ ከተመለከትናቸው ነጥቦች አንጻር ስንመለከተው ተረክ የትኛውም ዘመን ወይም የትኛውም ማኅበረሰብ ከተረክ ተለይቶ አያውቅም ብለን መደምደም የሚያስችለን መሰረት ላይ እንቆማለን (Herman 2005)፡፡ ምክንያቱም አንድ ማኅበረሰብ ወይም አንድ ዘመን ስላለፈውም ሆነ ስላለበት ያለውና የሚለው ብዙ ነገሮች አሉትና፡፡ ቢያንስ ሰው ስለመወለዱ፣ ስለቤተቡና ስለአካባቢው፣ ልራቅ ልራቀቅ ሲልም ስለአፈጣጠሩ እና ስለ ስነፍጥረት መግለጹ አይቀርም፡፡

በሌላም ሁኔታ በአንድ ጊዜና ቦታ የምናስባቸውና የምንናገራቸው ነገሮች ሁሉ በራሳቸው ጊዜ ወደተረክ ይለወጣሉ፡፡ ይህም በራሱ ተረክ የማይቋረጥና ያልተቋረጠ የሰው ልጆች ሀብት መሆኑን ያስረዳል፡፡ ከጥንታውያኑ ሚትና አፈ-ታሪክ እስከ ድህረ ዘመናዊነት "ፋቡሌሽን" ድረስ ተረክ ማዕከላዊ ጉዳያቸው /ተፈጥሯቸው/ ነው፡፡ ሁሉም ነገሮች በተረክ የተሞሉ መሆናቸውን የድህረ መዋቅር ሀሳባዊያን ያስረግጣሉ ፡፡ ለዚህም በአስረጂነት ቀጣዩን ሐሳብ መመልከት እንችላለን፡፡

> a good number of contemporary thinkers hasten to add, whatever you say and think about a certain time or place becomes a narrative in its own right. From the oldest myths and legends to postmodern fabulation, narration has always been central. Postmodern philosophers may submit that there are no longer any grand, encompassing narratives, but they also contend that everything amounts to a narrative, including the world and the self. (Herman 2005፡).

በዚህም መሰረት የተረክ ጥናት በክበረ ማማ ላይ ያሉትንና የጥንቱን ዘመን ትረካዎች ብቻ የሚመለከት አይሆንም ማለት ነው፡፡ ይልቁንም በውስጡ ስለእውነታና ሰብአዊ ፍጡራን መሰረታዊ ባህሉ-ጸን /culture-specific/ አስተሳሰቦችን ግልጽ በማድረግ በታሪኮችና ልቦለዶች ወደ ተረክ ተለውጠው የሚቀርቡ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በአንድ ባህልና ማህበረሰብ ውስጥ መልካምና መጥፎ ጠንካራና ደካማ አስፈላጊና አላስፈላጊ የሚባሉትን ነጥቦች በመያዝ እነዚህን ሀሳቦች በሚያጎላ ታሪክ ታቅፈው የሚቀርቡበት መንገድ ተረክ ነው፡፡ በሌላም በኩል በአንዳንድ ዘመን ተሻጋሪ በሆኑት ላይ ብቻ ሳይሆን ተረካዊ ቅንጣት ባላቸው የተረክ አይነቶች ላይ ሁሉ ዓለምና ተፈጥሮ እንዲሁም ምናባዊ እና ተጨባጩ የሰው ልጆች ሐሳብ ይንጸባረቃል፡፡ በመሆኑም አስቀድመን በተሰማ መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ላይ አንስተን የነበረውን ጥያቄ እዚህ ላይ እንመልስ፤ ተረክ በነገሥታት ቤተመንግሥት፣ በታላላቆች ሰገነት፣ በአማኞች ምኩራብ ላይ ብቻ ሳይሆን የሚያተኩረው አጠቃላይ ሰው አስተሳሰቡ እና አለሙ (ህዋው ሳይቀር) መሆኑን ልብ ልንል ይገባል፡፡

በዚህም ምክንያት ነው ተረክ በየምርምሩ ዘርፍ ላይ ትልቁን ድርሻ በመያዝ ላይ የሚገኘው፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ የተረክ ምንነት በሥነ-ጽሑፍ ትወራዎች፣ በስነ ልቦና፣ በስነ መለኮት፣ እንዲሁም በህግ ንድፈ ሐሳብ የጥናት እና በሌሎች በርካታ መስኮች ውስጥ በእጅጉ ታዋቂ እየሆነ መምጣት ችሏል (Kindt 2003፡ 35)፡፡ በተለይም የነገረ-ሰበዕ /humanities/ የምርምር ዘርፎች ላይ ተረክ መሠረታዊ የመመርመሪያ እና የመመራመሪያ

ነጥብ ሆኖ ይታያል፡፡ ከሁሉ በላይ በሥነ-ጽሑፉ ዘርፍ ተረክ ማዕከላዊውን ስፍራ ይዞ እናገኘዋለን፡፡ በዚሁ የጥናት ዘርፍ ላይ ተረክ የሚጠናበት መንገድ ስነ ተረክ /narratology/ በመባል ይታወቃል፡፡

## 2.2.2 ስነ ተረክ /narratology/ ምንድን ነው?

የተለያዩ ምሁራን በስነ ተረክ ዙሪያ የተለያየ አመለካከትና አስተሳሰቦች አሏቸው፡፡ የስነ ተረክ ጥናትን በቀዳሚነት የስነ ልሳን ጥናት ላይ የተሰማሩ አጥኚዎች /መዋቅራውያን/ የጀመሩት ቢሆንም በኋላ ድህረ መዋቅራዊነት በሚባለው እንቅስቃሴ 1960ዎቹ የበለጠ በመስፋፋት በሌሎችም የምርምር ዘርፎች ውስጥ በስፋት ትኩረት እያገኘ እንደመጣ መዛግብት ይጠቁማሉ (Prince 2008፡115)፡፡ ይህ የምርምር ዘርፍ አስቀድመን ለማየት እንደሞከርነው በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ውስጥ ትኩረት ከማግኘት በዘለለ የተለያዩ የአስተሳሰብ ፈለጎችና ትምህርት ቤቶች /school of thought/ ሳይቀሩ ተስበውበት የየራሳቸውን አስተሳሰብና እይታ የሚያነጽሩበት ለመሆን ችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው የስነ ተረክ ብያኔዎች የተለያዩና ሰፊ የሆኑት፡፡ ስነ ተረክን እንደ ሥነ-ጽሑፍ ምርምር ዘርፍ አንድሪው ቤንት እና ኒኮላስ ሮይል እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> Narratology: the field of critical and theoretical inquiry concerned with analysis of the underlying narrative structure or form of literary and other texts. Originating in the structuralist desire to produce a quasi-mathematical modelling of the deep structure of all narrative texts, recent developments in the field have encompassed poststructuralism, (Bennett 2004፡ 293)

ስነ ተረክ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በተመረጠ የተረክ መዋቅርና ስነ ጽሑፋዊ ጉዳዮች ላይ ሂሳዊና ንድፈ ሐሳባዊ ትንታኔ ማድረግ ነው፡፡ አስቀድሞም መዋቅራውያን የተረክን መዋቅር ጥልቅ ምርመራ በማድረግ ሂደት ውስጥ የተፈጠረ ቢሆንም አሁን በድህረ መዋቅራዊነት ውስጥም ትኩረትን እንዳገኘ መረዳት እንችላለን፡፡ በመሆኑም በዚህ ብያኔ ላይ በመንተራስ ከላይ በተወሰነ ደረጃ ለማስረዳት እንደሞከርነው ስነ ተረክ ሥነ-ጽሑፋዊ የሆኑና ሌሎች ቴክስቶች ላይ በመመስረት የተመረጡ መዋቅሮችን ወይም ቅጥጦችን መርጦ ሂሳዊና ንድፈ ሐሳባዊ ምርምር የማድረግ ሂደት ነው ማለት እንችላለን፡፡

ስነ ተረክ በሁሉም ሥነ-ጽሑፍ ዘሮች ላይ ያለውን የተረክ አጠቃላይ ንድፈ ሐሳብ እና ሂደት የሚያመላክት ቃል ነው፡፡ በተለይም የተረክ አይነቶችን፣ የተረክ መዋቅሮችን ወይም የተለያዩ አይነት አወቃቀሮችን፣ የተለመዱ የመተረኪያ መንገዶችን እና ተናጋሪው

ማን ነው? እና ተራኪውን እንዲሁም በስውርና በግልጽ ለማን ነው ታሪኩ እየተተረከ ያለው? የሚለውን ሀቲት አካቶ ይይዛል (Abrams 1999፡ 173)፡፡

ሲይሞን ቻትማን Story and Discourse በሚል መጽሐፉ ውስጥ የተረክ ንድፈ ሐሳብን በተነተነበት ክፍሉ ላይ የመዋቅራውያን አስተሳሰብን በመንተራስ ከዚህ በታች ያለውን ትንታኔ ይሰጣል፡፡

> Stracturalist theory argues that each narrative has two parts: a story_(histoire), the contet or chain of events (actions, happnings), plus what may be called the existents (characters, items of setting); and a discourse (discours), that is, the experession, the means by which the content is communicated. In simple terms, the story is the *what* in a narrative that is depicted, discourse the *haw*. (Chatman 1983፡ 19)

ከላይ ቻትማን እንደገለጸው የተረክ ጥናት በሁለት ተከፍሏል፤ "ምን" በተረኩ ውስጥ ተከናወነ የሚሉትን ጥያቄዎችን የሚመልሰው የታሪክ ክፍሉን እና "እንዴት" ተከናወነ የሚሉትን የሚያጠና እና የሚያብራራው የሀቲት ክፍሉ፡፡ ቻትማን ባነሳው በመጀመሪያው አከፋፈል ላይ ተረኩ የተላለፈበትን ሂደት የሚያብራራው መዋቅራዊነቱ ጎልቶ ሲታይ በሁለተኛው ክፍሉ ውስጥ ደግሞ ተረኩ የሚተላለፍበት መንገድ፣ ሀቲት ይታይበታል፡፡ በዚህ ሀቲት ስርም የአጠቃላይ ተረኩ ቅርጽ እና አሳቤው የሚተነተንበት ክፍሎችን እንደሚይዝ ያስረዳል (ዝኒ ከማሁ)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስነ ተረክ ከተለመዱት ሥነ-ጽሑፋዊ ሂሶች ተረኩ እንዴት ባለ ሁኔታ ተተረከ/ተነገረ፣ የተረክ ቅርጻዊ አላባውያን ወይም በተራኪው፣ በሚተረክለት /Narratee/፣ እና በከዋኝ/ደራሲ በመሰሉ በሌሎች ነጥቦች ላይ ባለው የአተናተን እና የአተያየት መንገድ ይለያል (Quinn 2006፡ 278)፡፡

የተረክን ድንበር ለማወቅ አስቀድሞ በተረክና ተረክ ባልሆኑ ጉዳዮች መሐል፣ ወይም ተረክን በራሱ እና በብቃቱ ምንነት መሐል ያለውን ልዩነትና አንድነት ማወቅ ይገባል፡፡ ይህንንም ስንል ተረክ ይሄ ነው ለማለት ተረክ ያልሆነው ምንድን ነው? ብለን መለየት አንደኛው ተረክን የመለያ መንገድ ነው ማለታችን ነው፡፡ ሁለተኛው ተረክን የማጥኛ እና የመለያ አቅጣጫ በተረክና የተረክን ጥንካሬ፣ የዚህ ዘርፍ የዚያኛው ብለን በምንፈርጅበት መመዘኛ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ድንበር ማበጀት ነው፡፡ ይሔን የማጥኛ መንገድንም ነው በስነ ተረክ ንድፈ ሐሳብ ውስጥ የምናገኘው (Kindt 2003: 1)፡፡

በስነ ተረክ አጥኚዎች ዙሪያ በራሱ በተረክ ምንነት ላይ ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡ አንዳንድ ተመራማሪዎች ሁሉም ነገር ተረክ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ይሔን ሀሳብ አይቀበሉም፡፡ ሁሉ ነገር ተረክ አይደለም ባዮቹ የሚያቀርቡት ምክንያት

ተረክ ባህል ላይ የተመሰረተ ጥገኛና፤ በአውድ የተገደበና ብቻውን መቆም መገለጽ የማይችል ነው የሚል ነው (ዝኒ ከማሁ)። እነዚህኛዎቹ የስነ ተረክ ተመራማሪዎች ከራሱ ከተረኩ ምንነት ላይ ጀምሮ ልዩነት ያስቀምጣሉ። በመሆኑም ከላይ እንዳነሳነው የተረክን ምንነት ለማወቅ ተረክ ያልሆኑትን መለየት አንደኛው መንገድ እንደሆነ ይጠቁማሉ። ሁሉም ነገሮች ተረክ የሚሆኑ ከሆነ ተረክ ያልሆኑትን ማግኘት ያዳግተናል። ስለዚህም የአንድ ነገር መሆን በማይሆነው ነገር መኖር የሚታይ በመሆኑ የዚህ ጥናት አቅራቢ ሁሉም ነገሮች ተረክ ናቸው የሚለውን ድምዳሜ አይቀበለውም።

ኤፍሬም እሸቴ የተረክን ምንነት የሚወስኑ አምስት ነጥቦችን ሚካኤል ቱሌንን ጠቅሶ በዚህ መልኩ አስቀምጧል። አንደኛ ተረክ ይሁነኝ ተብሎ የሚፈጠር ነው፣ ሁለተኛ የራሱን አተራረክ የሚፈጥርና ከቀደሙት የሚቀዳው ነገሮች አሉት፣ ሦስተኛ ባለአላማ ነው፣ ከዚህም የተነሳ ጅማሬ መሀል እና ፍጻሜ አለው፣ አራተኛ ተራኪ /ነጋሪ/ አለው፣ አምስተኛ ከተራኪው እና ከአንባቢው ታሪኩ የጊዜና የቦታ ርቀት ያለው መሆኑን ያብራራል (ኤፍሬም 2007፡12)።

በመሆኑም አንድ ተረክን ተረክ ለማለት ይሁነኝ ተብሎ የሚፈጠር፣ የሚነገር፣ የሚከወን መሆን አለበት። አለበለዚያ ስርክ የምንኖረው ኑሮ ሁሉ ተረክ ነው ማለት ይሆናል። በሌላም በኩል ተረክ ስንል ከዚህ ቀደም ተረኮች የሚኖራቸውን የአተራረክ መንገድ ወይም የተረክ አላባውያንን በውስጡ ሲያካትት የሚችልበት ሁኔታ አለ። ከነርሱ በመነሳት ነው የራሱን አዲስ ተረክ የሚሠራው። ይሔንንም ሲያደርግ አንዳች ሲያከናውነው የሚፈልገው አላማ ይኖረዋል። ይህ አላማ እንደተረኩ አይነት እና እንደተራኪው መሻት የሚወሰን ይሆናል። በሌላም በኩል ሲጀምር መጨረሻ ሲኖረው ይገባል። በመሆኑም የተሟላ ተረካዊ አካል ይኖረዋል፤ ጅማሬ ዋና አካል እና ፍጻሜ የምንለውን ማለት ነው። ይሔንንም ሥርዐት በመጠበቅ ታሪኩን የሚተርክ ተራኪ ሊኖረው ግድ ነው። ተራኪውም ሆነ አንባቢው ለተረኩ እንግዶች ናቸው። በዚህም መስፈርት መሰረት ተረክን ተረክ ካልሆኑ ጉዳዮች ለይተን ማየት እንችላለን።

በሌላ አቅጣጫ አንዳንድ የስነ ተረክ አጥኚዎች ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የተረክን ምንነት ሲያስቀምጡ "ቃላዊ የድርጊያ ወይም የድርጊያዎች ቅደም ተከተላዊ ነገራ ነው" ይሉታል፤ ሌሎች ደግሞ ማንኛውም አይነት ወኪላዊ ክዋኔዎች ማለትም ቃላዊ ያልሆኑም ቢሆን ተረክ ልንላቸው እንችላለን ይላሉ። የተቀሩት ደግሞ በበኩላቸው ተረክ የምክንያትና ውጤት መቀናጀት የሚፈጥሩት ነው ብለው ያምናሉ። በመሆኑም ስነ ተረክ በተለያዩ ጥበባዊ መስኮች ውስጥ ያለን አተራረክ ማለትም ስዕልም፣ ፊልምም፣ ሙዚቃም

ሆነ ሥነ-ጽሑፍ ሊኖራቸው የሚችሉትን ትረካ የምንመረምርበት የጥናት መስክ ነው (Coste 1989: 34፣ Childs 2006: 151)። ስነ ተረክ በሚተረኩ ታሪኮች ላይ ያለን ብቃት ለይቶ የማሳየት እና በተረኮች መሐል ያለ ተመሳሳይነትን እና የጋራ ነጥቦችን ማለትም በይነ-ቴክስታዊነትን በተጨባጭ አስረጂ ያረጋግጣል። ይሔንን አመለካከት ስናነሳም ከላይ በቱሌን ዝርዝር ከተመለከትናቸው የተረክ መገለጫ ባህርያት አንጻር በሁለተኛ ደረጃ ያነሳነውን የሚታከክ ነጥብ ሆኖ እናገኘዋለን።

ስነ ተረክ አጠቃላይ የተረክን ንድፈ ሐሳብ እና ዘልማድን ከሁሉም የሥነ-ጽሑፍ ማያ መንገዶች አንጻር የሚመለከት የምርምር ዘርፍ ነው። በተለይም የተራኪዎችን አይነት፣ የተረኮች ቅርጻዊ አላባዎች የሚቀናጁበትን አኳኋን፣ ያሉትን የመተረኪያ መንገዶች፣ ስለ መተረኪያ ጉዳዮች እና ራሱ የተራኪን ማንነነት በሚተነትኑ የሀቲት አይነቶች፣ በአጠቃላይ የተራኪውንና የሚተረክላቸውን ሰዎች ማንነትና ምንነት እንዲሁም ለምንነት የሚፈተሽበት መንገድ ነው (Abrams 1999፡ 173)።

በመሆኑም ስነ ተረክ ስለተረክ የሚያጠና ሳይንስ ነው ብለን መደምደም ብቻ በቂ ስለማይሆን የሚያጠናበትን ዘዴና የአጠናን ንድፈ ሀሳቦች ማወቅ ተገቢነት ይኖረዋል። በስነ ተረክ አጠናን ዙሪያ የተለያዩ አይነት ንድፈ ሐሳቦች አሉ። ከነዚህ መሐል Narratology in the Age of Cross-Disciplinary Narrative Research በተሰኘው መጽሐፍ ላይ በዚህ ደረጃ የማጥኛ መንገዶቹን የሚከፈሉ መሆኑ ተጠቅሶ እናገኛለን።

የመጀመሪያው ንድፈ ሐሳብ ፦ መሰረታዊ ገላጫዊነት /basically descriptive/ ጎልቶ የሚሰማበት ፣ ስለጥቂት ነገሮች በማንሳት የማብራራት አቅጣጫን የሚከተል ነው። ለምሳሌ በአንድ ዘውግ ውስጥ ስለሚገኙ የተራኪ አይነቶች፣ ግልጽ የሆኑ ገጸዊ ንባብ /ቴክስቱዋል/ ዳሰሳዎችን የሚያይ ነው። ከቴክስቱ ባልዘለለ ሁኔታ የገጸ-ባህሪውን አሳሳል፣ የተራኪውን መደብ፣ የመቼትና መሰል ተረካዊ ጭብጦችን በመግለጽና እሱኑ በማብራራት ላይ የተመሰረተውን የስነ ተረክ የአጠናን ትኩረት አቅጣጫ የሚይዝ ነው።

በሁለተኛ የምናገኘው ንድፈ ሐሳብ፦ ከመጀመሪያው አንጻር ሲታይ ጥልቀት ያላቸውን እሳቤዎችን፣ ንድፈ ሐሳባዊ እይታዎችን፣ የተረኩን ተፈጥሮ፣ አገልግሎት ወይም ከሌሎች አቻ ቴክስቶች ጋር ያለውን የልዩነት ድንበር እንደመፈተሽ ያሉ በቀጥታ ከቴክስቱ ውስጥ የሚያስስ እና የሚመረምር የተረክ ጥናት አቅጣጫ ነው።

በሁለተኛነት ያነሳነው ንድፈ ሀሳብ በተረኩ ገጸዊ ንባብ ላይ ከመመርኮዝ ይልቅ ገጹን ሳይለቅ አውዱን አውዱን ይዞ ገጹን ሊያጠና የሚሞክር አጠናን ነው። የተረኩን

አፈጣጠር የሚመረምር የተረኩን ጥቅም ዘርዝሮ የሚመለከትና የሚያመላክት፣ ከሌሎች ቴክስቶች አንጻር በትኖ ፈታትቶ መልሶ የሚያስር የሚገጥም የምርምር ሂደት መሆኑን ያስረዳል።

ሦስተኛው ንድፈ-ሐሳብ ፦ አጠቃላይ በከፊል ትርጓሜ የተግባቦት ንድፈ ሐሳብ ሥነ ልሳንን ወይም አጠቃላይ የክዋኔ ንድፈ ሐሳብን ተንተርሶ የሚጠናበት መንገድ ነው። ይህ የአጠናን መንገድ ከስነ ተረክ እና ከተረክ ግንኙነት ውጪ ያሉ የጥናት ዘርፎችን የሚነካ ነው። ከሁሉ አስቀድሞ ሦስተኛው ዓይነት የጥናት ንድፈ ሐሳብ የስነተረክ አካል መሰረታዊ አላማ አይደለም ሲሉ ተመራማሪዎች ጥያቄ ያነሱበታል። ምክንያቱም ቀደምት መዋቅራውያን ተረክን ለስነ-ሰብዕ እና የነገረ-እውቀትን ምንጭ ለማጥኛ ይጠቅማል ብለው የሚከተሉት መንገድ ነውና። ሆኖም ስነ ተረክ የሚያጠናው አንዱና ብቸኛው ጉዳይ ተረክን እንጂ አዕምሮን ወይም የሰው ተፈጥሮን አይደለምና የመጀመሪያ እና ሁለተኛ የማጥኛ መንገዶች ለስነ ተረክ ጥናት የተሻሉት ናቸው ሲሉ ያብራራሉ (Heinen 2009፡ 3)።

በሌላም አቅጣጫ ተረክን በምንመረምርበት ወቅት አትኩሮት ሰጥተን ልንመረምራቸው ከሚገቡን ጉዳዮች መካከል ጊዜ፣ ገጸባህሪ እና አተኩሮ ዓበይቱ ናቸው (Herman 2005፡ 70)። ይህን ስንል ግን በተረክ ጥናት ውስጥ ዋንኛ ጉዳይ የሆኑት ነጥቦች እኒህ ብቻ ናቸው ማለታችን አይደለም።

በዚህም መሰረት ከላይ ካየናቸው የመመርመሪያ አቅጣጫዎች አንጻር ስነ ተረክን ለመመርመር ስንነሳ ድንበር እና ከለላችንን እንዲሁም የትኩረት አቅጣጫችንን ለይተን እንድንገባ ያስፈልጋል። በመሆኑም የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫው ምን ምን እንደሆነ ለይቶ ማስቀመጥ አግባብነት ይኖረዋል። ከላይ ለማየት እንደተሞከረው የስነ ተረክ ጥናት ሰፊና ጥልቅ ነው። በተጨማሪም በሁሉም የመመርመሪያ አቅጣጫዎች ውስጥ በአንድ ጊዜ መግባት ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም። ስለዚህም በዚህ ጥናት ላይ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚታዩት ነጥቦች ዜና መዋዕሎች ውስጥ ያሉት የአተራረክ ብልሀቶች ናቸው፤ በመሆኑም ከመተረኪያ ብልቶች ውስጥ አተኩሮን /focalization/፣ ዜና መዋዕላቱ እርስ በእርሳቸው እና ከሌሎች መጽሐፍት ጋር ያላቸው ህብር በይነ-ቴክስታዊነት /intertextuality/ን ለይቼ እመለከታለሁ። እነዚህኑ መመልከቻ ነጥቦች በመንተራስም የማገኛቸውን የጋራ ባህርያትን እና ልዩነትን መመርመር ላይ ትኩረት የማደርግ ይሆናል። በመሆኑም በምድብ አንድ ያለውን የማጥኛ አቅጣጫና በምድብ ሁለት ያለውን አቅጣጫ በጥናቴ አደባልቄ እጠቀማለሁ ማለት ነው።

በመጨረሻም በእነዚህ የማሄጃ መንገዶችም ላይ የጠራ ግንዛቤ እንዲኖር ለማስቻል አተኩሮ፣ እና በይነ-ቴክስታዊነት የተባሉትን ጉዳዮች አስቀድሞ ማስረዳትና ግልጽ ማድረግ ስለሚገባ ይሄንኑ ለመመልከት እንሞክር።

### 2.3.2.1 አተኩሮ / focalization /

አተኩሮ /focalization/ በስነ ተረክ ጥናት ውስጥ ትኩረት ካገኙ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። በርካታ አጥኚዎች እና የስነ ተረክ ምሁራን ይሄን ነጥብ አኲያ፣ ርዕዮት፣ ግንዛቤ ወዘተ ለሚሉት እሳቤዎች ማቀፊያነት ይጠቀሙበታል። አንዳንዶቹም አጠቃላይ የአተኩሮን እሳቤዎች በአኲያ /point of viwe/ ገለጻዎች አካተዋቸው እናገኛለን። ሌሎች ደግሞ አኲያን ለሁሉም ማካተቻ ያደርጉታል ለዚህም ክራውስ ጆንን መጥቀስ ይቻላል (Herman 2007: 97-98) ።

ፎካላይዜሽን እጅግ አስቸጋሪና በብዙዎች ዘንድ አነጋጋሪ ከሆኑ የስነ ተረክ ጥናት መስኮች መሀል አንዱ ነው። (Heinen 2009፡ 171) እነዚህ አነጋጋሪነቶች የሚመጡት ከተለያዩ ነጥቦች አንጻር ሲሆን 'አኲያ /Point of view/ (አተኩሮ Focalization)' የምንለውን አስተሳሰብና አረዳዳችንን አስፍተን እንድናይ ያስገድደናል። የዚህም ምክንያት 'አኲያ /Point of view/ (አተኩሮ Focalization)' ታሪኩ የሚነገርበት የአተራረክ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የተራኪው ማንነትና ርዕዮተ ዓለም እንዲሁም የአንባቢው መረዳት ዝንባሌ ወዘተ በዚህ ስር አብረው የሚታዩ ነጥቦች በመሆናቸው ነው። በሌላ አባባል ጉዳዩ በማን ነው? እንዴት ነው የሚቀርበው? ብቻ ሳይሆን በማን አይን ነው የታየው? የሚለውን ጥያቄና ለማን እና ለምን አላማ ነው የተተረከው? ያም በምን አይነት አቅጣጫ ነው የተነገረው? የሚለውንም ጠልቀን የምንመረምርበት አስተሳሰብ በውስጡ አቅፏል (Horstkotte, 2005፡ 25-44)።

ከዚህ በላይ ዘርዘር ባለ መልኩ Seymour chatman አኲያን በሶስት አቅጣጫ ዘርዝሮ ይመለከተዋል። ቻትማን በገለጻው ውስጥ አኲያ ሲል የገለጻቸው አስተሳሰቦች እና ትንታኔዎች ሌሎች አተኩሮ እያሉ ለሚበይኑት እሳቤ አቻ ሆኖ እናገኘዋለን። እንደቻትማን አባባል አኲያን ስናነሳ ቢያንስ በቀላሉ ወደህሊናችን ሊመጡ የሚችሉ ፍቺዎች እኒህ ናቸው ሲል ያብራራል።

A) Literal: through someone's eyes (perception);
B) Figurative: through someone's world view (ideology, conceptual system, *weltanschauung*, etc);
C) Transferred: from someone interest-vantage (caracteraizing his general interst, profit, welfare, well beig, etc). (chatman 1983፡ 151)

በመሆኑም በአንድ ተረክ ውስጥ ያለ ተራኪን ስንመረምር የተራኪውን የእይታ አቅጣጫ ወይም አካላዊ ስፍራ፣ የተራኪውን ለነገሮች መረዳት ያለውን ደረጃ ወይም ርዕዮተ ዓለም እንዲሁም የተራኪውን አላማ መረዳት እንችላለን። ይህንንም ቻትማን perception, conception, interest point of view ሲል ይገልጻቸዋል።

ይሄንኑ እሳቤ ዳኛቸው ወርቁ <u>የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ</u> በሚለው መጽሐፉ ላይ እንዲህ ያብራራዋል።

> አኪያዎች አንድን ሁኔታ ወይም ድርጊያ ከቦታ፣ ከርዕዮተ-ዓለም ወይም ከእለት በእለት ኑሮ አንጻር መመልከቻ የሆኑ፡ ተራኪውም ሆነ ገፀ-ባህርይው፤ የት ሆኖ በማን አይን አየው? ወይም ይህን ለማለት ያስቻለው እምነቱ፣ አስተሳሰቡ፣ የሞራል መለኪያው፣ በጠቅላላው ዓለምን መመልከቻው እንዴት ቢሆን ነው? ወይም ካለበት የእለት በእለት ተግባራዊ ህይወቱ አንፃር ሲታይስ እንዴት እያደረገው ወዴትስ እየመራው ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉን ናቸው። (ዳኛቸው 1977፡ 299)

በሌላ አቅጣጫ Silke Horstkotte 'አተኩሮ' በስነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ያለውን እይታዊ መልክ /እሳቤ/ የሚያስረዳ ከመሆኑ ባሻገር በጥበባዊ ሥራው እና በተቀባዩ መካከል ያለ መገናኘትም ጭምር እንደሆነ ያብራራል። አሲያም በጥበባዊው ሥራው (በተረክ)ና በተረክ ትንታኔ መካከል ያለ ቀመርም ጭምር ነው ማለት ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ አተኩሮ /Focalization/ በአተኳሪው (focalizor) እና በሚተኮርበት ነገር (focalize) መካከል ያለ ግንኙነትን እንድንረዳ እንደሚያደርግ ይገልጻል። እንደ Horstkotte አገላለጽ አንጻር/አኪያ /perspective or point of view/ እና አተኩሮን አቀላቅሎ እና አደባልቆ ማየት ያረጀ አገላለጽ ሲሆን ይህም አረዳድ ታሪኩን በምንረዳበት ደረጃ (levels of story) እና በተረኩ (text) መካከል ግልጽ የሆነ ድንበር ማበጀት ያልቻለ መሆኑን ያስረዳል /2005፡ 27-28/። ከላይ ያነሳነውን ነጥብ የሚያጠናክርልን የሉሲ ሄርማን እና የባርት ቨርቬክ ትንታኔ እንዲህ ይገልጸዋል The term [focalization] refers to the relation between that which is focalized – the characters, actions, and objects offered to the reader – and the focalizer, the agent who perceives and who therefore determines what is presented to the reader. (2005: 70)

ቃሉ እንደሚያስረዳው አተኩሮ አትኩሮት በሚሰጣቸው ገጸ ባህርያት እና ድርጊቶች ላይ እንዲሁም ይሔንን አትኩሮትን በሰጠው አካል (ተራኪ) መሐል ያለ ግንኙነትን የሚመረምር ነው። በመሆኑም ቃሉ የሚያመለክተው የተረኩን አቀራረብ ብቻ ሳይሆን

አቅራቢውንም በመሆኑ በጥልቀት ልንመለከተው ያስችለናል፡፡ Tatjana Jesch እና Malte Stein በአንጻር እና በአተኩሮ መካከል ያለውን ልዩነት ሲያስረዱ በካሜራ ይመስሉታል፡፡ የካሜራው የእይታ አቅጣጫን 'አንጻር' ልንለው ስንችል አተኩሮ የሰጠው ክፍሉን በ'አተኩሮ' ልንመለከተው እንችላለን (Hühn 2009: 65)፡፡

ከላይ ባነሳነው የአኪያ እሳቤ ታሪኩ የሚተረከው በማን የመመልከቻ አቅጣጫ /አንጻር/ ነው? የሚለውን ጥያቄ ከሚመልሳቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ በዚህም እያነበብን ወይ እየሰማነው ያለው ተረክ እየተረከልን ያለው ማን ነው? ለሚለው ጥያቄያችን መልስ ይሰጠናል፡፡ ለምሳሌ ተራኪያችን ከባለታሪኮቹ አንዱ ሆኖ ሲመጣ አንደኛ መደብ በምንለው ተራኪ ልንመድበው እንችላለን፡፡ የሚያይበት መጠን ውስናዊነቱ ጎልቶ ሲታይ የሚያይበትም የእይታ አቅጣጫ ከታሪኩና ከገጸ ባህሪው የእይታ አቅጣጫ በመሆኑ 'ውስጣዊ አንደኛ መደብ ተራኪ' ልንለው ይቻለናል፡፡ ይሄንንም ተንተርሰን የተራኪያችንን አቅምም የምናውቅበት እምነታችንን የምንጥልበትና የማንጥልበት ሆኖ ልናገኘው እንችላለን (Baldick 2001:98)፡፡

በሌላም በኩል በሁሉን አወቅ ተራኪ ታሪኩንና ባለታሪኮቹን በእኩል አቅጣጫ የሚመለከት በመሆኑ ውስን አተኩሮ የሌለው፣ ሁሉንም በሁሉ አቅጣጫ የሚያይ ነው ልንል እንችላለን፡፡ ይሄንም ልንል የቻልነው ከአንድ ከተወሰነ ገጸ ባህርይ ወይም የታሪክ ጊዜና ቦታ ውጪ በሁሉም ስፍራና ወቅት በታሪኩ ውስጥ ተገኝቶ የሚተርክ በመሆኑ የትኩረቱ ሁኔታ ሁሉም እና በሁሉም ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም ይሔንን የተራኪ አይነት 'ውጫዊ ተራኪ' እንለዋለን፡፡ ምክንያቱም ከላይ ካነሳው የተራኪ አይነት በተቃራኒው በሚተረከው ውስጥ ተሳታፊ ሳይሆን ታዛቢና ተመልካች ሆኖ ስለምናገኘው ነው፡፡

ከላይ የተመለከትናቸውን የመተረኪያ አንጻር አይነቶችን ማንፍሬድ ጃን እንዲህ ይገልጻቸዋል፡፡ ማንፍሬድ ጃን በዚህ ማብራሪያው ላይ አተኩሮን የአኪያ፣ አንጻር /Point of view, perspective / አቻ አድርጎ ነው የሚገልጸው፡፡

ሀ/ ውሱን አተኩሮ አልባ /non-focalization or zero-focalization/:- የዚህ አይነት የተራኪ አንጻርን ሁሉን አወቅ የምንለው ሲሆን በሁሉም ጉዳዮችና ሁኔታዎች ውስጥ በጥልቀት እና በእኩል ደረጃ መተረክ የሚችለውን የመተረኪያ (የመመልከቻ) አይነት ነው፡፡

ለ/ ውስጣዊ አተኩሮ /ተራኪ/ internal focalization ፡- በታሪኩ ውስጥ ተሳታፊ በሆነ ወይም በሆኑ ተራኪዎች የሚቀርብ ነው፡፡ በመሆኑም የሚነገረው ታሪክ በተራኪው ግንዛቤ፣ በመረዳትና የተረዳውን በመግለጽ ብቃቱ እንዲሁም በአመለካከቱ ተጽዕኖ ስር የወደቀ ይሆናል፡፡ ውስጣዊ አተኳሪ /ተራኪ/ በሦስት ይከፈላል፡-

1. ቋሚ አትኳሪ /ተራኪ/ fixed focalization ፡- ሙሉ በሙሉ በአንድ ተራኪ ብቻ የሚቀርብ ነው፡፡
2. ተለዋዋጭ አትኳሪ /ተራኪ/ Variable focalization ፡- ከአንድ በላይ ተራኪዎች ተረኩን የሚያቀርቡበት መንገድ ነው፡፡
3. ተዳግሞ አትኳሪ /ተራኪ/ Multiple focalization ፡- ይህ የተለየ ተለዋዋጭ አተኩሮ /ተራኪ/ አይነት ሲሆን ስለአንድ ታሪክ ወይም የተረክ አካል ከአንድ በላይ የሆኑ አካላት በተደጋጋሚ ወይም በድጋሚ የሚተርኩበት መንገድ ነው፡፡ ይህ አይነት አተራረክ አንዱ ድርጊት ከሁለቱ አትኳሪ ተራኪዎች አንጻር ያለውን ስእልና ትርጉም እንድናውቅ ይረዳናል፡፡

ሐ/ ዳረኛ አተኩሮ /ተራኪ/ External focalization ፡- ይሄኛው የተራኪ አይነት ራሱን ከድርጊቱ ከጉዳዩ ውጭና ዳር ተመልካች በማድረግ የሚነግረን መረጃዎች በበርካታ ደረጃዎች የተገደበ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከዳር ሆኖ ያየውንና የሰማውን ብቻ ለይቶ ያሳየናል (Herman 2007: 97-98)፡፡

በመሆኑ አተኩሮን ስናጠቃልል አንድ ነጥብ ላይ መድረስ እንችላለን፡፡ አተኩሮ በተራኪ እና በሚተረከው ነገር መካከል ያለ ግንኙነትን የምንመረምርበት መንገድ ሲሆን፤ ይሄንንም ግንኙነት ለመመርመር የተራኪውን አኳያዎች መመልከት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በዚህም ስር የተራኪውን አንጻር፣ የተራኪውን ርዕዮተ ዓለም እና የተራኪውን አላማ በጥልቀት መመልከት ይገባል፡፡

### 2.3.2.2 በይነ-ቴክስታዊነት /intertextuality/

ሌላው በዚህ ጥናት ላይ የምናየው ጉዳይ በይነ-ቴክስታዊነት /intertextuality/ን ነው፡፡ በመሆኑም እዚህም ላይ በይነ-ቴክስታዊነት ምንድን ነው? የሚለውን በይነን እና መልክ ሰጥተን ማለፍ ይኖርብናል፡፡ የበይነ-ቴክስታዊነት አስተሳሰብ በቀደመው ዘመን የሥራዎችን መመሳሰል፤ መወራረስን ለማጥናት በግልጋሎት ላይ የዋለ ነበር (Bauman 2004: 1)፡፡ ሆኖም ግን በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የቃላዊ ትውፊትና ክንዋኔ እንዲሁም የቋንቋ ባህል ለውጥ በፈጠሩበት ወቅት በተረኮችና ተረኮች ማሃል ያለ ዝምድናንና የመወራረስን /intertextualization/ እሳቤን ማየት እንደተጀመረ መረጃዎች ያመለክታሉ /ዝኒ ከማሁ/፡፡

ከዚህ በኋላ በ18ኛው መ.ክ.ዘ. የቀድሞዎቹ ቃላዊ ጥበቦች ዘመንን አልፌው በነበረው ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ትኩስ ጉዳዮች ህያው መሆናቸው አሁንም ነሻጭ ዛሬም ምሉዕ ሆነው መደመጣቸው በትክክል ምክንያቱን ለማጥናት እንዲነሳሱ አድርጓቸዋል። (ዝኒ ከማሁ)። ይህንንም ጥናት እያንዳንዱ ታሪክ ከቀዳሚ ተቀራራቢ ቅጂዎች /version/፣ እንዲሁም ከሌሎች ታሪኮች ጋር /variant/ ጋር በማተያየት በመመርመር መሰረታዊ የቴክስት ህልውነት መሠረቱ የበይነ-ቴክስታዊ ግንኙነት ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደረሱ። ይህን እንበል እንጂ በንድፌ ሀሳብ ደረጃ የድህረ ዘመናዊነት እንቅስቃሴ ወደዚህ መዳረሻ ቢያመጣውም በይነ-ቴክስታዊነት በተገቢው መንገድ አሁን ባለው እሳቤ መጠን ቃሉን የፌጠረችው እና በቃሉ የተገለገለችው ፌረንሳይቷ ሀያሲ ጁሊያ ክርስቲቫ ነበረች። የርሷም መነሻ የ“Dialogism” ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኙ የBakhtin ሀሳብ ነበር (Allen 2000፡ 21፣ Childs 2006፡121) ።

በይነ-ቴክስታዊነትን በተመለከተ በተመራማሪዎች መኃል ያሉት ጉልህ መስማማቶች የቴክስት /texts/ ዝምድና ወይም ግንኙነት መሆኑ ላይ ነው። በምልክቶችና በትርጉማቸው፣ የቃላዊና ጽሑፋዊ ቴክስቶች ይዘት በሌሎች ቴክስቶች ውስጥ ያለውን ትርጉምና ቅጥ እንዲሁም ሌሎች ቴክስቶች በግልባጩ በቃላዊና ጽሑፋዊ እንዲሁም “ቴክስት” በሚባሉ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ የምናይበት መንገድ ነው። ክሪስቲቫ በአሁኑ ወቅት በይነ-ቴክስታዊነትን በብዛት ከምንጭ ጥናት ጋር ተያይዞ እየተነሳ መሆኑን በማውሳት ሆኖም በቴክስት ውስጥ የሚታየው መወራረስ ወይም ግንኙነት ወይም በቋንቋም ሆነ በተረክ ውስጥ የሚከሰተው በይነ-ቴክስታዊነት የቅንብር ለውጥና ቅመራም ጭምር መሆኑን ታስረግጣለች። ለዚህም ከላይ ካነሳችው የምንጭ ጥናት ከሚለው እሳቤ ስመለየት በአማራጭነት “transposition” የሚል መጠሪያን ትጠቀማለች (Kristeva, 1984: 60)።

የቋንቋ መዋቅራውያን በይነ-ቴክስታዊነት የምልክቶች የእርስ በርስ የጠበቀ ግንኙነትና እነዚህ ምልክቶች የሚፈጥሩት ትርጉም፤ እነዚህ ምልክቶች ደግሞ በሌላ መንገድ ቢገናኙ ደግሞ የሚፈጥሩት አዲስ ትርጉም እና አስፈላጊነት ማለት ነው ሲሉ ያብራራሉ። በይነ-ቴክስታዊነት የሚለው አጠራር የተሰጠው በሁሉም እንደቴክስት በሚቆጠሩ ነጥቦች ላይ ሲሆን እነዚህም ቃላዊ፤ ዕይታዊ፤ ጽሑፋዊ እንዲሁም ሐሣባዊ ስሆኑ ሁሉ በውስጣቸው የሌሎች ቴክስቶች የእርስ በእርስ ግንኙነት ኖሯቸው አንዱ ለአንዱ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦና ድርሻ ሲኖራቸው ይህን ግንኙነት በይነ-ቴክስታዊ ብለን ልንጠራቸው እንደምንችል ያብራራሉ (Childs 2006፡121)።

ይሔንንም መሰረት በማድረግ የትኛውም ቴክስት የተፈጠረው ከሌሎች ቴክስቶች ውህድና ህብር ነው በማለት ክሪስቲቫ በይነ-ቴክስታዊነትን "Mosaic of quotations" የሚለውን የባርቴዝን አባባል ታጸናለች (Moi, 1986፡ 36-37፣Becker-Leckrone 2005፡ 93፣ Allen 2000፡ 39)፡፡ በአንድ ሞዛይክ ላይ የተለያዩ ቅርጽና ቀለም እንዲሁም ልስላሴ ያላቸው መስታወቶች ተገጣጥመው የተዋበ ሥዕል እንደሚሰጡን ሁሉ በእያንዳንዱ ቴክስት ውስጥም የተለያዩ ሀሳቦች፤ እምነቶች፤ ቃላቶች፤ ምልክቶች፤ ቅርጾች፤ ታሪኮች ወዘተ. . .ተካተውበት ነው የሚቀርበው የሚሠራው ፡፡

እንደ ክርስቲቫ ሁሉ ይሔን ሀሳብ የሚያቀነቅኑት ቴክስት፡- በይነ-ቴክስታዊነት ምልክቶች ህብር ሰርተው ባህሉ ሥርዐቱ የሚፈቅደውን ትርጉም የሚሰጡ ማህበረሰቡ የሚስማማባቸው ኮዶች እና አመለካከቶች ናቸው ሲሉ ይገልጹታል (Abrams 1999፡ 317)፡፡ ጠለቅ ብለን ስንመለከተው የዚህ ሐሳብ አራማጆች የቴክስትን አህድነት፣ ወጥነት (originality) አስተሳሰብ ወደጎን በመግፋት የፈጠራ ባለቤትነትንና የአንድን ጉዳይ የበላይነት በቴክስት ውስጥ አይቀበሉም፡፡ አንዳንዴም ጉዳዩን እስከጥግ ድረስ በመውሰድ አዲስ የምንለው ምንጭ የለም ይልቁንም ተሀድሷዊ ምንጭ (re-creation) ነው ያለው ወደሚል ጠንካራ አቅጣጫ ይወስዱታል፡፡ እንደማስረጃም ቢያንስ አሁን እንደ አዲስ ሀሣብ እንደአዲስ የፈጠራ ሥራ የምንቆጥረው ነገር አስቀድሞ በቋንቋው ሥርዐት ውስጥ ተቀምጧል በማለት ያብራራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቀድሞ የተፈጠሩትን ቴክስቶች እኬስትሬት ማድረግ (ማዛነቅ) እንጂ ቴክስቶችን አንፈጥርም ሲሉ ያክሉበታል (Kristeva: 1984፡ 60, Allen 2000፡ 35, Childs 2006፡ 122, Habib 2005: 178) ፡፡ ቀጣዩ ሐሳብም ይሔንኑ ያነሳነውን ጭብጥ የሚያጠናክርልን ነው፡፡

> [. . .] every text as constituting an *intertext* in a succession of texts already written or yet to be written. A version of this idea has recently begun to be incorporated into the linguistic analysis of texts. The general idea is that a text does not exist in isolation and cannot be fully appreciated in isolation; instead, a full understanding of its origins, purposes and form may depend in important ways on knowledge of other texts. A sonnet may depend upon the reader's familiarity with the sonnet-writing tradition; a newspaper story may depend upon previous news stories; a political speech may invoke earlier speeches and political statements; even a recipe may depend upon the reader's acquaintance with other recipes. (Trask 1999፡ 87)

በይነ-ቴክስታዊነት የመቅደምና የመከተል ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ በአንድ ቴክስት ላይ የበርካቶች ሀሳብ እና ቀመር ግንኙነት ማለትንም ጨምሮ ነው፡፡ ቀመሩም፤ ሀሳቡም

ለየብቻቸው ቴክስት ሊባሉ ቢችሉም ህብር በመፍጠር ወይም "intertext" በማድረግ አዲስ የመሰለን ቴክስት ይፈጥሩታልና (Kristeva, 1984: 60)። ጆናታን ኩለር "አንድን የሥነ-ጽሑፍ ሥራ ስታነብ የሥነ-ልሳን ክስተትን እያነበብክ መሆኑ ነው" (2000፡ 33) በማለት በቀላሉ በቴክስቶች መሀል ያለን ግንኙነት ያሳየናል። በመጠኑ ሰፋ አድርገን ይሔንኑ ምሳሌ ብንመለከተው ሰዋሰዋዊው ሥርዐት ስነ ልሳንን እንደ ጠራው ሁሉ የያዘው ሀሳብ ደግሞ ርዕዮትን ፍልስፍናን ወዘተ እንዲሁም የአተራረክ መንገድና ቴክኒኩ ደግሞ አስቀድሞ የተፃፉ የሥነ-ጽሑፍ መፃህፍትን ማገናኘቱ ዕውን ነው። በመሆኑም በቀላሉ አንድ ቴክስት ነው ብለን የምናስበው ሥነ-ጽሑፍን እንኳን ለቁጥር የታከቱ ዲስፕሊኖች ህብር ሰርተው እንዳቆሙት /በይነ-ዲስፕሊናዊ እንደሆነ/ ልብ እንላለን።

በርግጥም በይነ-ቴክስታዊነት ከላይ ያለውን አይነት ትርጉም ባህርይውን እንደጠበቀ በርካታ የጥናት መስኮች መሠረታዊ መርሁን ሳይለቁ እንደጥናቱ አቅጣጫ ቃሉን ይጠቀሙበታል። በየዘመኑም የተነሱ አስተምህሮት እና እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት ያጣ ጉዳይ አይደለም።

> The concept of intertextuality is characterised by being interdisciplinary, influenced, for example, by linguistics, psychoanalysis and philosophy. "Intertextuality" is employed in structuralism, poststructuralism, deconstruction and Marxism, as well as cultural, postcolonial and gender studies. (Joachimsen 2011: 220)

የበይነ-ቴክስታዊነት የመፈጠሪያ /የመከሠቻ/ መንገዶችን በርካቶች በየራሳቸው መንገድ አስቀምጠዋቸው እናገኛለን። እነዚህ መንገዶችንም በግልጽ ወይም በስውር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሲሉ ይገልጿቸዋል። ይህም ማለት በቴክስቱ ውስጥ የሌላው ቴክስት ቅርፁን ሳይለውጥ ተካቶ ማግኘታችንን አሊያ አዲስ ካልነው ቴክስት ጋር ተዋህዶ ኢቀጥታዊ በሆነ መንገድ ማግኘታችንን ለማስረዳት ነው። ከዚህም በተጨማሪ በይነ-ቴክስታዊነት ሲከስት የተለያዩ የባህል ቅርጾች ውስጥ በተለያየ ምክንያት እና ሂደት ሊሆን ይችላል። ወደራስ ባህልና ቋንቋ በመመለስ፣ በመተርጎም፣ ስልትን በመውሰድ፣ በማስመሰል በመገልበጥ እና በሌሎች የመደጋገፊያ መንገዶች ሊፈጠር ይችላል (Quinn 2006፡ 218-219)። በምክንያትነትም ቀዳሚው ቴክስት በህዝብ ዘንድ የበለጠ ተቀባይ በመሆኑ እና ተደጋግሞ የቀረበ የተሰማ በመሆኑ አሊያም አማራጭ የሌለው የቴክስቱ መፈጠሪያ መንገድ ከሆነ ነባሩን ቴክስት በአዲሱ ቴክስት ውስጥ እናገኘዋለን። በምን አይነት መንገድ እንደገባ የመረጃ ወይም የማወቂያ መንገዶችም በመጥቀስ እና በማስታከክ ወይም በጥቁምታ መንገድ ሊሆን ይችላል።

There are two types of intertextuality: citation and presupposition. Citation includes not only direct quotation and allusion, but also literary conventions, imitation, parody, and unconscious sources. Presupposition involves assumptions regarding the reader, the situation being referred to, and its context. (ዝኒ ከማሁ)

ይሔ ነባሩን ጠቅሶ ወደ ጽሑፉ ማካተት /citation/ ደራሲው ንቁ ሆኖ በይሁንኝ በይነ-ቴክስታዊነትን መፍጠሩን መገመት አይከብድም። ይልቁንም አስቀድሞ ባነሳው ጉዳይ ላይ የተባለ የተነገረ መሆኑን በማስረገጥ ወይም በመጠቆም ነው የርሱን አዲሱን ማስኬድ የሚፈልገው።

አስቀድመን ስሟን በጉልህ ያነሳናት ጁሊያ ክሪስቲቫ ሁለት አይነት የበይነ-ቴክስታዊነት መንገዶችን (አይነቶችን) አሳይታለች። እነዚህን ሁለቱ የበይነ-ቴክታዊነት አይነቶች Horizontal Axis Intertextuality /አግድሞሽ/ እና vertical Axis Intertextuality /ቁማዊ/ በማለት ትጠራቸዋለች (Childs 2006፡ 12፣ Kristeva፡ 2005፡ 123)። ክርስቴቫ ዲያሎግን የሚፈጥሩ ሶስቱቹ አምዶች የጽሑፉ ጉዳይ (subject)፣ ተደራሹ (addressee) እና ከቴክስቱ ውጭ ያሉ ነገሮች ናቸው በማለት የባርቴዝን ዲያሎጊዝም ሐሳብ ስታጠናክር በአግድሞሽ /horizontal axis/ የጽሑፉ ጉዳይ እና ተደራሹ (subject-addressee) እና በቁማዊ /vertical axis/ ደግሞ ቴክስቱ እና አውዱን (text-context) ይካተታሉ ስትል ታስረዳለች (Moi 1986፡ 37)።

### አግድሞሻዊ በይነ-ቴክስታዊነት /Horizontal Axis Intertextuality/

ይህ የበይነ-ቴክስታዊነት ዓይነት ትኩረቱን የሚያደርገው በቴክስቱ ሀሳብ እና ቴክስቱን በሚያየው በእድምተኛ ወይም በአንባቢው መሀል ያለ ነው። ይህ ማለት አንባቢው ወይም ተመልካቹ ቴክስቱን ባነበበት ወይም ባየበት መንገድ ከራሱ የቀድሞ ግንዛቤና እምነት እንዲሁም እውቀት አንጻር የሚፈጠር የትርጉም በይነ-ቴክስታዊነት አይነት ነው። በሌላ አባባል አንድን ቴክስት ተቀብለን እንደገና ወደሌላ አይነት ቴክስት የመለወጥን ሂደት እንደማለት ነው። በዚህም አንድን የጥበብ ሥራ የደራሲው ሐሳብ እና እምነት (ነጠላ ትርጉምና ጭብጥ) ብቻ ሳይሆን ከአንድ በላይ የሆነ ትርጓሜም ያለው ጭምር መሆኑን እንረዳለን።

**ቁማዊ በይነ-ቴክስታዊነት /Vertical Axis Intertextuality/**

የዚህኛው የተበባዊነት አይነት ትኩረቱን የሚያደርገው በሁለት የተለያዩ በየራሳቸው ቴክስት በምንላቸው መሀል ያለው ዝምድናና ተራክቦ ላይ ነው። ይኸንንም አቅጣጫ አውዱ ቴክስቱ ላይ የፈጠረውን ተጽዕኖ የምናይበት ሲሆን በአንዱ ቴክስትና በሌላው ቴክስት መሀል የተሠሩበት ቀመር፣ ቅጥ፣ ቅንብር፣ ቅርጽ ወዘተ መመሳሰልን አለያም አንዱ በአንዱ ውስጥ ያለው መደጋገፍና መቆም እንዲሁም ውህደትን የምናይበት መንገድ ነው።

የተለያዩ ሙያዎች ወይም የሙያ ዘርፎች በይነ-ቴክስታዊነት የሚለውን እሳቤ በተለያየ አጠራር ሊጠሩት ይችላሉ። መሠረታዊ ነጥብ ግን Vertical በሆነው ወይም Horizontal በሆነው አቅጣጫ ቴክስቶች ያላቸውን አንድነት ማሳየታቸው ነው ቁም ነገሩ።

በመሆኑም ዜና መዋዕላቱን ለመመልከት በሁለቱም የበይነ-ቴክስታዊነት መፈጠሪያ መንገዶች በኩል ለመመልከትና ለመመርመር ይሞከራል።

# ምዕራፍ ሦስት

## ዜና መዋዕል

ኢትዮጵያ በረዥም ዘመን ታሪኳ ካሏት ሀብቶች መካከል ሥነ-ጽሑፋዊ ሀብቶቿ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ጽሑፋዊ ሀብቶቿን በተለያየ ዘውግ ልንከፍላቸው የምንችል ሲሆን ዜና መዋዕል ከነዚህ ውስጥ አንዱ ነው። ዜና መዋዕል የኢትዮጵያን ቀደምት ታሪክ ዘግበው የያዙ ሰነዶች እንደሆኑ "The origion of Ethiopian historiography can be traced back, first and foremost, of the chronicle." (2012: 30) ሲል ይገልጻል። ዜና መዋዕላት በኢትዮጵያ ውስጥ የነገሡ ነገሥታትን ታሪክ የያዙ ጽሑፋዊ ሰነዶች ናቸው። ዜና መዋዕልን ማዘጋጀት መቼ ተጀመረ ለሚለው ቁርጥ ያለ መልስ መስጠት አይቻልም የሚሉ ምሑራን ያሉ ሲሆን እስካሁን ግን ካሉት ዜና መዋዕላት ውስጥ በዘመን ቀዳሚነት ያለው "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ነው። ከዐምደ ጽዮን በፊት ሌላ ዜና መዋዕል ሊኖር ይችል ይሆናል ባይዎቹ ቀደምቱ ምናልባት በዘመን ብዛት ጠፍተው ወይም በተለያየ ምክንያት ሳናገኛቸው ቀርተን ሲሆን ይችላል የሚል መላምት ይሰጣሉ (አምባቸው 1999፡ ገጽ የሌለው)።

በሌላ በኩል በርካቶች (ፓንክረስት 1967፣ ሃንቲንግፎርድ 1965 እና ሌሎች) በመካከለኛው ዘመን ከመጡ ነገሥታት መካከል የመጀመሪያው ዜና መዋዕል አድርገው የሚያነሱት የዐምደ ጽዮንን ዜና መዋዕል ነው። የዜና መዋዕል ጸሐፍትን በቤተመንግሥቱ ውስጥ ቀጥሮ እንደ ሥልጣንም ተቆጥሮ የተደራጀው በዚሁ በዐፄ ዐምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው (አምባቸው1999፡ ገጽ የሌለው፣ ባርትኒስኪ 2003፡ 56)። ጸሐፊ ትዕዛዝ የንጉሡን ታሪክ ከመመዝገብና ከመዘገብ በተጨማሪ በርካታ የጽሕፈት ሥራዎችን የሚሠራ እንደነበር ሪቻርድ ፓንክረስት ይገልጻል (1967፡ xii)። በሌላ መልኩም የታሪክ ነገሥት ጸሐፍት ሁለት አይነቶች ናቸው፤ አንደኛው ከላይ እንዳነሳነው ቀለባቸውን ከነገሥታቱ የሚያገኙ "የቤተ መንግሥት ሊቃውንት" ሲሆኑ ሁለተኛው ግን በየገዳማቱ የሚኖሩ "መነኮሳት" ናቸው ሲል ገብረሀይወት ባይከዳኝ ይገልጻል (ገብረ ሕይወት 2002፡ 3)።

ጸሐፊው ዜና መዋዕሉን በሚጽፍበት ወቅት የነገሥታቱ የቅርብ ክትትልና ይሁንታ እንዲኖረው የሚደረግ ሲሆን በአብዛኛው ጊዜም ታሪኩን ከሚጽፍለት ንጉሥ አንጻር ቆሞ ይተርካል። ይህን እንበል እንጂ በአብዛኛው ጊዜ የዜና መዋዕል ጸሐፊዎች ታሪኩን አግዝፈውና አጋነው ከመጻፍ ውጪ ከንጉሡ በተቃራኒ የሚቆሙ ባለታሪኮችን ሐቅ በውሸት አይጽፉም። ባይሆን ይዘሉት ካልሆነ ድላቸውን በሽንፈት ጽናታቸውን በድክመት ለውጠው አይዘግቡም (አምባቸው1999፡ ገጽ የሌለው)። ይሔን ሐሳብ ግን ገብረሀይወት

የሚስማማበት አይመስልም። "ያገራችን የታሪክ ጸሐፊዎች ግን በነዚህ ነገሮች ላይ ኃጢአት ይሠራሉ። በትልቁ ነገር ፊንታ ትኒሹን ይመለከታሉ። ለእውነት መፍረድንም ትተው በአድልዎ ልባቸውን ያጠባሉ" (ገብረ ሕይወት 2002፡ 3) ሲል ይገልጸዋል።

ዜና መዋዕላት በሁለት አይነት መንገድ ሊጻፉ ይችላሉ። የመጀመሪያው መንገድ ከላይ በተገለጸው መሰረት ባለታሪኩ በቤተመንግሥቱ ውስጥ በሕይወት እያለ ለጸሐፊው ደሞዝ ቆርጦለት ቀለብ ሰፍሮለት እየተከታተለ የሚያስጽፈው ሲሆን፤ ለዚህም "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ማስረጃ መሆን ይችላል። ሁለተኛው ደግሞ ባለታሪኩ ካለፈ ከሞተ በኋላ ተከታዩ ንጉሥ ወይም ሌላ ሰው መረጃ ሰብስቦ የነበረበትን አገናዝቦ የሟቹን ንጉሥ ታሪክ የሚያስጽፍበት ሂደት ነው። ለዚህኛው ደግሞ የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብን ዜና መዋዕል መመልከት ይቻላል (ፓንክረስት 1967፡ xii- xiv)።

ባሕሩ የዜና መዋዕል ጸሐፍቱ የሚተርኩት ታሪክ በሰዎች መደረጉን ከመግለጽ ይልቅ በፈጣሪ ወይም በሰይጣን እንደተፈጸመ የመተረክ ዝንባሌ እንዳላቸው ያስረዳል። በሌላ አኳያ ግን በገለጻቸው ላይ በዘመነ ንግስናው ወቅት ያሉትን ሁናቴዎችን እና ክስተቶችን በዝርዝር የመተረክ ብቃት እንዳላቸው ያብራራል (ባሕሩ 2012፡ 30-31)። ከአተራረክም አንጻር የዜና መዋዕላት አተራረክ "ገድላዊ ነው" ብለው የሚገልጹ በርካታ ምሁራን አሉ። ከነዚህ መሀል ዘሪሁን አስፋውንና አምሳሉ አክሊሉን ማንሳት ይቻላል።

አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ዜና መዋዕላት በግዕዝ ቋንቋ የተጻፉ ናቸው። ዜና መዋዕሎችን በአማርኛ መጻፍ የተጀመረው ከዐፄ ቴድሮስ ዳግማዊ በኋላ እንደሆነ ሰነዶች ያረጋግጣሉ። ሆኖም በአሁኑ ወቅት ዜና መዋዕሎች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በተለያየ ምክንያት ወደተለያዩ ቋንቋዎች እየተተረጎሙ ይገኛሉ። በዚህ ጥናት ላይ የምንመረምረው "የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል"ን ጨምሮ ሌሎችም የተለያየ ቅጂዎች በግዕዝና በአማርኛ ከመኖራቸው በተጨማሪ በላቲን፣ በፈረንሳይኛ፣ በጣሊያንኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በጀርመን፣ በፖርቱጊዝ እና በሩሲያንኛ ተተርጉሟል (ፓንክረስት 1967፡ xvi)።

ለዚህ ጥናት ከተጠቀምኩባቸው ዜና መዋዕላት መሐል የዐፄ ዐምደ ጽዮንን ከግዕዝ ወደ አማርኛ የመለሰው ይኩኑ አምላክ የተባለ ጸሐፊ ሲሆን፣ የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብን ዜና መዋዕል የተረጎመው ሰው ደግሞ እንባቆም ቃለወልድ ይባላል። የሁለቱንም ትርጉም ዜና መዋዕሎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲቱት ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነው ያገኘኋቸው። የመጀመሪያው "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" የተተየበና የተርጓሚው ስም በየገጹ በእጅ ጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኝበት ነው። በአንጻሩ "የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ከ"ዐፄ በእደ ማርያም ታሪክ" ጋር አንድ ላይ ሙሉ በሙሉ

በእጅ ጽሑፍ ተጽፎ ከተተየበው "የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ጋር በአንድነት የተጠረዘ ነው። የተርጓሚውም ስም ታሪኩ ሲጀምር ከርዕሱ ስር ከመስፈሩ በተጨማሪ በዛው የእጅ ጽሑፍ "በ፵፱ ገጾች በአ/ ዕንባቆም ቃለወልድ ተተርጉሞ የቀረበ የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብና የበዕደ ማርያም የታሪክ መጽሐፍ" የሚል ጽሑፍ በመጨረሻው ገጽ ላይ ሰፍሮበታል።

## ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በንድፈ ሐሳብ ክፍል ውስጥ ያነሳናቸው ጽንሰ ሐሳባዊ ጉዳዮች እንደምን ተደርገው በዜና መዋዕላቱ ውስጥ ተገልጠዋል የሚለውን እንመለከታለን። በንድፈ ሐሳብ ዳሰሳ ክፍል ውስጥ ያነሳኋቸውን አተኩሮ እና በይነ-ቴክስታዊነትን በሁለት ዋና ክፍሎች በመለየት እተነትናለሁ። በትንተናዬ ውስጥም በሁለቱ አበይት የትንተና ማዕከሎች ስር ሊነሱ ይገባቸዋል ብዬ ያሰብኳቸውን ንዑስ ርዕስ ነገሮችን በአስረጂ በማስደገፍ አብራራለሁ። የዚህ ምርምር ዐቢይ አላማው የአተራረክ ቴክኒክን መተንተን በመሆኑ በተቻለ መጠን አስረጂዎቹ ተረካዊ ስዕሉን ሊያሳዩ እንዲችሉ ተጥሯል።

### 3.ሀ. "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል"

### 3.1 አተኩሮ በዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ፡-

በንድፈ ሐሳብ ዳሰሳ ውስጥ ለማሳየት እንደሞከርኩት አተኩሮ /focalization/ን ስንመረምር የተራኪውን አኳያ ማየት ይገባናል። የተራኪው አኳያንም በሶስት ክፍሎች ከፍለን ልንመለከተው እችላለን። በዚህም መሰረት አኳያን፡- በአንጻር (ተራኪው መደብ እና የዕይታ አቅጣጫ) ፣ በርዕዮተ ዓለም እና በአላማ ከፍለን እናየዋለን። በነዚህም መንደርደሪያ ዜና መዋዕላቱ የሚተርኩበትን ብልሀትና በጎንዮሽም የመጻፋቸውን ግብ እንመለከታለን።

በትንታኔው ውስጥ አጠቃላይ ስዕሉን ማየት እንዲያስችል በየዜና መዋዕላቱ ውስጥ ያሉትን መልኮች በቅደም ተከተል በያነሳሁት ጭብጥ ስር እየተነተንኩና እያብራራሁ እሄዳለሁ።

#### 3.1.1 አንጻር (ተራኪው፣ መደብ እና የዕይታ አቅጣጫ) ፡-

በ "ዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ውስጥ ተራኪው ከየት አንጻር ሆኖ ነው የሚመለከተው ብለን ስንጠይቅ በከፍተኛ ጥንቃቄ ልናጤናቸው የሚገቡ ነጥቦችን እናገኛለን። ምክንያቱም አጠቃላይ ዜና መዋዕሉ ጀምሮ እስኪጨርስ ድረስ ተራኪው የት ነው ያለው? የሚለውን ማየት ይኖርብናልና። በመሆኑም አስቀድመን ተራኪው ማን ነው?

ታሪኩንስ ከየትኛው የመመልከቻ አቅጣጫ ሆኖ ነው የሚተርክልን? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች በማንሳት የተራኪውን አንጻር የሚያመላክቱ የተረኩ ክፍሎችን እየተመለከትን አጠቃላይ ዜና መዋዕሉ በየትኛው የመተረኪያ አንጻር ነው የተተረከው ወደሚለው መዳረሻችን በአስረጂዎች እያረጋገጥን እናምራ።

በ"ዐጼ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ላይ ተራኪው ራሱን በተለያየ መልኩ ሲገልጽ እንመለከታለን። ይህም በነጠላ ቁጥር ብቻ ሳይሆን በብዙ ቁጥርም ጭምር ነው ራሱን የሚገልጸው። ይሔም ምናልባት ተራኪው ከአንድ በላይ ይሆን? የሚል ጥያቄን እንድናነሳ ሊጋብዘን ይችላል። ዜና መዋዕሉ ገና አስቀድሞ ተረኩን ሲጀምር ይሔው ነጥብ ተደጋግሞ ይታያል።

> ለኢትዮጵያ በነገሠ የመንግሥቱም ስም ገብረ መስቀል በተባለ፣ በዐምደ ጽዮን ዕጀች፣ በአስራ ስምንተኛው ዓመተ መንግሥቱ በ517 (በሺሕ ሦስት መቶ አሥራ አምስት) ዓመተ ምሕረት እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ኃይልንና ድንቅ ሥራን ማቸነፍንም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አጋዥነት እንጽፋለን።
>
> ወይም ይህን መጽሐፍ በሺሕ ሦስት መቶ ዐሥራ አምስት ዓመተ ምሕረት እንጽፋለን። የሚረዳ አብንና የሚያረጋጋ ወልድን የሚመራ መንፈስ ቅዱስንም አምነን። ከልዩ ሦስት (ሦስትነት ከጸናችላቸው አካላት) አጋዥነትን እየሻን። ጥበብን ያጣት ሰው ቢኖር በለጋስነት ለሁሉ ከሚሰጥ ከማይገዳደርም ከሰጭ እግዚአብሔር ዘንድ ይለምን፣ ብሎ ያዕቆብ ሐዋርያ እንደተናገረ። እኛም ከአብና ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስም ዘንድ አጋዥነትን እንሻ ። (ገጽ 1 ፣አጽንዖት ከራሴ)

ከላይ አጽንዖት የተደረገባቸው ቃላት በግርድፉ ሲያዩዋቸው ተራኪው ከአንድ በላይ እንደሆነ ሊያመላክት ይችላል። ምክንያቱም "እንጽፋለን፣ አምነን፣ እየሻን፣ እንሻ" የሚሉት ቃላት የነጠላ ቁጥር ጠቋሚ አይደሉምና። ይሔው የአገላለጽ ሁናቴ በዚህ ላይ ብቻ የሚቆም አይደለም። ይልቁንም ተረኩን በሚያቀርብባቸው ጊዜያትም ይስተዋላል።

> እኛ ግን ሰምተናል ከቅዱሳት መጻሕፍትም (ተመልክተን) የተነሳ አውቀናል፣ አወን ማለትንና የለም ማለትን ያልኾነ ማለት እውነትና ሐሰት ያልተቀላቀለበትን የታመነ ነገርን እንናገራለን የእስላሞች መንግሥትም ጥቂት እንደኾነ እንናገራለን። ያውም በጊዜው ጊዜ የሚሻር የሚጠፋ ሰባት መቶ ዓመት እንደኾነ እንናገራለን ። (ገጽ 6 ፣አጽንዖት ከራሴ)

እዚህም ላይ ከላይ እንደተመለከትነው ተራኪው "እኔ" በሚል መደብ ሳይሆን ራሱን አብዝቶ "እኛ" በሚል አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር ሲገልጥ ነው የምናስተውለው፡፡ ይሔው አይነት አገላለጽ እያሰለሰ ብቅ የሚል ሲሆን በዜና መዋዕሉ በገጽ 32፣33 ላይ እንዲሁ ይታያል፡፡ ሆኖም ይሄንን በማየት ብቻ የተራኪያችን ማንነት ከአንድ በላይ ነው ብለን ልናምን አንችልም፡፡ ምክንያቱም በሌላም በኩል ተራኪው ራሱን በነጠላ አንቀጽ ሲጠራ እናገኘዋለንና፡፡ ይሔም በግልጽ የተራኪነትን ሚና ሲወስድ የሚያሳየን ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆኑ እማኞችን ደግሞ እንመልከት፡፡

> በመዓልትና በሌሊት ዕረፍት በሌላቸው በንጉሥና በሠራዊቱ ላይ የተደረገውን ፀብ (ጦርነት) እነግራችኁ ዘንድ አሁንም ስሙ፡፡ (ገጽ19፣ አጽንዖት ከራሴ)
>
> የተወደድኽ ሰው ሆይ የምነግርኽን ነገር ዳግመኛ ስማ፡፡ ነገሬንም ከንቱ አታስመስል ለኔማ ዛፎችም ተራሮችም ኮረብቶችም ከእርሳቸው ጋራ የሚሮጹ (ለኔ) መሰለኝ፡፡ ደመናት በሰማይ ስፍሐት (ኅዋ) በሮጹ ጊዜ ጨረቃና ከዋክብት የሚሮፁ እንዲመስሉ፡፡ (ገጽ30፣ አጽንዖት ከራሴ)
>
> ቃሉን ግን የሚሰማው ማንም ማን አልነበረም፡፡ ጉላቸው ሽሹ እንጅ፡፡ ጉላቸው ሽሹ ብልም በፍርሃት አይምሰላችኁ፣ አታድንቁም፡፡
>
> ግን እንዲህ እላለሁ የሸዋና የዳሞት የጎዣምና የትግሬ ሠራዊት የአምሐራና የብጉና ሠራዊትም የኢትዮጵያ ሠራዊት ጉላቸውም በሙሉ በእግዚአብሔር ኃይል ባይሆን ካልሆነ በፊታቸው መቆምን ባልቻሉም ነበረ (እልኽ)፡፡ (ገጽ 32፣ አጽንዖት ከራሴ)
>
> ዕጁም ከመግደል ብዛት የተነሳ በሰው ደም ከጦሩ ጋር እስኪጣበቅ ድረስ ገደላቸው፡፡ ዕጁንም በኃይል ፈቱ (አስለቀቁ)፡፡ ጦርንም ከዕጁ ወሰዱ፡፡ በዚያች ቀን የተደረገውን፣ በቀደሙ የኢትዮጵያ ነገሥትም ዘንድ ያልኾነውን ፀብ (ጦር) ዳግሞ እነግራቸሁ ዘንድ ስሙኝ ፡፡ (ገጽ 33 ፣አጽንዖት ከራሴ)

እንግዲህ ከላይ ባየናው ምሳሌዎች መጀመሪያ ተራኪው ማን ነው? ስንት ነው? የሚለውን ለይተን ለመመልከት እንሞክር፡፡ ይሔንንም በመንተራስ የተራኪውን አንጻር ለመመርመር እንሞክር፡፡ ከላይ በመጀመሪያ የተመለከትናቸውን አስረጂዎችን በመንተራስ ተራኪው ከአንድ በላይ መስሎ ቢሰማንም ታሪኩን ተከትለንና አጠቃላይ የታሪኩን ፍሰት ተንተርሰን የምንደርስበት ድምዳሜ ተራኪው አንድ መሆኑን ይልቁንም በወል ቁጥር ራሱን የመግለጽ የአተራረክ መንገድን ወይም ፈሊጥ እያቀላቀለ የሚሔድ መሆኑን ልብ እንላለን፡፡ የዚህ አይነት የወል ተራኪ መሰል ትረካዎች በቀደምት ሃይማኖታዊ መጻሕፍት

ውስጥ የተለመደ ነው። ይህንንም ዝቅ ብለን በምንመለከታቸው ማስረጃዎች ጸሐፊው ለእነዚሁ መጻሕፍት በእጅጉ የተጋለጠ መሆኑን ስንመለከት ይሔን የአተራረክ ቴክኒክ ወደራሱ ቴክስት ውስጥ አልምዶታል ማለት ያስችለናል። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ የተመለከትናቸው የወልነት አገላለጾች የተራኪውን የእምነት እና የታሪክ ተጋሪዎችን የሚወክል የጋራ ድምጽ /stand/ መገለጫ ጭምር መሆናቸውን መረዳት ተገቢ ነው።

በሌላ አንጻር ተራኪው ለታሪኩ ያለውን ቅርበት፣ የታሪኩን ቅደም ተከተልና ፍሰት እንዲሁም የአተራረክ ብልሐቱን ስንመረምር በአንድ ተራኪ መተረኩን ልብ እንላለን። ይህንንም ለማስረዳት ተራኪው በአጠቃላይ የትረካ ሂደቱ ላይ በአንደኛ መደብ በጥልቀት እና በዝርዝር ነገሮችን እና መረጃዎችን ማስቀመጥ መቻሉ ለታሪኩ ያለውን ቅርበት ማስረዳት የሚችል ነው። በመጨረሻም ተራኪው በዚህ እና ከዚህ በታች ልንመረምራቸው በምንሞክራቸው መሰረታዊ ነጥቦች ላይ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከመጨረሻው የትርክት መቋጫ ድረስ በተመሳሳይ ቃና፣ ስልት፣ ፍሰት እና ቋንቋ መዝለቁ ተራኪው አንድ መሆኑን ያመላክታል።

ይሄንን ይዘን ትረካው በየትኛው አንጻር ነው የተተረከው? ወይም ታሪኩን በማን አይን ነው የምናየው? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ይኖርብናል። በዐዔ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ውስጥ ይሔን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመመልከት ስንሞክር በርካታ አሻሚ ነጥቦችን እናገኛለን። ምናልባትም እነዚህ አሻሚ ነጥቦች የዜና መዋዕላት የአተራረክ ስልት ላይ ያለንን የአንጻር እይታችንን ቆም ብለን እንድንጠይቅ እድል ይሰጠናል።

በመጀመሪያ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ተረኩን የሚተርክልን ተራኪ ነጠላ ወይም አንድ ነው። ይህም ተራኪ ባየናቸው ምሳሌዎች እራሱን ሲገልጽ "እኔ" የሚል ግልነት ያለው አካል ነው። ይሔም ሲባል ሁሉን አወቅ ወይም በሁሉ ቦታ እና ጊዜ የሚገኝ አካል (እንደአምላክ ያለ) አይደለም ማለት ነው። በመሆኑም ተራኪያችን ውስንነት[7] አለበት ብለን እናምናለን። ይሔንን ተንተርሰን የመመልከቻ መጠኑን ለመገመት እንሞክራለን። ከላይ በንደፈ ሐሳብ ክፍል ባየነው መሰረትም የዜና መዋዕሉ ተራኪ አንደኛ መደብ ውስጣዊ አተኳሪ መሆኑን እንገነዘባለን ። ሆኖም ውስጣዊ አተኳሪ ተራኪ ካለው አቅም እና ችሎታ ተሻግሮ ተራኪው ባልነበረበት እና በሌለበት ቦታ እንደ አምላክ አከል ባህሪ ልብ ያሰላሰለውን ደም ያመላለሰውን ሁሉ ሲተርክ እናገኘዋለን። ጥቂት ማስረጃ በማቅረብ እንመልከት።

---

[7] ውስንነት አለበት ስል ከተነሳሁበት ጭብጥ አኳያ የእይታዊ እሳቤውን ተንተርሶ የሚመጣውን በጊዜና ስፈራ መወሰንን ታሳቢ አድርጌ ነው።

ታሪኩን ለመረዳት ያክል ተራኪው አብዛኛውን ጊዜ ራሱን አኑሮ የምናገኘው ከንጉሥ ዐምደ ጽዮን ቅርብ አኳያ ነው። በሌላ አባባል በታሪኩ ውስጥ የርሱ የተሳታፊነት ጎራ ከንጉሡ ባለሙዋሎች እንደ አንዱ ነው። ይህም ማለት ተራኪው ካለበት ጎራ በተቃራኒው ያለውን ኃይል ምክር እና ሐሳብ ሊያይ ሊሰማ እና ሊተርክ የሚያስችል ዕድል የለውም። ሆኖም ከታች በምናየው የተረክ ቅንጭብ ውስጥ የሚተርክልን ከርሱ የእይታ ማዕቀፍ ውጪ የሆኑ ሁለት አካላትን ንግግር እና ሀሳብ ጭምር ነው።

ዐመፅን የፈጸመ የሰብረዲን ወንድም (ግማለዲን) ንጉሥ ከመታሰር የፈታው፣ ስለ ወንድሙ ስለ ሰብረዲን ፈንታም በእስላሞች ምድር ላይ የሾመው ያነገሠውም ግማለዲን ወንጀልን አደረገ። ከእነዚያም ነገሥታትና መኳንንት ጋር በምክር ተባበረ። ወደ አዳል ንጉሥም ላከ (እንዲህ ሲል) ፍቅር አንድነት ላንተ ይገባል ለክብርኸም ሰላምታ ፍቅር ይገባል። ምክሬን ስማ፣ የምነግርኸንም ነገሬን አድምጽ። የክርስቲያን ንጉሥ መውጣትን (ሊወጣ) በማይችልበት በጸባብ መንገድ እነሆ መጣ። አንተም ከሑለት መንገዶች አንዱን ለራስኽ ምረጥ። ግብርንና እጅ መንሻን ልታወጣለት ትሻ እንደ ኾነ ወይም ይህ ሕሊና የለብኽ እንደ ኾነ (ከሑለቱ መንገዶች አንዱን ምረጥ)።

ዕጅ መንሻን ልታወጣለት ከሻኽ ግን ሚስትኽንና ልጆችኽን ያለኽንም ገንዘብ ኍሉ ሽጥ። ካንተ አስቀድመው የነበሩ አባቶችኽ ያላደረጉትን ይህን ካደረኽም ከዘርክና ከወገንኽ ዘር ባርነት አይወገድም።

የምታደርገውን ጥበብ እወቅ። ሰይፍ መዘው ቀስት ስበው ጋሻ መክተው ጦር ወርውረው የእንጨት ጦሮችን ስለው የብረት በትር ጎመድ ይዘው የሚጋደሉ ሠራዊትን ሰብስብ። እኔም ሰይፍና ቀስት ጋሻም ጦርም የእንጨት ጦሮችንም የእንጭትና የብረት በትርም ይገዬ ከሠራዊት ጋር እመጣለኍ። ሠራዊቱም በፈረስ መቀመጥን በእግር መሮጥን የለመዱ ሰዎች ናቸው። በ፩ መዓዝን በኍሉ እንክበብና በ1 ጊዜ እንፍጀው (እንጨርሰው)፣ ከሠራዊቱም አንዱን እናስቀር ብሎ (ወደ አዳል ንጉሥ ላከ)።

የአዳል ንጉሥም ይህን ነገር ሰምቶ ሠራዊትና ነገሥትንም መኳንንትንም የምድራቸው ሰዎችንም ሁሉ ሰበሰበ። እሊህንም ኍሉ ሲሰበስብ 4ወር ቆየ (ተቀመጠ)። የአዳል ንጉሥ ከእግዚአብሔር ብቻ በቀር እነሱን መቁጠር የሚችል ማንም ማን የሌላቸው ብዙዎች ሠራዊት ኍሉ ወደ እርሱ እንደተሰበሰቡ ባየ ጊዜ በልቡናው ታበየ። እግዚአብሔርንም ተገዳደረ። በሙሴ ላይ እንደ ታበየ፣ በሾተሌ

እገድላለኍ፣ በሥልጣኔም እገዛለሁ። ምርኮንም ለሰውነቴ አጸግባታለኍ እንዳለ እንደግብጽ ንጉሥ እንደ ፈርዖንና፣ በሕዝቅያስ ላይ እንደታበየ ከዕጄ የሚያድንኽ አምላክ አለን እንዳለ እንደ ሰናክሬም ታበየ (ተገዳደረ)

እንደዚሁም ያ ከሃዲ ወንጀለኛ፣ የሰይጣን ባልንጀራ፣ በክርስቶስ ላይ ታበየ። እንዲህም አለ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጥዋ ያለባትን የተራዳ ድንኳን ለራሴ መስገጃ አደርጋለኹ። በውስጥዋ ያለ ዕቃንም ወርቅንም ብርንም በዚያ የተገኙ የክብር ልብሶችንም ለቤቴ አደርጋለኍ። ክርስቲያንንም ከንጉሣቸው ጋራ አጠፋቸዋለኍ። ከሠራዊቱም ጋራ የሰበሰበውን (የገዛውን) ገንዘቡን ለሠራዊቴና ለገመል ለእንስሳም እከፍለዋለኍ። የቀሩ ሰዎችንም ለምድሬ ገበራርትና የገመልና የእንስሳ ጉሉ ጠባቆች አደርጋለኍ። ንግሥት ዣንን መንግሣንና የንጉሥ ሚስቶችን ዕቁባቱንም የሚፈጩ ገረዶችን አደርጋለኍ (አለ)። ይህንም ካለ በኋላ ነገሥትንና መኳንንትን ሠራዊትንም ጉሉ እንዲህ አላቸው። የኢፋት ንጉሥ ሳይደርስ ተነሡና እንሂድ፣ ከክርስቲያንም ንጉሥ ጋራ ለብቻችን እንዋጋ፣ (የኢፋት ንጉሥ ሳይደርስ) የክርስቲያን ገንዘብ ለእርሱና ለእኛ አይበቃምና (አላቸው)።

ይህንም እግዚአብሔር አደረገ። ዳዊትንም ይገድለው ዘንድ ክፉ ምክርን የመከረበት የአኪጦፌል ምክርን እንደለወጠ መምከራቸውን ለወጠ። ከዚህም በኋላ የአዳል ንጉሥ አስቀድመን ከጠራናቸው ነገሥትና መኳንንት ጋራ መጣ ። (ገጽ 24-25)

እንግዲህ ከላይ ለማስረዳት እንደሞከርነው ተራኪው ተረኩን የሚተርክበት አንጻር ከላይ የተመለከትነውን ተረክ ለማየት ከመቻል የራቀ ሆኖ ቢሰማንም በማይጎረብጥ እና ለታሪኩ ፍሰት በሚመች መልኩ ትረካ ውስጥ ከትቶት እናገኛለን። የዚህ አይነት ከተራኪው የዕይታ አድማስ ውጪ የሆኑ፣ ዳሩ ግን በተራኪው የሚቀርቡ ተረኮች በዜና መዋዕሉ ውስጥ በርካቶች ናቸው። ሌላው ቀርቶ የዐምደ ጽዮንን የቤተ መቅደስ ውስጥ የግል ጸሎትና ልመና ሳይቀር ቃል በቃል ይተርክልናል።

ንጉሥም ወደ ሰማይ ተመለከተ (አንጋጠጠ) ዕጆቹንም ዘረጋ እንዲህም አለ ኃያል ጽኑ እግዚአብሔር ቸር ይቅር ባይ ሰውን የምትወድ እግዚአብሔር ወገኖችህን አድን። ስለ ኃጢአታቸውም አታጥፋቸው። በይቅርታኽ ይቅር በላቸው እንጅ ቁጣኽ የራቀ ነውና ቸርነትኽም የበዛ ነውና። እውነተኛም ነኽና። እኔን ግን እንደ ወድድኽ አደርግ (አለ ብሎ) ስለ ራሱም ያይደለ ስለወገኖቹ እግዚአብሔርን ፈዕሞ ለመነ። ቸር ጠባቂ ቤዛ ኾኖ ስለ በጎቹ ፈንታ ሰውነቱን ለመከራ ይሰጣል ያለውንም የወንጌልን ቃል ፈፀመ። (ገጽ 30)

በቀላሉ እንደምንረዳው የአንድ ሰው ጸሎት በአምላክ ፊት የሚደረግ የብቻ ንግግር ሆኖ ሳለ በዚህ ያህል ጥልቀት እንዲህ አለ ብሎ ያንን ለመተረክ የሚያስችል ቅርበት መኖሩ የተራኪው ማንነት ላይ ጥያቄን የሚያስነሳ ይሆናል። በመሆኑም የአጠቃላይ ዜና መዋዕሉ ተረክ የመተረኪያ አንጻሩ ምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ አንዱን አንጻር ብቻ ለማግኘት አዳጋች ይሆንብናል።

በመሆኑም "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" የትረካው አኪያን ከአይታዊ አቅጣጫው አንጻር በአንደኛ መደብ ውስጣዊ ተራኪ የሚተረክ ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ ስሜት በሚሰጥ መልኩ ተቀያያሪ አንጻርን በተለይ ሁሉን አወቅ አንጻርን /omniscient perspective/ በማቀላቀል ይተርካል ማለት እንችላለን።

### 3.1.2 ርዕዮተ ዓለም

የዜና መዋዕሉን ተራኪ አኪያዎች ስንመረምር ልንመለከታቸው ከሚገቡ ነጥቦች መካከል የተራኪው ርዕዮተ ዓለም አንዱ ነው። ርዕዮተ ዓለም ስንል ተራኪው ለሚተርክለት ታሪክ እና ስለሚተረክለት ጉዳይ ያለው አመለካከት ሚዛኑ ምንድን ነው? የሚለውን የምንመለከትበት ነጥብ ነው። ከዚህም በመነሳት ተራኪው ተተኪረ ያደረገው ማንን ነው? ለምን? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችሉ መላምቶችን እንድንሰነዝር ዕድል ይሰጣል።

ለዚህም የሚረዱን ተራኪው ከባለታሪኩ አቅጣጫ ነገሮችን እንደምን ይመዝናል? ለባለታሪኩ ተቀናቃኝ እንደኤት ያለ ስሜት አለው? የሚሉትን እንመለከታለን። በዚህ ጥያቄ ውስጥ የተራኪውን ርዕዮተ ዓለም አመላካች ነጥቦችን ማግኘት ያስችለናልና። "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ተራኪ በተለያየ መልክ ንጉሥን መሐሪ፣ ተፈሪ ፣ ይቅር ባይ፣ ታጋሽ እንዲሁም 'ንጉሥ የሚሆን ንጉሥ ብቻ ለመሆን የተፈጠረ ነው' ብሎ የሚያምን እንደሆነ በትረካው ውስጥ እናያለን። ይሔንን ሊያብራራ የሚችል አስረጂ እንመልከት። በዚህ አስረጂ የምናየው በተረኩ ውስጥ ንጉሥ ዐምደ ጽዮንን በመክዳት የተዋጋው ሰብረዲን በንጉሡ ፊት ሲመረመር ከተናገረው ቃል የተቀነጨበ ነው።

> እንደ ፈጣሪው ሲሆን እንደ ሻ እንደ ድያብሎስም መስለኻልና (ብሎ መረመረው)። ያ ወንጀለኛም የንጉሥ ቃልን ሰምቶ ከፍርሀትና ከመንቀጥቀጥ የተነሳ የሚመልስለትን መልስ አጣ። <u>የንጉሥ ፊት ተፈሪ ነውና</u> ። (ገጽ11፣ አጽንዖት ከራሴ)

የምርመራው ሂደት እና ውጤት ምንም ቢሆን ምንም ተራኪው የተከሳሹን መልስ ማጣት ሊያያይዝ እየሞከረ ያለው የንጉሥ ፊት ተፈሪ ከመሆን አንጻር ነው። ዋናው መልዕክቱም በርግጥም ንጉሥ መሆን ተራ ሰው እንደመሆን ያለ አለመሆኑን ይልቁንም በፊቱ መቆም የማይቻል ግርማው የሚያስፈራ ታላቅ መሆኑን መስበክ ነው። በዚህም ንጉሡን ከሰውነት ተራ በማውጣት ሌላ ደረጃ መስጠትን የፈለገ ይመስላል። ይሄንን አስፈሪ ግርማ ግን ጨካኝ ብለን መተርጎም እንዳንችል ሌላ ሰብአዊ አንዳንዴም መለኮታዊ ባህሪ ያላብሰዋል። እንዲህ ሲል፡-

> እንዲህ ካሉ በኋላ ከወገቡና ከክንዱ ክታቦቹን ወሰዱ፣ የሥራየ ጥበብ ተቀዋሚነትም (አለመቃወም) ተገለጸ። ንጉሥም ይህ ጉሉ ስራይኸ ከዕጁ በውኑ አዳነኸ፣ እግዚአብሔር በዕጄ ጥሎኻልና አለው። ንጉሥ በብረት ሰንሰለት ሑለቱ ዕጆቹንና ሁለቱ እግሮቹን እሰሩት ብሎ አዘዘ። <u>ሊገድለው ግን አልወደደም ርኅሩኅ ነውና ይቅር ባይም ነውና ዕጉሥም ነውና</u> ። (ገጽ 11፣ አጽንዖት ከራሴ)

አስቀደሞ ያየነው አስፈሪነት እና አንቀጥቃጭነት እዚህ ላይ ደግሞ በሌላ ለስላሳ ባህሪ ተተክቶ እናገኘዋለን። ርኅሩኅነት፣ ይቅር ባይነት እና ዕጉሥ /ታጋሽነት/ ባህሪው እንደሆነ ይነግረናል። ይህ ስዕል ተራኪው ስለንጉሥ እና ስለንግሥና ያለውን አመለካከት ያስረዳናል። ለተራኪው ንጉሥ ማለት እንደመለኮት ግርማው የሚያስፈራ በፊቱ ለመቆም የሚያንቀጠቅጥ ከዚህ ግርማና ግዝፈት በላይ አዛኝነት ቂም አልባነት ታጋሽነት እንደሆነ ያምናል፣ እርሱንም ይነግረናል። በሌላም በኩል ንጉሥ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ከዚህ በታች በምናየው አስረጂ ላይ እንዲህ ይገልጽልናል። በዚህኛው አስረጂ ላይ ከፍ ብለን ያየነው ተከሳሽ ሰብረዲን ከዐፄ ዐምደ ጽዮን ጋር የተጋጨበትን ምክንያት የሚዘረዝር ሲሆን እኔም ንጉሥ ነኝ በሚል በዐፄው ግዛት ላይ መኳንንቶችን ስለመሾሙ የሚተርክበት ክፍል ነው።

> <u>እግር ራስን ሊኾን አይችልምና፣ ምድርም ሰማይን ሊኾን ሥራም ሠሪውን ሊሆን አይችልምና በመንግሥት መድረስ በማይችልበት በኢትዮጵያ ምድር ጉሉ ላይ ያልሾመበትን ቦታ አልተወም ማለት ያልሾመበት ቦታ የለም</u> ። (ገጽ፣ 2)

ለተራኪው ሰብረዲን ንጉሥ መሆን አለመቻሉን እግር ራስ፣ ምድር ሰማይ፣ ሥራም ሠሪን ሊሆን ካለመቻል ጋር አቻ አድርጎታል። ስለዚህም ለተራኪያችን ንግሥና ለማንም የሚሰጥ ወይም የቻለ የሚነግሥበት ጉዳይ አይደለም። ይልቁንስ "የዳዊት ዘሩን" ለንግሥና ለሚፈጠሩ ብቻ እንደሆነ በጽናት ያምናል። እነዚህ እና ሌሎች እምነቶቹም ናቸው ያተኮረባቸው ጉዳዮች እና ባጉዳይ ላይ እንዲያተኩር የሚገፉት።

እኒህ ከላይ ያየናቸው አስረጂዎች ተራኪው አተኩሮ ለሰጠው ባለታሪክ (ለዐምደ ጽዮን) ማንነት ያለውን አመለካከት የሚያሳዩ ናቸው። ምክንያቱም ስለ ንጉሥነትና ንግሥና ያለውን ርዕዮት ነው በጉልህ ለባለታሪኩ ሲሰጥ የሚታየው። በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች የተራኪውን ርዕዮት ሊገልጹ የሚችሉ አስረጂዎችን ደግሞ ለመመልከት እንሞክር።

> የሚገድል የሚያድንም የሚገርፍም ይቅር የሚልም የሚሽርም የሚሾምም የሚያዘግምም የሚያበልጽግም (ድሐ የሚያደርግም በዐለ ጸጋ የሚያደርግም) የሚያዋርድም የሚያከብርም የጸና የሚያደክም የደከመ የሚያጸና እርሱ በኾነ በአምላኩ በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን አድርጎ ሔደ። መጽሐፍ እንዳለ የእግዚአብሔር ጽናት (ብርታት) በድኩማን ላይ ይገለጻል። (ገጽ፣ 28)

ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው ምስለ ንጉሥ በተራኪው እይታ እንደተገለጸው ሆኖ እናገኘዋለን። ንጉሥን ደግሞ እንዲያ የሚያደርግ የሚሠራ የሚያደክም እና የሚያበረታ ኃላፊው እግዚአብሔር ነው ይለናል። ይሔንንም እምነቱን ተንተርሶም ለንጉሡ መጽናትና መጠንከር ምክንያት አድርጎ ያሳየናል። በተረኩ ላይ ለማየት እንደሚቻለው ገዳይ አዳኝ፣ ገራፊ፣ ይቅር ባይ፣ የሚሾም፣ የሚሽር . . . አምላክ መሆኑን አረጋግጦ ሲያበቃ ነው ንጉሥ በርሱ ጸና የሚለን። በመሆኑም ተራኪው 'የሁሉ ነገር ሠሪ ፈጣሪ ሰው አይደለም አምላክ ነው' የሚለውን ርዕዮትን በግልጽ ያስረዳል። ለርዕዮቱም ማስረገጫ መጽሐፍ ይጠቅሳል።

ከዚህም አኳያ ተራኪው ርዕዮቱን የተጋራውን ንጉሥ ተከትሎ የንጉሥ ተጻራሪ በሆኑት ላይ ሁሉ ከሳሽ እና ወቃሽ ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህ እምነቱ ውጪ /እንደ ተራኪው እይታ/ የሚያገኛቸውን ወንጀለኛ የእፍኝት ልጆች ይላቸዋል፣ እውቀታቸውን አላዋቂነት ያደርገዋል፣ ሐሰተኞች ብሎ ይፈርጃቸዋል ። ምክንያቱም አስቀድሞ ለርሱ እውነትና ትክክል ብሎ ካመነበት ርዕዮት ውጪ ናቸውና። ከዚህ በታች ያሉትን አስረጂዎች እንመልከት

> ያ ወንጀለኛ የእፍኝት እባብ ልጅ፣ መርዝ ያለው የጎበና ዘር፣ ከሰይጣን ሥር የተገኘ ማለት ከሰይጣን አባትነት የተነሣ የተገኘ የባዕድ ልጅ (ያ) የዳዊት ዙፋንን ዐሰበ። በጽዮንም እነግሳለሁ አለ። በአባቱ በዲያቢሎስም ልቡና ትዕቢት እንዳደረ በልቡናው ትዕቢት ዐደረበት። (ገጽ 2 አጽንዖት ከራሴ)

ይህን ካለ በኋላም የእስላሞች ሠራዊትን ኑሉ ሰበሰበ። ብልሆችና አዋቆችንም ከእርሳቸው ወገን መረጠ። ግን ብልሆችና አዋቆች አይደሉም ሰነፎች ናቸው እንጅ፣ ስተው የሚያስቱ ጠፍተው የሚያጠፉ ናቸው እንጅ። (ገጽ 4 አጽንዖት ከራሴ)

ያ የሐሰት መምህርም ያንጊዜ ታጣ፣ ወደ ኢፋት ምድር ሸሽቶም በዚያ ተቀመጠ። ሐሰትንም ያስተምር ነበረ። (ሐሰትን እያስተማረ) ግን እርሱ ብቻ ሐሰተኛ ኹኖ አይደለም፣ እርሱ ሳይቀር የእስላሞች ወገኖች በእግዚአብሔር ልጅ የማያምኑ ትላቸውም ሐሰተኞች ናቸው እንጅ ። (ገጽ 5 አጽንዖት ከራሴ)

ይለናል። ሚዛኑ የተራኪው ርዕዮት ነው። ከርዕዮቱ ከእምነቱ ውጭ ከሆኑ ለርሱ ሌሎች /Others/ ናቸው። የተራኪው ርዕዮት ምንጮችም ክርስቲያናዊ መጽሐፍት እና ክርስትና ነው ማለት እንችላለን። ምክንያቱም የተራኪው አመክንዮዎች ሁሉ የሚነሱት ከክርስትና መጽሐፍትና ፍልስፍናዎች ስለሚሆኑ። ይሔን የበለጠ ለመረዳት በበይነ-ቴክስታዊነት ክፍል በተጨባጭ ማስረጃዎች የምንመለከተው ይሆናል። ሆኖም የተነሳንበትን ጭብጥ አጽንተን ለማለፍ ቀጥሎ ያሉትን ሁለት አስረጂዎች እንመልከት።

የሰይጣን ልጅ፣ የእውነትም ጠላት፣ የክርስቶስ ሃይማኖትን የሚቃወም፣ ከእግዚአብሔር የራቀ፣ ወልድ ከሚሰጠው ክብር የተለየ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ከሚገኝ ሽልማትም (ጌፅም) የተለየ፣ ያ ርጉም ዐመፀኛ ከንጉሥ መላእክተኛ ይህን ነገር ሰምቶ ወደ ንጉሥ ላከ። እንዲህ ሲል ወዳንተ አልመጣም በፊትኽም አልቆምም። ወደ እኔ ብትመጣም አልፈራም። ሰይፍንና ሾተልን ይዘው፣ በፈረሶችም ላይ የተቀመጠው ጋሻ መክተው ቀስት ስበው ጦር ወርውረው የብረት በትር የሆነ ቦሎታ ይዘው የፍላፃ ጦሮችንም ይዘው። የሚጋደሉ (የሚዋጉ)፣ ከሠራዊትኽ የሚበዙ ሠራዊት አሉኝና። ወደ እኔ ልትመጣም ከወደድኽ በሰፊ መንገድ ና ። (ገጽ 3 አጽንዖት ከራሴ)

እርሱም ቅሉ ለፀብ ተዘጋጀ ንጉሥ ወደ አለበት ወደሸዋ ምድር ሊሄድ፤ የባርያ ባርያ ወደ አለቆች አለቃ፣ የውሻ ኸራት ወደ አንበሳ ራስ ሊወጣ ተዘጋጀ። የክርስቲያን መንግሥት እንደ አለቀ እንደ ተፈጸመ በማይታመን ነገር አምኖ ሊዘምት ተዘጋጀ ። (ገጽ 6 አጽንዖት ከራሴ)

ከላይ ባነሳናቸው ምሳሌዎች በግልጽ ማየት እንደምንችለው "የክርስቶስ ሃይማኖትን የሚቃወም" ሲል እንዲሁም በቀጣዩ አስረጅ "የክርስቲያን መንግሥት እንደ አለቀ እንደ ተፈጸመ በማይታመን ነገር አምኖ ሊዘምት ተዘጋጀ" ሲል የርሱን የርዕዮት ምንጭ እና አቋም በግልጽ ማሳየት ይችላል።

በመሆኑም የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ተራኪ ንጉሥ ማለት የሚፈራ፣ ታጋሽ፣ መሐሪ፣ ቂመኛ ያልሆነ ነው ብሎ የሚያምን ሲሆን ንግሥናንም ማንም እግዚአብሔር ከሰጠው በቀር የማይዘው ነው ብሎ ያምናል። ይሔን ንግሥና የሚቃወሙትን ደግሞ ከሐዲ የእባብ ልጅ የሰይጣን ዘር ይላቸዋል። ለዚህ ሁሉ ፍርድ መሰረታዊ ማስረጃውና ማጽኛው ቃለ እግዚአብሔር የሚለው ክርስትናዊ አስተምህሮ ነው።

### 3.1.3 አላማ

በዚህ ክፍል የምንመለከተው የተረኩ አኳያ "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ተራኪ መሰረታዊ አላማው ምንድን ነው? የሚለውን ነጥብ ነው። ይህን ለመረዳት አጠቃላይ ተረኩ የሚያጠነጥንበትን ጭብጥ እና ባለታሪኩ የሚያልፍበትን የታሪክ መስመር በቅጡ መመርመር ያስፈልጋል። በሌላም በኩል ተራኪው በሚተርክበት ጊዜ አትኩሮቱ ያለበትን ስፍራ እንዲሁም ደጋግሞ የሚያነሳቸውን ርዕስ ጉዳዮች እና እነዛን ርዕስ ጉዳዮችና ድርጊቶች የሚገልጽበትን መንገድ በጥንቃቄ ማጤን ተገቢ ነው። የዚህ ጥናት አቅራቢ የዜና መዋዕሉ ተራኪ አላማ ሁለት ነው ተብሎ ያምናል። እነዚህም ሁለት አላማዎች ለባለታሪኩ (ለዐምደ ጽዮን) ምድራዊ ልዕልና መስጠት እና ሰማያዊ ብጽዕናን ማጎናጸፍ ናቸው።

#### 3.1.3.1 ምድራዊ ልዕልና መስጠት

በዚህ ትንታኔ ውስጥ 'ምድራዊ ልዕልና' ስንል ባለታሪኩ በኖረበት ቦታ እና ጊዜ ውስጥ ከሁሉ የላቀና ከፍ ያለ ማንነት መስጠት ማለታችን ነው። በዚህ መሰረትም በ"ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ላይ ከመጀመሪያው አንስቶ የሚጀምርበት የታሪኩ ክፍል ሆን ተብሎ የንጉሡን ልዕልና ማግዘፍን ኢላማ ያደረገ ነው። ይሔንን ልዕልና የማላቅ ሥራ ተራኪው ሲሠራ ደጋግሞ የሚጠቀምበት ብልሐት አለው። ይሔም ብልሐት የዐምደ ጽዮን ተቃዋሚ ሆነው የሚነሱትን ጠላቶች ከፍ አድርጎ አልቆ የመሳል ብሂል ነው። በሌላ አባባል አስቀድሞ ጊዜያዊ አተኩሮን ለተቀናቃኙ ይሰጣል። ይህም ከፍ ተደርጎ የተሳለ 'ጠላት' በዐምደ ጽዮን ኃይል ሲገረሰስ በማሳየት ንጉሡን የአሸናፊዎች አሸናፊ የኃያላን ኃያል ተደርጎ እንዲታይ ያደርገዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ተቀናቃኙ ከፍ ከማለቱ ጋር ንጉሡን የሚዳፈርበት መጠን ኃያል እና ሰብዕናን የሚፈታተን ለቁጣ የሚጋብዝ እንዲሆን ያደርገዋል። ይሔ አይነት አገላለጹም ንጉሡ ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ትክክለኛ ገፊ ምክንያቶች ሆነው እንዲሰሙን ከማስቻሉም በላይ ተረኩ ልብን ቀፍድዶ እንዲይዝ ያስችለዋል። ከላይ ያነሳናቸውን ነጥቦች የሚያስረግጡ አስረጂዎችን በዝርዝር እንመልከት።

ዐምደ ጽዮን የተባለ የኢትዮጵያ ንጉሥ በፈጣሪው ላይ እንደተመካ፤ (ታበየ) እንደ ልዑልም እግዚአብሔርም እኾናለሁ እንዳለ እንደ ዲያብሎስ ራሱን ከፍ ከፍ ያደረገ፣ ፍጹም ዕቡይ ወንጀለኛ የወንጀለኞች ንጉሥ እንደ ከዳው እንዳመፀበት ሰምቶ ነበር፡፡ ስሙ ሰብረዲን የሚባል የወንጀለኞች ንጉሥ ራሱን ከፍከፍ አደረገ፤ በጌታው በዐምደ ጽዮንም ላይ ተመካ፡፡ እንዲህም አለ በኢትዮጵያ ምድር ጉሉ ላይ ንጉሥን እኾናለኹ፡፡ ክርስቲያኑም እንደ ሕጌ አስመልካቸዋለኍ፡፡ አብያተ ክርስቲያንንም አፈርሳለኍ (አለ)፡፡

ይህንም ብሎ ተነሥቶ ሔደ ወደ ክርስቲያንም ምድር ደርሶ ቤተክርስቲያንን አቃጠለ፡፡ ክርስቲያንንም ገደላቸው፡፡ የተረፉ ወንድንና ሴትንም ማርኮ ወደ ሕጉ አገባቸው፡፡ ከዚህም በኋላ እንዲህ አለ የፅዮን ንጉሥ በኢትዮጵያ አውራጃዎች ላይ ገዢዎችን እዲሾሙ እኔም እሾማለኍ (አለ)፡፡ መሳፍንትንና መኳንንትንም ሾመ ፡፡ (ገጽ1 አጽንዖት ከራሴ)

እንዲህም አለ አብያተ ክርስቲያንን ለእስላሞች መስገጃ አደርጋለኍ፡፡ የክርስቲያን ንጉሥንም ከወገኖቹ ጋራ ወደ ሕጌ አገባዋለኍ፡፡ ከመኳንንትም እንደ አንዱ እሾመዋለኍ፡፡ ወደ ሕጌ መግባትን ዕምቢ ቢል ግን እንስሳን ለሚጠብቁ ዘላኖች ወርጅሕ ለሚልዋቸው አሳልፌ እሰጠዋለኍ፡፡ ገመሎችን የሚጠብቅ ያደርጉት ዘንድ፡፡ የንጉሥ ሚስት ንግሥት ዣን መንግሣንም የምትፈጭ ገረድ አደርጋታለኍ፡፡ የመንግሥቱ ከተማ መርዓዴንም የኔ ከተማ አደርጋለኍ፡፡ የጫት ተክልንም በዚያ እተክላለኍ፣ እስላሞች ያንን ተክል ይወዱታልና (አለ)፡፡(ገጽ 2፣ አጽንዖት ከራሴ)

ተራኪው እንደሚነግረን ሰብረዲን እጅግ ተመክቷል፡፡ መመካቱም በንጉሡ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ተራኪው አምላክና ፈጣሪ በሚለው ከላይ ባየነው የርዕዮቱ መሰረት በሆነው ክርስትናው ሁሉ ላይ ነው፡፡ የሰብረዲን ንቀት እና ግፊያው ከንጉሡ እምነት ሃይማኖት ጋር ብቻ አይደለም፡፡ በርስት በሥልጣኑም ጭምር እንጂ፡፡ እናም ንጉሥ ይሾምበት በነበረበት ግዛት ሁሉ ሹመትን ይሰጣል፡፡ በኢትዮጵያ ግዛት ሁሉ ላይ ለመንገሥ ያልማል፡፡ ከፍ ሲልም ንጉሡን ከመስፍኖቹ እንደአንዱ ሊሾመው ይመኛል፡፡ ይህ ሁሉ በቂ አይደለም በእምነቱ ያላገጠበት በርስት በሥልጣኑ ያዘዘበት በመጨረሻ ደግሞ በሰብዕናው ላይ ይመጣል፡፡ እምቢ ቢል ለግመል ጠባቂ እረኝነት ሊሸጠው ሚስቱንም እንደገረድ ወፍጮ ሊያስፈጫት ይዝታል፡፡ ስለዚህም የሰብረዲን ድፍረት በንጉሡ እምነት፣ ግዛት እና ሚስት ላይ ሁሉ የመጣ በመሆኑ ትንሽ ጠላት ወይም ወንጀለኛ ነው ብለን አናምንም፡፡ አንድ ንጉሥ በግዛቱ፣ በመንግሥቱ ከዛም አልፎ በሚስቱ ከመጡ እንደንጉሥ ምንም አይቀረውም፡፡ በመሆኑም የዐምደ ጽዮን ጠላት ቀላል እና ትንሽ አይደለም፡፡

ይሔ ስዕል ነው የዐምደ ጽዮንን ድል ታላቅ ሆኖ እንዲታየን የሚያደርገው፡፡ ዐምደ ጽዮን በጭፍሮቹ አማካይነት ከተዋጋ የሰፍረዲንን ግዛትና ሀገር ከመዘበረ፣ ራሱም በአካል ብቻውን ከዘመተ በኋላ ሰብረዲን ሲንበረከክ ሲሸነፍ ተራኪው ያሳየናል፡፡ ያውም ሽንፈቱን የሚነግረን ገረድ አደርጋታለሁ ብሎ በዛተባት በሚስቱ በገ'ን መንግሣ በኩል ምልጃን እንደላከ በመንገር ነው፡፡ በዚህ ተረክ ውስጥ የሰብረዲን መሸነፍ አይደለም ጎልቶ የሚታየን፤ ዐምደ ጽዮን እንደምን ችሎ ይሄን "ሰይጣን" አሸነፈው ስንል ነው እምንገኘው፡፡ ይህ ማለት ንጉሡ እጅግ ኃያል ማንንም ማንበርከክ የሚችል ነው ብለን እንድናምን ያደርገናል፡፡ አሊያማ በሀገር እንደሚገኙ እንደተራ አማጺና ሽፍታ ቀጣው ገደለው ሊለን ይችል ነበር፡፡ በዚህ መልክ አቅልሎ የተረካቸው ሌሎች ትረካዎች በዜና መዋዕሉ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሌሎች የዜና መዋዕሉ ክፍሎች ውስጥም እንዲሁ ጎልቶ የሚታይ የልዕለ ሰብዕና ግንባታን እናገኛለን፡፡ በበርካታ ጦርነቶች ላይ ንጉሥ በወታደሮቹ መከታነት የሚኖር መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ለዚህም ራሱ ዐምደ ጽዮን በዚሁ ዜና መዋዕል ላይ "ንጉሥማ ሠራዊቱን ይጣራ ነበር፣ ወደ ፀብ (ጦር) ይሰዳቸው ዘንድ፡፡ ወደ ፀብ (ጦር) ትሰዱኝ ዘንድ እኔን እንዴት ትጠራላችሁ ያለኔ መዋጋትንስ እንዴት አትችሉም" ሲል ይሞግታል፡፡ በዚህ ዜና መዋዕል ውስጥ ንጉሡ ወታደሮቹን ሳይቀር በጦርነት እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚጋርድ የሚታደግ ሆኖ ተስሏል፡፡ ከተራ ሰው ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ነገሥታት ሁሉ የተለየ መሆኑን መንገር የተራኪው ዋና አላማ ነው፡፡ ይሔንን የሚያረጋግጡልንን ጥቂት ክፍሎችን በአስረጂነት እንመልከት፡፡

> ከዚህም በኋላ ዐመፀኞች መጡ በሌሊት በዝግታ ይጣሉት ዘንድ፡፡ ብዛታቸው እንደ ባሕር አሸዋ ሆነ ፯ ታላላቅ አህጉር አደል ሞራ ጢቆ ጳጉማ ለበከላ ወርጋር ገቦላ እሊህ ጉሉ ወደ ቦታችን ሳይደርስ በሌሊት እንጨርሰው፣ ከሠራዊቱም ጋራ ተኝቶ ሳለ ከእርሳቸው አንዱን አናትርፍ ብለው በክፉ ምክር ተባብረው (መጡ)፡፡
>
> ንጉሥም ከሠራዊቱ ጋራ በተኛ ጊዜ ዐመፀኞች ከተማውን ከበቡ፡፡ የንጉሥ ሠራዊትም ያንዜ ጮኹ፡ ንጉሥ ወዴት አለ ከወንጀለኞች ዕጅ ያድነን ዘንድ ብለው (ያንጊዜ ጮኹ)፡፡ ንጉሥም የከተማ ጩኸትን ሰምቶ ከእንቅልፉ ነቃ፡፡ ከምኝታውም ተነሥቶ ሰይፉን ታጥቆ ከድንኳኑ ወጥቶ በፈረሱ ላይ ተቀምጦ ወንጀለኞችን ተገናኛቸው ተዋጋቸውም፣ ከፊቱም ፊዕመው ሸሹ፡፡ እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ወደ ከተማው ተመለሰ፡፡ ወንጀለኞች ዳግመኛ መጡ በለሊት ንጉሥን ከሠራዊቱ ጋራ ያጠፉት ዘንድ፡፡ የንጉሥ ሠራዊትም ንጉሥ የት አለ፣ ከውሾች ያድነን ዘንድ

ብለው ጮኹ። ንጉሥም ያንጊዜ ወጥቶ ከዐመፀኞች ጋራ ተጋደለ። በእግዚአብሔርም ኃይል አሸነፋቸው። ወልድንም እያመሰገነ ወደ አደራሹ ተመለሰ።

በቀዳሚ ጊዜና በኋላ ጊዜ ከመጡ ዐመፀኞች የበዙ ዐመፀኞችም በመንፈቀ ሌሊት በቀስታ በዝግታ ደግመው መጡ። ንጉሥንም ከሠራዊቱ ጋራ በጉሉ ዘንድ ማለት በ4 መዓዝን ከበቡት ታላቅ ድንፋታም ደነፉ ከተማም ይህን ድንፋታ ዕጅግ ሰማች። የንጉሥ ሠራዊትም ወንድና ሴት ታናሽና ታላቅ ተፍጸጹ (ጮኹ)። ንጉሣችን ጌታችንም በየት አለ ከዐመፀኞች ዕጅ ያድነን ዘንድ፣ ልንጠፋ ነውና (ደርሰናልና) ብለው (ጮኹ)።

ንጉሥም (ያንጊዜ ወጣ) እርሱ ራሱ ታጥቆ በፈረስ ላይም ተቀምጦ ያን ጊዜ ወጣ። እንዲህም አለ ባሪያ ዳዊትን ከክፋዎች ጦር ያዳንኸው ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዕዳቸው አድነኝ (አለ)። ንጉሥ ይህን ካለ በኋላ ወደ ፀብዕ ገባ። ወንጀለኞችንም ገደላቸው፣ በኢየሱስ ክርስቶስም ኃይል አቸነፋቸው ።

ከእርሳቸውም አንዱ ከሠራዊቱ እንደ አንዱ መስሎ በንጉሥ በኋላ በኩል መጣ (መጥቶ) በሰይፍ መታው፣ የወገቡንም ዝናር ቆረጠ የሚጎናፀፍበትን የፀብ ልብስ (የሰልፍ ልብስንም) ቆረጠ። ንጉሥን ግን እግዚአብሔር አዳነው። ንጉሥም ተመልሶ በጦር ፊቱን ወጋው ከባዕድ ወገኖችም ለይቶ ያን ሰው በአንድ ጊዜ ጣለው።

ሠራዊቱም ዐመፀኞችን ተከትለው ሔዱ። ዐመፀኞችም ተመልሰው ከንጉሥ ሠራዊት ጋር ተጋደሉ። የንጉሥ ሠራዊት ከእነዚያ ጋራ መዋጋትን አልቻሉም፣ ንጉሥ ወዴት አለ ብለውም ጮኹ። ንጉሣቸው ፅኑ ነውና፣ በፀብዕ ጊዜም የሚመስለው የሌለ አሸናፊ ነውና። እንደዚህም ሲጮኹ፣ ንጉሥ (በኋላቸው ደረሰ) በፈረስ ላይ ተቀምጦ በኋቸው ደረሰ። በወንጀለኞችም መካከል ገባ ከእርሳቸውም አንዱን በጦር አፍ ወጋው ወደኋላውም ወደቀ። ያንጊዜም ዐመፀኞች ሸሹ፣ በፊቱም ሊቆሙ አልቻሉም። ንጉሥም ከሠራዊቱ ጋራ ተከተላቸው ፈፅሞ ገደላቸው። በድኖቻቸውንም በምድር ፊት ላይ ረበረበ። አባት እግዚአብሔርንም ከልጁና ከቅዱስ እስትንፋሱ ጋራ እያመሰገነ ወደ ከተማው ተመልሶ ገባ። ድል መንሣትን ሰጥቶታልና ። (ገጽ14-15፣ አጽንኦት ከራሴ)

በዚህ አስረጅ ላይ እንደተመለከትነው አስቀድሞ የጠላትን ጽናትና ብዛት ነው የሚዘረዝርልን። ጠላቱ ኃያል መሆኑን ሲያገዝፍ። ቀጥሎ ደግሞ የንጉሡን ሠራዊት ፈሪ

እንደህጻን ያለ ረዳት ፈላጊ አድርጎ ያስቀምጠዋል። ያ ሁሉ የርሱ ሠራዊት ያልቻለውን የባላንጣ ጦር ከእንቅልፉ ነቅቶ፣ ታጥቆ፣ ፈረሱ ላይ ወጥቶ የሚፋለመው እና የሚያሸንፈው ዐምደ ጽዮን ነው። ማሸነፉ ብቻ አይደለም ትልቁ ጉዳይ የንጉሡን ታዳጊነት /አዳኝነት/ ማሳየት ጭምር እንጂ። በዚህ ዜና መዋዕል ላይ በኃያል ባላንጣ እና በደካማ ሠራዊት መካከል ደጋግሞ ንጉሡ ሲገኝ እናስተውላለን። ሁሌም ግን አሸናፊ ነው። እንዲህ ጠላቱን ኃያል የርሱን ሠራዊት ፈሪ አድርጎ ተራኪው ለምን ማስቀመጥ አስፈለገው? ካልን አሁንም መልሱ የተረኩም ዋና አላማ የንጉሡን ልዕለ ሰብዕነትን ማግዘፍ በመሆኑ ነው የሚል ነው። ከላይ እንደተመለከትነውም በግልጽም "ንጉሣቸው ፅኑ ነውና በፀብዕ ጊዜም የሚመስለው የሌለ አሸናፊ ነውና" ሲል ይነግረናል።

ተራኪው በተለየ ሁኔታ ንጉሡን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ላይ ሲያስገባው ብቻውን እንዲነጠል ያደርጋል። አንዳንዴም ሲተርክ "ከሠራዊቱ ተሰወረ" ነው የሚለን (ገጽ 9)። ወይም የሚመካባቸው የተባሉ ታላላቅ ተዋጊዎቹን ወደሌላ ስፍራ ልኳቸው ነበር ከርሱ ጋር አልነበሩም ብሎ ነው ብቻውን ለችግር ለጦርነት አሳልፎ የሚሰጠው። እንዲያም ሲል በዚህ መነጠሉ መለየቱ ላይ ህመምና ስቃይ ይጨምርበትና ያጎሳቁለዋል። በዚህ በተደራረበ መዳከም ውስጥ የሚመጡበት ጠላቶች ብዛት ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ቆጥሮ የሚጨርሳቸው አይሆኑም። ንጉሥ በሠራዊቱ ይታመናል፣ እንዲያም ሲል በኃይሉ በጤናው ተስፋ ያደርጋል፤ ዐምደ ጽዮን ግን ብቻውን ነው እንዲሆን የሚያደርገው። እስቲ በአስረጂ ይህንኑ የሚያረጋግጥልንን ተረክ እንመልከት።

> [የዐምደ ጽዮን ወታደሮች] በፈረስ መቀመጥን በእግር መሮጥን የለመዱ ሰዎች ናቸው፣ ለመጋደል የተዘጋጁ የጸኑ ዐርበኞች ናቸው። ወደ ፀብ በገቡ ጊዜ እንደ አሞራ ይበራሉ እንፌቆም ይሮጻሉ። እግራቸውም ደንግያን ይፈነቅላል (ይገለብጣል)። ድምፃቸውም እንደ ባሕር ድምፅ ነው።
>
> ሕዝቅኤል ነብይ እንዳለ የመላእክት የክንፈሮቻቸውን ድምፅ እንደ ብዙ ወሐ መስሎ ሰማሁ፣ እንደ ሠራዊት ድምፅና እንደ ከተማ ቃልም በዝቶ ሰማሁ (እንዳለ)። በፀብ ጊዜ የታመነባቸው የንጉሥ ዐምደ ጽዮን ሠራዊትም እንዲሁ ናቸው። ወንጀለኞች በተጣሉት ጊዜ ግን እሊህ ሁሉ ከእርሱ ጋራ አልነበሩም። ንጉሥ እነሱን የሰደደበትን ሌላ አውራጃን ሊጣሉ (ሊወጉ) ሔደው ነበሩ እንጅ። ከሔዱም ዘንድ ሰዎችን ወንድና ሴትን ሽማግሎችንና ሕፃናትን እንስሳንም ገደሉ። በንጉሣቸው ዘንድ የኾነውን ነገር (ግን) አላወቁም ነበረ። ንጉሥ ዐምደ ጽዮን ግን የታመመ ኾኖ በአዳራሹ ውስጥ ነበረ። በዐልጋውም ላይ ተኝቶ ነበረ። ዕጅግም ይታመም ነበረ።

የሰባት ቀንና ሰባት ሌሊት እኽል አልበላም ወሐም አልጠጣም፡፡ ውሾችን የሚስቡ የታናናሾች ጭፍሮች አለቃ የኾነ ስሙ ዘና የማኑ የተባለውን አንዱን ወታደር እንዲህ አለው ሔደኽ አራዊትን አድን (አለው)፡፡ ሲሔድም ከወንጀለኞች ዐረበኞች ጋር ተገናኘ፡፡ አራዊትንም ማደን ትቶ ወደ ንጉሥ ላከ እንዲህ ሲል ከሠራዊትኽ ኹሉ የሚበዙ የወንጀለኞች ሠራዊት መጡ፡፡ እኛም ከአንተ ጋራ እንሞት ዘንድ ወዳንተ እንመጣለን (ብሎ ላከ)፡፡

ንጉሥም ያን መልእክት ሰምቶ በፈረሶች ላይ የተቀመጡ (የወጡ) ጉብኞችን ሰደደ፡፡ የወንጀለኞች ጭፍራ ምንአልባት ብዙ እንደ ኾነ ጥቂትም እንደ ኾነ ያዩ ዘንድ፡፡ የንጉሥ መልእክተኞችም ምድርን ኹሉ እንደሚያለብስ እንደአንበጣ ብዛትና የሰማይን ስፋትን (እንደሚያለብስ) እንደሚሸፈን እንደተዘረጋ ጓሜ ወንጀለኞች የበዙትን ብዛት ባዩጊዜ ዐይኖቻቸው ጨለሙ፡፡ ልቡናቸውም ጠፋ፡፡ ወደ ንጉሥም ተመለሱ ነገሩትም እንዲህ ሲሉ ምድር ኹሉ እነዚያ አሕዛብን መወሰን (መቻል) አትችልም የኢትዮጵያ ሠራዊትም ኹላቸው ቢመጡ፡፡ ከዳርዋ ዠምረው እስከ ዳርዋ ድረስ ያሉ ታናሽና ታላቅ ተሰብስበውም ቢመጡ ከእነሱ ጋራ መጋደልን ባልቻልንም ነበረ ብለው (ነገሩት)፡፡

ንጉሥም ይህንም ነገር በሰማ ጊዜ ከምኝታው ተነሣ፡፡ የታመመ የደከመ ሲኾንም ከድኳኑ ወደ ኣፍኣ ሲወጣ ወደደ፡፡ በላዩም ላይ ካለበት ሕማም ብዛት (ጽናት) የተነሳ ወገቡን መታጠቅና በእግሩ መቆም አልቻለም፡፡ ከዐልጋውም ወደቀ፡፡ ብላቴኖቹም (ባሮቹም) ኣነሡት ወገቡንም በሰልፍ ትጥቅ አስታጠቁት፡፡ ወዲያና ወዲህ እየተናጨም (እየተወዛወዘም) ከድንኳኑ ወጣ

ሑለትም እቴጌዎች ንጉሥን ተከተሉት፡፡ መሪር እንባም (እያፈሰሱ) አፍስሰው እያለቀሱ እንዲህ አሉት ጌታችን እንዴት ወደ ፀብ (ጦር) ትሔዳለኽ፡፡ ሕያው እንደ ነበርኽበት ጊዜ እንደ ድሮው ለመሮጽ እግር አለኽን፡፡ ቀስትንም ትስብ ዘንድ ጋሻንና ጦርንም ትይዝ ዘንድ ዕጅ አለኽን፡፡ በፈረስም ላይ ትጫን ዘንድ ኃይል አለኽን፡፡ ኣካልኽ በህማም ኀድላለችና (አሉት)፡፡ መሪር እንባንም እያነቡ ዕጅግም እያለቀሱ ይህን አሉ፡፡

ንጉሥ ግን እኔ የሴቶች ሞትን እሞታለትን፣ እኔ የሴቶች ሞትን አልሞትም የሚጋደሉ የጎበዞች ወንዶች ሞትን አውቃለትና ብሎ መለሰላቸው፡፡ ይህንም ካለ በኊላ ሔደ ፡፡ (ገጽ 26-27፣ አጽንኦት ከራሴ)

[. . .] የወንጀለኞችም ሠራዊት ያን ጊዜ መጡ። ሰይፎቻቸውም እነደ መብረቅ እያንፀባረቁ (መጡ)። የተሳቡ ቀስቶችና የብረት ጦር የእንጨትም ጦሮች የብረት በትር የኾነ መንዶም በዕጆቻቸው ተይዘዋል። ብዛታቸውም እንደ አንበጣና እንደ ሰማይ ከዋክብት በባሕርም ዳር እንዳለ አሸዋ ሰማይንም እንደሚሸፍን ደመና ነው ድምፃቸውም ነፋስ እንደሚመታት እንደ ባሕር ማዕበል ድምፅ ነው። ቃላቸውም በዝናም ጊዜ እነደሚሰሙ እንደመብረቅና እንደ ነጎድጓድ ቃል ነው። ተራሮችና ኮረብቶችም በጩኸታቸው ቃል ተነዋወጹ። ምድርም በእግራቸው ድምፅ ተናወጸች።

የተወደድኽ ሰው ሆይ የምነግርኽን ነገር ዳግመኛ ስማ። ነገሬንም ከንቱ አታስመስል ለኤማ ዛፎችም ተራሮችም ኮረብቶችም ከእርሳቸው ጋራ የሚሮጹ (ለኔ) መሰለኝ። ዳመናት በሰማይ ስፍሐት (ኀዋ) በሮፁ ጊዜ ጨረቃና ከዋክብት የሚሮጹን እንዲመስሉ። ለኛም እንዲሁ መሰለን።

የወንጀለኞችም አመጣጥ እንደዚህ ነው። ምድርን ጉሉ አልብሰዋታልና፣ ብዙዎችም ናቸውና፣ ቁጥርም የላቸውምና። ለመናገርም ያፅራል (ያስጨንቃል)። ሕሲናም ይደክማል ማለት ሊደርስበት አይችልም። ከንፈርም ይህን መተርጎም አይችልም አንደበትም ይህን መናገር አይችልም።

ሰይፎቻቸውም ያንፀባርቃሉ፣ ምድርም ተናወጸች። የሰዎችም ልብ ጠፋ፣ ኃይላቸውም (ደከመ) እንደ ሰም ቀለጠ። አራዊትም ቦታ አጡ፣ ሸሽተውም ወደ ንጉሥ ዐምደ ጽዮን ከተማ ገቡ። ወንጀለኞች ምድርን ጉሉ ከበዋልና ። (ገጽ30-31፣ አጽንኦት ከራሴ)

ተራኪው በታላቅ ግርማቸው የሳላቸው በምድር ያለን ድንጋይ በእግራቸው የሚፈነቅሉ በሰማይ እንደነንስር የሚበሩ የንጉሥ ሠራዊቶች በዚህ ክፉ ሰአት ከንጉሥ ጋር አይደሉም። ይልቁንም ሴቶችና ህጻናት ደካሞችና ካህናት ናቸው ከርሱ ጋር የሚገኙት። ከላይ ባልነው መሰረትም በእግሮቹ መቆም ትጥቆቹን እንኳ መታጠቅ ያልቻለ ደካማውን ዐምደ ጽዮን ነው የሚያሳየን። ሚስቶቹ ትዋጋበት ዘንድ ምን አካል ምን ጉልበት አለህ? የሚሉለትን በህመም የደቀቀ ዐምደ ጽዮንን ነው ከፊታችን የሚያስቀምጠው።

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን በአስገራሚ ገለጻ በአስፈሪ ስዕል አግዝፎ የሚያሳየን የባላንጦቹን ኃይል ነው። በእውኑ ለሚያይም ይህ ንጉሥ አለቀለት ያስብላል። ምናልበትም የዜና መዋዕሉ ፍጻሜ በንጉሥ ሽንፈት የሚደመደም ይመስላል። "ብዛታቸውም እንደ አንበጣና እንደ ሰማይ ከዋክብት በባህርም ዳር እንዳለ አሸዋ ሰማይም እንደሚሸፍን ደመና

ነው" የተባለላቸውን የጦር አዋቂነታቸው የተነገረን ኃያላን ከዐምደ ጽዮን ጋር ስናስተያየው ግምታችንን እናምናለን። ይህ ጠላትን አግዝፎ የመሳል ዋና ግቡ የሚገባን ተረኩ መቋጫውን ሲያገኝ ነው።

> ንጉሥ ግን የዮርዳኖስ ወሐን በላያቸው ላይ አስረጨ። ስራያቸው ይጠፉ ዘንድ። በፈረሶች ላይ የተቀመጡ ሰዎችንና እግረኞች ሰዎችንም ወደ ፊቱ ሰደደ፣ ወንጀለኞችንም ተገናኙአቸው። በፊታቸው መቆምንም አልቻሉም፡ ኍላቸውም ሸሹ። ከሠራዊቱም ወገን ወደ ከተማ ቅዕር ገብተን በዚያ እንዋጋ (እንጋደል) ብሎ ለንጉሥ የነገረው ሰው አለ። ንጉሥ ግን እንዲህ አለ በሚስቴ አጠገብ አልሞትም እንቢ፣ በሰልፍ ውስጥ የወንድ ሞት እሞታለኍ እንጂ (አለ)። በፈረሶች ላይ ተቀምጠን እንሸሽ ሠራዊትም ወዳሉበት ቦታ እንሒድ። ከሠራዊትም ጋር ተመልሰን ልንጋደላቸው (ልንዋጋቸው) ብትሻ እንደፈቃድኽ ይኹን ያሉትም አሉ።
>
> ንጉሥም መለሰ እንዲኽ አለ። አምላኪየ ያሠለጠነኝ የሾመኝ እኔ ሚስቴንና ልጆቼን ሰዎችንም ኍሉ ብተው። ወይም ገገርዬ (ፈጣሪዬ) ያስጠበቀኝን ሚስቴንና ልጆቼን ሰዎቼንም ኍሉ ብተውማ (መተውማ) ኢየሱስን እተዋለኍ ማለት አምላኪዬ ኢየሱስን መካድ ነው። ይህንም አላደርግም፤ የእግዚአብሔር ልጅ ሊገድለኝ ከወደደ ይግደለኝ እንጅ ሊያድነኝም ከወደደ ያድነኝ እንጅ (ብሎ መለሰ ንጉሥ)።
>
> ይህንም ባላቸው ጊዜ ወዳጆቹ ዕጆቹንና እግሮቹን ዐይኖቹንም ደረቱንም ትከሻውንም ሳሙት። ለሞትም ሰጥተውት ኍላቸው ሸሹ። ንጉሥ ግን እንደማያዘነብል ምሰሶና እንደማይነዋወጽ መሰረት እንደ አድማስ ግድግዳም ጸንቶ ብቻውን ቆመ። ሠራዊቱንም እንዲህ አላቸው የምገደልም እንደኾንኹ፣ የምሞትም እንደሆንኹ፣ እግዚአብሔር በዕጁ ዛሬ እንዴት እንዲያደርግ ታዩ ዘንድ ጥቂት ታግሳችኍ ቁሙ አላቸው።
>
> ቃሉን ግን የሚሰማው ማንም ማን አልነበረም። ኍላቸው ሸሹ እንጂ። ኍላችው ሸሹ ብልም በፍርሃት አይምሰላችኍ አታድንቁም። ግን እንዲህ እላለኍ የሸዋና የዳሞት የጎዣምና የትግሬ ሠራዊት የአምሐራ የብጉና ሠራዊትም የኢትዮጵያ ሠራዊት ኍላቸውም በሙሉ በእግዚአብሔር ኃይል ባይሆን (ካልሆነ በቀር) በፊታቸው መቆምን ባልቻሉም ነበረ (አልኍ)። (ገጽ 31-32 አጽንዖት ከራሴ)

ንጉሥም የወንጀለኞች ብዛት ወዳለበት በግራ በኩል ገባ። ወደ ኋላውም አላፈገፈገም። ፍላፃም በላዩ ላይ እንደ ዝናም ሲዘንም፣ የብረት ዘገርና ብትርና

የእንጨቶች ጦሮች እንደ በረድ በላዩ ሲዘንሙ ዠርባውን አልመለሰም (አልቀለሰም)፡፡ ሰይፎችንም ይዘው ሲከቡት መጡ፡፡ እርሱ ግን ፊቱን እንደ ደንጋይ አጸና፡፡ ልቡንም (ስውነቱንም) ለሞት አስጨከነ፡፡ የወንጀለኞችንም ከተማ ሰነጠቀ፡፡ አንዱንም በወጋው ጊዜ ሑለተኛውን ወጋው፡፡ ሑለቱንም ጉሉ እንደ አንድ አካል መጠን በእግዚአብሔር ኃይል በአንዲት ጦር ወጋችው፡፡

ወንጀለኞችም ያን ጊዜ ፊጽመው ሸሹ፡፡ በፊቱ መቆምንም አልቻሉም፡፡ ማንም ማን በፀብ ጊዜ በፊቱ መቆምን የሚችል የሌለበት፣ ከድሮ ዠምሮ ፀብን የተማረ ነውና፡፡ በመጀመሪያ የጠራናቸው በፈረሶች ላይ የተቀመጡ ስድስቱም፡ ወንጀለኞችን በኋላቸው በኩል ወጉአቸው፡፡ ሸሽተው የነበሩ ሠራዊትም ንጉሥ ወንጀለኞችን ባባረራቸው ጊዜ ተመለሱ፡፡ ወንጀለኞችንም እግዚአብሔር ባዘጋጀው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ አራገፋቸው፡፡ እነዚህም ቁጥር የሌላቸው ዕጅግ የበዙ ነበሩ፡፡

ከፈረሱም ወረደ ጋሻንም ያዘ ወንጀለኞችንም ወጋቸው፡፡ ቀኝ ዕጁ በደከመ ጊዜ በግራ ዕጁ ይወጋ ነበረ፡፡ የግራ ዕጁ በደከመ ጊዜም በቀኝ ዕጁ ይወጋ ነበር፡፡ የእነዚያ አሕዛብ ግን ቁመታቸው የረዘመ ነው፡፡ መልካቸውም የከፋ ነው የራሳቸውም ጸጉር እንደ ሴት ጸጉር የተፈተለ ነው (የተታታ ነው)፡፡ እስከ ወገባቸውም ድረስ ይደርሳል፡፡ ወደ ፀብም በገቡ ጊዜ ይየያዛሉ፡፡ አንዱም ከአንዱ ጋራ የልብሱን ዘርፍ ያስራል፣ ከፀብ እንዳይሸሹ፡፡ ሰልፍን የተማሩ ዕጅግ ተጋዳዮች (አርበኞች ናቸው) ናቸውና፡፡

ንጉሥ ዐምደ ጽዮን በእርሳቸው ላይ ጸና በእግዚአብሔርም ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ነቀላቸው ጨረሳቸውም የሰማይ ሙሽራ በኾነች፣ የዓለምም ጉሉ መመኪያ በኾነች በጽዮን አጋዥነትም፡፡ በካህናትና በዲያቆናት በመነኩሳትም ጸሎት በአማኒዎች ወንዶችና በአማኒዎች ሴቶችም ጸሎት፡፡ ይልቁንም በፍጹም ሃይማኖቱ ጽናት ጨርሶ አጠፋቸው፡፡

ንጉሥም ከዚህ በኋላ በፈረሱ ላይ ተጫነ የሸሹትንም ተከተላቸው፡፡ ከሠራዊቱም ጥቂቶቹ ተከተሉት፡፡ ንጉሥም እንዲህ አለ የተጋደሉ ሰዎችን ሰለባ አትውሰዱ፡፡ በሕይወት ያሉ ወንጀለኞችን ተከተሉ እንጂ የተገደሉ ሰዎችን ግን ሴቶች ይግፈፉ አለ፡፡ (23-33 ፣አጽንኦት ከራሴ)

በዚህ ተረክ ላይ እንደምንመለከተው የደከመው ዐምደ ጽዮን ሲበረታ እና ለጸብ ሲወጣ ከርሱ ጋር ያለው ሠራዊቱ ግን የሚያፈገፍግ ሆኖ ይገኛል፡፡ ዐምደ ጽዮን በኪሳራ

ላይ ኪሳራ እንደወደቀበት እናምናለን። በዚህ ሰአት ግን ልዕለ ሰብዑ ዐምደ ጽዮን ይገለጣል። እንደ አንበጣ ምድርን የወረረ እንደደመና ሰማይን የጋረደ የተባለለትን ኃይል ብቻውን ይጋፈጣል። ያሉትን ሁለት ተዋጊዎች ቀለል ባለው የጦርነት ክፍል አስገብቶ እርሱ ግን ጽኑ በሆነው የጠላት ኃይል መሐል ሰንጥቆ ይገባል።

ያ በእግሮቹ መቆም ትጥቁን እንኳን መታጠቅ ያቃተው የነበር ህሙም ንጉሥ በእጁ ጦር ወርውሮ በአንዴ ሁለት የጠላት ወታደር ደራርቦ ይጥላል። ግራ እና ቀኝ እጁን እያፈራረቀ እስኪደክመው ጠላትን ያጭዳል። በአንድ ጉድጓድም የጠላት ክምር ይጨምራል። ምክንያቱም እርሱ "ማንም ማን በፀብ ጊዜ በፊቱ መቆምን የሚችል የሌለበት ከድሮ ዠምሮ ፀብን የተማረ ነውና"። እንግዲህ ይሄ ነው ዐምደ ጽዮን። ትልልቆችን ትንሽ የሚያደርግ፣ የኃያላን ኃያል፣ በፊቱ በጽናት ሊቆም የሚችል የሌለ፣ አሸናፊነት ዕጣ ክፍሉ የሆነ ንጉሥ። ከርሱ ቀድመው ከነበሩ ነገሥታት ከርሱ ኋላም ከሚመጡ ነገሥታት ብልጫ ያለው ተወዳዳሪ የሌለው ንጉሥ መሆኑን መስበክ ማውጅ ነው የተራኪው አላማ።

> እንደዚህም ያለ ነገር በሌሎች ነገሥት ዘንድ አልተረደገም አልተሰማም። አባቶቻችንም አላወሩልንም፣ የቀደሙን ሽማግሎዎችም አልነገሩንም አልሰማንም አላየንምም እኛም ብንሆን አባቶቻችንም ቢሆኑ። ንጉሥም በቀኝ ያሉን ከጨረሳቸው በኋላ በግራ በኩል ባሉ በኋላቸው መጣ። ነፋስ ትቢያን እንዲበትንም በተናቸው። ወንጀለኞችንም ገደላቸው ከቀኑ ሰዓት ከስድስተኛው ጊዜ ዠምሮም ፀሐይ እስኪገባ ድረስ ወንጀለኞችን ወጋቸው። ዕጁም ከመግደል ብዛት የተነሣ በሰው ደም ከጦሩ ጋር እስኪጣበቅ ድረስ ገደላቸው። ዕጁንም በኃይል ፈቱ (አስለቀቁ)። ጦሩንም ከዕጁ ወሰዱ። በዚያች ቀን የተደረገውን፣ በቀደሙ በኢትዮጵያ ነገሥትም ዘንድ ያልሆነውን ፀብ (ጦር) ደግሞ እነግራቸው ዘንድ አትንም ስሙኝ። (ገጽ 33 አጽንዖት ከራሴ)

የተራኪው ዋና ግብም ይህ ነው። ማንገስ፣ ማግነን፣ ከከፍታም ከፍ ያለውን የሰውነት ደረጃ ማቀዳጀት፤ ቀድሞ ያልተሰማ ገድል ማሰማት፣ ማወጅ። እንዲህም ለማድረግ የተሸናፊዎችን ስዕል ማሳነስ ሳይሆን ማግዘፍን እንደስልት ተጠቅሟል። ዐምደ ጽዮን አሸናፊ የሚሆነው ከርሱ ካነሰ ጋር ተጋድሎ ሳይሆን ከላቀ ጋር ተጋጥሞ ነው። እንደውም ከአቻው ጋር ብቻ ሳይሆን በጊዜው ምናልባት ከሚበልጡት ኃይላት ጋር ነው የሚዋጋው። ይሔንንም ምስክርነት የሚሰጡት ወዳጆቹ ብቻ እንዲሆኑ አይፈቅድም ተራኪው፤ ጠላቶቹም እንጂ።

ከዚህ ጦርነት በኋላ በተደረጉ ሌሎች ጦርነቶች ውስጥ የተማረኩ የአዳል ንጉሥ ልጆችና የንጉሡ ወንድም እንዲህ ይተርካሉ፡፡

> የአዳል ንጉሥም ልጆች እንዲህ አሉ፣ ንጉሥ ሆይ ስማ ምድራችንና እኛን ከእግዚአብሔር ብቻ በቀር የሚገዛ አልነበረም፡፡ የሚችለንም ማንም ማን አልነበረም (አንተም ወደኛ የመጣኽበትን ጊዜ የሠርግ ጊዜ ደስታን አስመስልነ)፡፡ አንተም ወደ እኛ የመጣኽበት ጊዜ በሠርግ በጫጉላ ደሥ የሚለው ሰውን አስመሰለን፡፡ እናንተም ፀብን የተማራችት ወንዶች እንደኾናችት አላወቅናችኹም ነበረ፡፡ ትንሽም የወንድ ብልት (ቁላ) በእናንተ ዘንድ እንዳለም አላደረግናችኹም፡፡ የክርስቲያን ገንዘብ ይበቃናልን፣ እኛ እንደ ባሕር አሸዋና እንደ ሰማይ ከዋክብት የበዛን ነንና አልነ እንጅ፡፡ አንተንና ሠራዊትኽንም ከዕጻችን በታች አድርገን ነበር፡፡
>
> አንተንም ብቻ የማንፈራ አይደለንም፡፡ የምድር ነገሥትም ጉላቸው ከምድር ዳርቻዎች ዠምረው እስከ ምድር ዳርቻዎች ድረስ ቢመጡ ባልፈራንም ነበረ እንጅ፡፡ በወጋናቸውም ነበረ እንገር፡፡ በፀብ ጊዜ በፊታችን መቆምን የሚችል የለምና፡፡ እኛንም ድል መንሣት የሚችል (የቻለ) ማንም ማን ያላንተ የለምና ንጉሥ ሆይ ቁጣኽንም አሁን ተው ንጉሥ ሆይ ፈጽመኽም አታጥፋን፡፡ እኛ ያዘዝኽንን ጉሉ እናደርጋለንና አሉ፡፡ (ገጽ 40-41፣ አጽንዖት ከራሴ)

በግልጽ እንደሚታየው እና ጠላቶች እንደሚመሰክሩለት እነሱ የኃያላን ኃያል ሲሆኑ እሱ ግን እነሱን ሳይቀር የረታ ያሸነፈ ትልቁ ኃያል ነው፡፡ ስለዚህ ዐምደ ጽዮን ከትንንሽ ጠላት ጋር አይደለም ግብ ግቡ፤ ጠላቶቹ ትልልቅ ናቸው፡፡ ያኔ ነው አሸናፊ መሆኑ የሚታወቀው፡፡ ይህ የዐምደ ጽዮንን ተፋላሚ አልቆና አግዝፎ የማሳየት ሒደት ዐምደ ጽዮንን የኃያላን ኃያል ተደርጎ እንዲታሰብ አስችሎታል፡፡

#### 3.1.3.2 ሰማያዊ ብጽዕና ማኅናጸፍ

በዚህ ክፍል ውስጥ በቀጥታ ወደ ትንተና ከመግባታችን በፊት አስቀድመን ሰማያዊ ብጽዕናን ማኅናጸፍ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ እንመልከት፡፡ በዚህ ጥናት 'ሰማያዊ ብጽዕና' ስንል ባለታሪኩ እንደሰው በምድር የኖረ ሆኖ ሳለ ለሚያደርጋቸውና ለሚሆናቸው እንዲሁም ለማንነቱ ሳይቀር መለኮታዊ ፍቃድ ያለው፤ እንዲሁም ከመለኮት የተቀባና በመለኮት ጥላና ጥበቃ የሚኖር፣ እርሱም /ባለታሪኩ/ መለኮት ከርሱ ጋር እንዲኖር የሚያስችል ምግባር ከሃይማኖት ያስተባበረ አድርጎ ማሳየትን ነው፡፡

ተራኪው ይሔን ባሕርይ ለባለታሪኩ ለማጎናጸፍ በተለያየ መልኩ ሲጥር እንመለከታለን። አንዳንዴ በቀጥታው መንገድ ይሔንኑ አላማውን ሲሰብክ የምናገኘው ሲሆን አንዳንዴ ደግሞ በንጉሡ ድርጊትና ክንውን ውስጥ የመለኮትን ድርሻ በማሳየት የንጉሡን ብጽዕና ሊነግረን ይሞክራል። በየትኛውም መንገድ ቢሆን ሊነግረን የሚፈልገው ቁም ነገር ባለታሪኩ በምድር የአምላክ ወኪል እንደራሴ እና የቅድስናው መገለጫ እንደሆነ ነው።

በዜና መዋዕሉ ውስጥ በጉልህ ሰፍሮ የምናገኘው የጦርነት እና የግጭቶች ምክንያት ሃይማኖት ሆኖ ይታያል። በሥልጣን እና በግዛት የሚነሱት ጦርነቶች እና ትግሎች እንኳን ሳይቀሩ መታገጊያ የሚያደርጉት ሃይማኖትን ሆኖ እናገኘዋለን። በአንዳንዶቹም ላይ ሁለቱም ማለትም የሃይማኖትና የስልጣን ግጭቶች ሲነሱ ተራኪው ከስልጣን ጥያቄው ይልቅ የሃይማኖቱን እሰጥ አገባ አጉልቶ ለማሳየት ይታገላል።

ከዚህ አይነት ትረካዎች ውስጥ በዜና መዋዕሉ የመጀመሪያ የትርክት ክፍል የምናገኘው የሰብረዲን የአመጽ ታሪክ ልናነሳ እንችላለን። የሰብረዲን የአመጽ ምክንያት ከሃይማኖቱ ባላነሰ እንደውም በላቀ ደረጃ የግዛት እና የስልጣን ጥያቄ ሆኖ እናገኘዋለን (ገጽ 1)።

ተራኪው ይሔንን የስልጣን ተገዳዳሪ አብዛኛውን ጊዜ በተረኩ ውስጥ ሲያነሳው እግዚአብሔርን የካደ፣ በወልድ አዳኝነት የማያምን፣ እንደ ሰይጣን በትዕቢት የተወጠረ በሚል ፍረጃ ውስጥ ሲከተው ነው የምናየው። ስለዚህም እንዲህ አድርጎ የዐምደ ጽዮን የሥልጣን ትግል ለሃይማኖት ከመታገል ጋር አንድ እንደሆነ ያስቀምጣል

> እርሱም ቅሉ ለፀብ ተዘጋጀ ንጉሥ ወደ አለበት ወደሸዋ ምድር ሊሄድ፣ የባርያ ባርያ ወደ አለቆች አለቃ፣ የውሻ ኹራት ወደ አንበሳ ራስ ሊወጣ ተዘጋጀ። የክርስቲያን መንግሥት እንደ አለቀ እንደ ተፈጸመ በማይታመን ነገር አምኖ ሊዘምት ተዘጋጀ። እኛ ግን ሰምተናል ከቅዱሳት መፃህፍትም (ተመልክተን) የተነሳ አውቀናል፣ አወን ማለትንና የለም ማለትን ያልኾን ማለት እውነትና ሐሰት ያልተቀላቀለበትን የታመነ ነገርን እንናገራለን የእስላሞች መንግሥትም ጥቂት እንደኾነ እንናገራለን። ያውም በጊዜው ጊዜ የሚሻር የሚጠፋ ሰባት መቶ ዓመት እንደኾን እንናገራለን።
>
> የክርስቲያን መንግሥት ግን የእግዚአብሔር ልጅ ዳግም መምጣት እስኪኾን ድረስ ጸንታ ትኖራለች ቅዱሳት መጻሕፍት እንደተናገሩ። ይልቁንም የኢትዮጵያ መንግሥት እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ ትኖራለች። ኢትዮጵያ ዕጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ታደርሳለች ብሎ ዳዊት ስለእርስዋ ትንቢት የተናገረላት ናትና ።
>
> (ገጽ6)

ይልና ሰብረዲን ይሔንን አምላካዊ ቃል ሊገረስስ ሊገነድስ የመጣ መሆኑን ነግሮን በአንጻሩ ደግሞ ዐምደ ጽዮን ይህን አምላካዊ ቃል ሊያስጠብቅ እንደሚጋደል ይተርክልናል። የዚህ አይነት ጥግና ጥግ የያዘ ፍረጃ በዚህም ትግል ውስጥ በአሸናፊነት የሚወጣው ኃይልን ለአምላክ የተገዛ በአምላክ የተቀባ አድርጎ ማሳየት ነው። በዚህም መሰረት የዐምደ ጽዮን ትምክህቱም አሸናፊነቱም በትህትና አንጂ ባለው የፈረስና የሠራዊት ብዛት እንዳልሆነ የድሉ ባለቤት እና ሰጪ ደግሞ አምላክ እንደሆነ በማስተባበር በመለኮትና በምድራዊው ንጉሥ መካከል ያለን መተሳሰር አጽንቶ እንዲህ ይተርክልናል።

> በፈረሶቹም ብዛት የሚታመን አይደለም በሠራዊቱም ብዛት የሚታመን አይደለም በቀስትም ቢኾን በጦርም ቢኾን የሚታመን አይደለም። ዳዊት እንዳለ ንጉሥ በሠራዊት ብዛት አይድንም። ፈረስም ሐሰት ነው አያድንም። በቀስቴ የምታመን አይደለኹም (እንዳለ)። ዐምደ ጽዮንም እንደ እርሱ በብዙ አይታመንም በጥቂቱም አይፈራም ሃይማኖቱን (እምነቱን) በፈጣሪው በእግዚአብሔር ላይ ያደርጋል እንጅ። ሠራዊቱ ግን ንጉሣቸውን እየፈለጉት ከዱር ወደዱር ዞሩ (ተንከራተቱ)። (ገጽ 9፣ አጽንዖት ከራሴ)

እንግዲህ በዚህ መልክ የተተረከለትን ባለታሪክ የመንፈሳዊነት ደረጃ ልንገምት እንችላለን። በሠራዊቱ ብዛት አለመታመኑንም ደጋግሞ ከላይ በልዕለ ሰብዕ ማግዘፍ ርዕስ ስር ባነሳነው መሰረት አሳይቶናል። በአስቸጋሪ የጦርነት ጊዜ ያለውን ጠንካራ ሠራዊትን ካጠገቡ በማራቅ፣ በዕጁ ያለውን ደግሞ ደካማና ፈሪ በማድረግ ወይም እነሱን በቀለለው እርሱ ግን በከበደው የጦርነት አውድማ ውስጥ ዘሎ በመግባት ይህንኑ አረጋግጦልናል። ይህ መንፈሳዊነት ሲገፋና ጫን ሲልም ንጉሡ በምድር የእግዚአብሔርን ሥርዐት ጠባቂም ብቻ ሳይሆን አስጠባቂ ሆኖ ይገለጻል። የሚክዱትን የሚያስተምር ብቻ ሳይሆን ቀጪም ሆኖ ይመጣል። ይሄ የብቃት ደረጃ ደግሞ ለማንም አማኝ እና እና ሰባኪ የሚሰጥ ሥልጣን አይደለም። ማስተማርን ለሁሉ /ለአገልጋዮች/ ሲሰጥ የመፍረድና የመቅጣት ጸጋ ግን የአምላክ ድርሻ ብቻ ነው። እናም ተራኪው 'ስለራሱ አይደለም ስለክርስቶስ ህግ ቀንቶ እንጂ' ብሎ የመቅጣቱን ምክንያት ያስረዳናል። ቀጣዩን አስረጅ እንመልከት

> እነዚህን ወደ ከሃድያን አውራጃ ሰደደ። እንደ ሰቃዮች አይሁድ ከሚመስሉ ሰሜን ወገራ ጸለምት ጸገዴ ከሚባሉ ጋራ ይጣሉ (ይዋጉ) ዘንድ። እነሱ ድሮ ክርስቲያን ነበሩ። ዛሬ ግን እንደ ስቃዮች እንደ አይሁድ ክርስቶስን ካዱ። ስለዚህም አፍርሰው (ዘርፈው) ያጠፉአቸው ዘንድ ሰደዳቸው። ይኸውም ለክርስቶስ ሕግ ቀንቶ ነው። ሌሎችንም የቀንጸልባ መኳንንትንና የዋግ ሹምን የዳኅና ሹምንም የሰሐርት ሹምንም ክበብንም የተዋዘት መካከልንም የባሕር መካከልንም ሰደደ። ስሙ ንድጎን ከተባለ ከ1 ወንጀለኛ ጋራ ይዋጉ ዘንድ። (ገጽ 8፣ አጽንዖት ከራሴ)

በመሆኑም ዐምደ ጽዮንን ተራኪው እንደ ተራ አማኝ አሊያም እንደተራ ሰባኪ ብቻ አይደለም ሊያሳየን የሚሞክረው፡፡ ይልቁንም በአምላክ አንጻር ቆሞ የመለኮትን ፍትህ የሚሰጥ ስለአምላክ ቀንቶ የሚቀጣ የሚገድል አድርጎ ጭምር እንጂ፡፡

ይህ ለአምላክ ቀናተኛ ንጉሥ እሱም ቢሆን ከጦርነት በፊት ካህናትን በጸሎት የሚያማልድ፣ እርሱም የሚጸልይና የሚሰግድ ከድሉም በኋላ ለአምላኩ ምስጋናን እና ውዳሴን የሚሰጥ እንደሆነ ደጋግመን እናያለን፡፡ አንዳንዴም በመከራ እና በሽብር ውስጥ እያለም ቢሆን ስለራሱ መከራና መሸበር ሳይሆን ስለህዝቡ መዳንና መትረፍ የሚማልድ ብጹዕ እንደሆነ ተራኪው ያረጋግጥልናል፡፡ "እኔን ግን እንደ ወደድኸ አድርግ (አለ ብሎ) ስለ ራሱም ያይደለ ስለ ወገኖቹ እግዚአብሔርን ፈጽሞ ለመነ፡፡ ቸር ጠባቂ ቤዛ ኾኖ ስለ በጎቹ ፈንታ ሰውነቱን ለመከራ ይሰጣል ያለውንም የወንጌል ቃል ፈጸመ" (ገጽ 30) በማለት ምስክርነቱን ይሰጠናል፡፡ በዚህ አይነት ጸሎት እና ምልጃ ውስጥ ነው የዐምደ ጽዮንን መንፈሳዊ ብቃትና ልቀት የሚነግረን፡፡ በሌላም በኩል ተራኪው በቀጥታ የዐምደ ጽዮንን ንግግር በመጥቀስና በመተረክ በምን ያህል ደረጃ መንፈሳዊነት እንደነበረው ያስረዳል፡፡ ስለማን እንደሚጋደል ለምን እንደሚዋጋ ዐምደ ጽዮን በግልጽ ይናገራል፡፡

> አብን ከልጁና ከቅዱስ መንፈሱ ጋራ የምታውቁት፣ በስሙ የተጠመቃችሁ፣ በደሙ የከበራችሁ፣ እለአንተማ እንዴት (አትጨክኑ)፡፡ ወንጀለኞችን ለምን ትፈሩአችዋላችሁ፡፡ በኔ ምክንያት ስለመጋደል ድሮ ትጨክኑ ነበረ፡፡ በክርስቶስም ሃይማኖት ስለ መጋደል ዛሬ ጨክኑ ከወንጀለኞችና ከከሃድያን ጋራ በብረት ሰይፍ ተጋደል፡፡ ሰይፍኽንም በተፈጸመች ሃይማኖት ምክንያት ምዘዝ እንዳለ የሥርዐት መጽሐፍ፡፡ እናንተም አፋችኹን (ሰይፋችሁን) ታጠቁ፣ ልባችኹንም አስጨክኑ፡፡ (ነፍሳችሁንም) ልባችሁን አታስደንግጹ፡፡ ጽኑ እንጂ፤ በእግዚአብሔርም እመኑ እንጂ፡፡ ፺ኛው የመዝሙር መጽሐፍ እንዳለ በእግዚአብሔር አመንኹ ሰው ምን ያደርገኛል ብዬ አልፈራም፡፡ እግዚአብሔር ይረዳኛል እኔም ጠላቶቼን አያቸዋለሁ (ሲጠፉ)፡፡ ዳግመኛም እንዲህ እንዳለ አሕዛብ ኁሉ ከበውኝ ነበረ፣ በእግዚአብሔር ስም ድል ነሳኂቸው እንጂ (እንዳለ)፡፡ (ገጽ 16)

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ዐምደ ጽዮን ሠራዊቱን እያጸና ነው፡፡ ቀድሞ ስለኔ ትጋደሉ ነበር ዛሬ ግን ስለሃይማኖታችሁ ነው የምትጋደሉት ይላቸዋል፡፡ እርሱም የዚሁ እምነት አካል ሆኖ መጽሐፍ ይጠቅሳል፡፡ 'እኛ ብንሞትም በሕይወት ብንኖር ለእግዚአብሔር ነው (እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው)' ሲል ይሰብካል፡፡ በዚህም የርሱ ልብ 'በክርስቶስ እንደጸና የእናንተም ይጽና' ይላቸዋል፡፡ የእርሱንም እውነት እና አላማንም

በባህታዊ ራዕይ ያጸድቃል፣ ያረጋግጣል። የሚጋደለው የሚወድቅ የሚነሳው ለሃይማኖት ለእምነቱ እንደሆነ ይገልጽልናል። ተራኪው ይህንን ሲነግረን ፍላጎቱ ምንድን ነው? ዐምደ ጽዮንን በየትኛው የመመልከቻ መነጽር እድንመለከው ነው የፈለገው? እዚህ ላይ በግልጽ /ሌላ ፍካሬ ውስጥ እስካልገባን ድረስ/ ለመመልከት እንደቻልነው መልሱ ጥርጥር በሌለው መልኩ የመተረኪያውም የመመልከቻውም አቅጣጫ መንፈሳዊ ነው። ተረኩን የሚሰማም የሚያገኘው ጭብጥ ዐምደ ጽዮን መንፈሳዊ መሆኑን ነፍሱንም ሳያስቀር ለእምነቱ ለሃይማኖቱ አሳልፎ ለመስጠት የተዘጋጀ መሆኑን ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ዐምደ ጽዮን መንፈሳዊ ሥጦታውና ጸጋውን የበለጠ አግዝፎ የሚያሳየው የዜና መዋዕሉ ክፍል የመጨረሻው የአዳል ከፍተኛው ውጊያ ላይ ነው። ይህን ከላይ በልዕለ ሰብ ማግዘፍ ክፍል ላይ የተመለከትነው ሲሆን ዐምደ ጽዮን በታመመ በደከመ ከሠራዊቱም በተነጠለ ሰአት ያደረገውን ታላቅ ትግል በስፋት ይተርካል። ይህ የተረክ ክፍል እጅግ ገላጭ እና መሳጭ ሲሆን ተራኪው እግዚአብሔር በእገዛው ከንጉሡ ጋር እንደነበረ የሚያስረዳ ነው። ከሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሁለት ነገሥታት እና መኳንንት ሠራዊት ጋር በአንድ ጊዜ ጦርት የገጠመው በሽተኛው ዐምደ ጽዮን የድልና የማሸነፉ ምስጢር ሆኖ የሚቀርብልን የዮርዳኖስ ጸበልና የዮርዳኖስ አፈር /እምነት/ ነው። ህሙሙ ንጉሥ ኃይልን የሚጎናጸፈው አቅሙ የሚመለስለት ጸበሉን ከተጠመቀ በኋላ ነው። የርሱ ኃይል መልበስ ብቻ ሳይሆን ይሔው የዮርዳኖስ ጸበል የጠላቱንም ስረይ ያመክናል፤ ኃይላቸውን ያደክማል። ይህም ሁኔታ ድልን እንዲቀዳጅ ያደርገዋል። ይህንንም ድል ተራኪው እንዲህ ይገልጸዋል

> በዚያችም ቀን የተጋደሉ የወንጀለኞች ወገኖችን መቁጠር የሚችል ማንም ማን የለም። ጉሉን ከሚችል፣ የሚሳነውም ከሌለ ከእግዚአብሔር በቀር። ዐምደ ጽዮን ተጣላ ወይም (ተዋጋ) እግዚአብሔር አሸነፈ። ዐምደ ጸዮን በሥጋ ተወጋ እግዚአብሔርም በፀጋ ረዳት ሆነ። ዐምደ ጽዮን በፈረስ ላይ ተቀምጦ እግዚአብሔርም ህይወቱ መንፈስ ቅዱስን ሰጠ ኃይልም ሆነ። አመፀኞችንም ጨረሳቸው ሠራዊቱንም አዳነ። (ገጽ 34፣ አጽንዖት ከራሴ)

በመሆኑም የዐምደ ጽዮን ድል የአምላክ ድል ነው። ያም መሆኑ ዐምደ ጽዮን የእግዚአብሔር ፈቃድ መፈጸሚያ አሊያም እንደራሴ ነው ማለት እንችላለን። በዚህም ደረጃ ተራኪው ንጉሡን በመሳል መንፈሳዊ ብቃቱን እና ብጽዕናውን ይነግረናል። ይህም ብቻ ሳይሆን የዚህን መዳን የዚህን ጦርነት መጠናቀቅ ተራኪው እግዚአብሔር ከሰማይ የመውረድ ያኽል አድርጎ ይተርክልናል። "እግዚአብሔር ኃይሉን ከሚገልጽባቸው

ከመላዕክት በዚያች ቀን ሚካኤልንና ገብርኤልን ከሠራዊቶቻቸው ጋር አልሰደዳቸውም እኮን ይረዱን ዘንድ፡፡ እርሱ ቅሉ እግዚአብሔር ወረደ እንጂ ከወንጀለኞችም እጅም በቀኝ እጁ ኃይል አዳነን እንጂ (አለው ንጉሡን)" (ገጽ 38፣ አጽንዖት ከራሴ) እንግዲህ ከዚህ አንጻር ስንመረምር ቀኝ እጅ ሆኖ ተዋግቶ ያሸነፈና ባለድሉ ዐምደ ጽዮን ነው፡፡ ስለዚህም ዐምደ ጽዮን የኃያላን ኃያል ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር እንደራሴና ቀኝ እጅ የሆነ ብጹዕ መንፈሳዊም ጭምር ነው፤ እንደተራኪው ገለጻ፡፡

ተራኪው ከዚህ በዘለለ ብጽዕናውን ለማላቅ የንጉሡን መንፈሳዊነት እና ምግባረ በጎነት ደጋግሞ ይገልጻል፡፡ እንደነሙሴና ዳዊት ገርነቱን ትሁት፣ ፈራጅ፣ ታጋሽ፣ ሽማግሌዎችን እንዳባቱ፣ ጎልማሶችንም እንደ ወንድሙ፣ ባልቴቶችንም እንደእናቱ፣ ካህናትና መነኩሳትንም እንደጌታው እንደሚወድ ይነግረናል፡፡ በትሩፋቱም ራሱን ዝቅ ዝቅ እንደሚያደርግ፣ ለተቸገሩ ምጽዋትን እንደሚሰጥ፣ አብዝቶም ለአብያተ ክርስቲያናት መባዕ እንደሚያስገባ ይተርካል (ገጽ 46)፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው የባለታሪኩን የዐምደ ጽዮንን መንፈሳዊ ብጽዕና የሚያስረግጡልንን ጥቅሶችን ሲሆን ለንጉሥነቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያለው፣ በአኗኗሩ ውስጥም እግዚአብሔርን ማስደሰት የአምላክን ህግ ማስጠበቅ፣ የመለኮትን እርዳታ መቀበል እንዲሁም ማመስገን እና መማለድ በጉልህ በዜና መዋዕሉ ውስጥ እንዳለ አይተናል፡፡ የዚህ ሁሉ ዋንኛ ግቡ የዐምደ ጽዮንን መንፈሳዊ ብጽዕና አጉልቶ ማሳየት ነው፡፡

### 3.2 "የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" በይነ-ቴክስታዊነት

በዚህ የትንተና ክፍል ውስጥ የምመለከተው ዜና መዋዕላቱ በተለያዩ መልኮች ከሌሎች መጻሕፍት እና ጽሑፎች ጋር ይናበባሉ ወይም ግንኙነት ይፈጥራሉ የሚለውን ነጥብ ነው፡፡ ይህንንም ለመመልከት እንድንችል እንደጥናቱ አቅራቢ እምነት በይነ-ቴክስታዊነትን ፈጥረዋል ከተባሉ የመጻሕፍት (ጽሑፍ) አይነቶች መኃል ሁለቱን ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ እና ገድላትን በመነጠል እንመለከታለን፡፡ እኒህን ሁለቱን ለይተን የመረጥንበት ሁለት ምክንያቶች አሉ፡፡ አንደኛው በተለይ መጽሐፍ ቅዱስን በቀጥታ ዜና መዋዕሉ በግልጽ በመጥቀስ አሊያም በማልመድ የትረካው አካል አድርጎት የምንመለከት በመሆኑ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ገድላትን ቀደምት አጥኚዎች የዜና መዋዕላቱ ባህሪ ገድላዊ ነው ያሉባቸውን ምክንያቶች ለመመርመር የሚያስችሉ ማስረጃዎችን በዜና መዋዕሉ ውስጥ የትኞች ነጥቦች እንደሆኑ ለማሳየት የሚቻል በመሆኑ ነው፡፡

በነዚህ በተጠቀሱት የጽሑፍ አይነቶች ውስጥም እንደ አጥኚው እምነት በይነ-ቴክስታዊነት የተከሰተባቸውን መንገዶች እንዲያስረዱ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ከዜና መዋዕላቱ እና በይነ-ቴክስታዊነቱን ከፈጠሩት ጽሑፎች ጋር በማገናዘብ በንዑሳን ክፍልነት በመመደብ ለማስረዳት ይሞከራል፡፡

### 3.2.1 "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" በይነ-ቴክስታዊነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር

ዜና መዋዕላቱ በዋንኛነት በይነ-ቴክስታዊነትን ከሚፈጥሩባቸው መጽሐፍት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ አንዱና ግንባር ቀደሙ ነው ማለት እንችላለን፡፡ እንደውም "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ተረክ ዋንኛው የመባያ መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በይነ-ቴክስታዊነት ነው ማለቱ የተሻለ ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪኮችንና ጥቅሶችን በዜና መዋዕሉ ወስጥ በተለያዩ መንገዶች እናገኛቸዋለን፡፡

አንደኛው መንገድ በቀጥታ በተረኩ ውስጥ ለተተረከው ጉዳይ ማረጋገጫነት ወይም ማጽኛ ሆኖ የሚቀርብ ሲሆን ይሔም በቀጥታ ታሪኩን እና የመጽሐፍ ቅዱሱን ጥቅስ በመግለጽ ሲልም ምዕራፍ እና ቁጥሩን በመጥቀስ የሚገለጽ ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥም "ጠቃሽ በይነ-ቴክስታዊነት" በማለት መድበን እንመለከተዋለን፡፡

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ተረኩ በሚተረክበት ሰአት በምሳሌ ወይም በማናጸሪያነት አሊያም እንደዘይቤ የሚጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በዜና መዋዕላቱ ውስጥ ሌሎቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በይነ-ቴክስታዊነት የሚፈጠርባቸው አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ የዚህ አይነት በይነ-ቴክስታዊነት አረፍተ ነገሩን ለማስዋብ፣ ገለጻውን ለማጠንከር ወይም ስዕል ለመስጠት ሲባል ነው የሚመጡት፡፡ ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በይነ-ቴክስታዊነት ክፍል ደግሞ ታሪኩን ተንተርሶ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉን አስታከው የሚያነሱ ወይም በይነ-ቴክስታዊነትን የሚፈጥሩ በመሆኑ ለዚህ ትንተና "ማስታከክ" የሚል ስያሜን ሰጥቼ እተነትናቸዋለሁ፡፡

#### 3.2.1.1 መጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሽ በይነ-ቴክስታዊነት

"በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ላይ በይነ-ቴክስታዊነት የሚጀምረው ገና ዜና መዋዕሉ ትረካውን ለመጀመር በሚንደረደርበት የመግቢያው ክፍል ላይ ነው፡፡ "ጥበብን ያጣት ሰው ቢኖር በለጋስነት ለሁሉ ከሚሰጥ ከማይገዳደርም ከሰጭ እግዚአብሔር ዘንድ ይለምን፤ ብሎ ያዕቆብ ሐዋርያ እንደተናገረ፡፡" (ገጽ 1) የሚል አርፍተ ነገርን እናገኛለን፡፡ በዚህ ላይ በግልጽ እንደምንመለከተው በመግቢያው ክፍል ላይ ተራኪው ተረኩን ሲጽፍ የመለኮት እርዳታን ከተማጸነ በኋላ ይሔን መማለድ ያደረገበትን ምክንያት ለማስረገጥ የሐዋርያው ያዕቆብ

መልዕክትን በማንሳት ሐሳቡን ለማጽናት ይሞክራል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሐዋርያው የያዕቆብ መልዕክት 1÷5 ላይ የምናገኘው ነው። ስለሆነም ተራኪው ምንጩን ጠቅሶ ቃሉን በማስረጃነት ያስቀመጠው በመሆኑ አሻሚነት ሳይኖር ከሌላ ጸሑፋዊ ምንጭ ተወስዶ መግባቱ በእርግጠኝነት የሚታይ ነጥብ ነው። በመሆኑም ዜና መዋዕሉን ከመግቢያው አንስቶ ባለው አጠቃላይ አካሉ ላይ በይነ-ቴክስታዊነትን መፍጠሩን ከሚያስረዱልን ነጥቦች መካከል አንዱ አድርገን ልንወስደው እንችላለን።

ከዚህ በሰፋ ሁኔታ በዋናው ተረክ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚናበቡ ትረካዎችን በማስረጃት /በማጽኛነት/ በበርካታ የዜና መዋዕሉ ክፍሎች ውስጥ ተጠቅሞ እናገኛለን። ተራኪው በነዚህ አይነት መጽሐፍ ቅዱስን እርሱ ላነሳቸው ሀሳቦች በማረጋገጫነት በሚጠቅስበት ጊዜ ከላይ እንዳየነው በቀጥታ የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል ብቻ ሳይሆን የሚያመላክተው ከመጽሐፍ ውስጥም የትኛው ስፍራ ላይ ወይም የትኛው ጸሐፊ እንደጻፈው ጨምሮ የሚያነሳበት አጋጣሚ እናገኛለን። በዚህ ሁኔታ በዜና መዋዕሉ ከተጠቀሱ መካከል "ኢትዮጵያ ዕጆቿዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ብሎ ዳዊት ስለእርስዋ ትንቢት የተናገረላት ናትና" (ገጽ 6) ሲል ያነሳውን ልንመለከት እንችላለን። በዚህ ተረክ ውስጥ ይሔንን የዳዊትን አባባል እንዲያነሳ ያስገደደው ነጥብ የዐምደ ጽዮን ተቃዋሚ የክርስቲያን መንግሥትን ሲያጠፋ የሚፈልግ እንደሆነ ከነገረን በኋላ ሆኖም የኢትዮጵያ መንግሥት አይጠፋም ለሚለው እንደማስረጃ ያቀረበው ነው። ለተራኪው ክርስቲያን ማለት ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያ ማለት ክርስቲያን ብሎ የሚያስብ መስሎ ይሰማናል። በቀጥታ ይሔ እንደማስረጃ የተጠቀሰው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል መዝ. ዳ 68÷31 ላይ የሚገኝ ነው። በመሆኑም ተራኪው ቃሉን ሲጠቅስ የማን መሆኑን በማሳወቅ ጭምር ነው።

በተመሳሳይ ዳዊትን ጠቅሶ "ዳዊት እንዳለ ንጉሥ በሠራዊት ብዛት አይድንም። ፈረስም ሀሰት ነው አያድንም። በቀስቴ የምታመን አይደለሁም (እንዳለ)። ዐምደ ጽዮንም እንደ እርሱ በብዙም አይታመንም፤ በጥቂትም አይፈራም" (ገጽ 9)። የዐምደ ጽዮንን ሰብዕና ሲነግረን በማስረጃነት ይሔንን ኃይለ-ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝ. ዳ. 20 ÷7 ይጠቅሳል። ሰብዕናውን መጥቀስ ያስፈለገው ግን ለዚህ ብቻ አይደለም። ጥቅሱ በስፈረበት ተረክ ውስጥ ዐምደ ጽዮን የሐድያውን ንጉሥ ሊወጋ ሲያስብ የነበሩትን ሠራዊቶች ሁሉ ትቶ በድብቅ ብቻውን ታላቅ ጀብድ ሰርቶ ከመጣ በኋላ ነው። ለዚህም ድርጊቱ እንዴት የሚል ጠያቂ ቢመጣ መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሶ ዳዊት እንዲህ ብሏል ምን ይደንቃል ለማለት ይመስላል። በዚህም መሰረት ተራኪው እኛ ዐምደ ጽዮንን እንድንመለከተው የሚጋብዘን ከዳዊት በአቻነት ነው። ምክንያቱም ዳዊት እንደቃሉ ነውና ዐምደ ጽዮንም እንደሱ በብዙም አይታመንም፤ በጥቂትም አይፈራም ብሎ የባህሪ አንድነትን ስለሚያጎናጽፈው።

ከዚህ በዘለለ በዜና መዋዕሉ ውስጥ በተለያየ መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በቀጥታ ተጠቅሶ በይነ-ቴክስታዊነትን የፈጠሩ ተረኮች እና ምንባቦችን እናገኛለን። እነዚህ ምንባቦች በጠቅላላ ለቀረበው ተረክ አባባል ወይም አኳኋን በማስረጃነት በቀጥታ ጸሐፊዎቹን በመጥቀስ አሊያም ከሌላ የጽሑፍ አካል መወሰዳቸውን አመላክተው ተጠቅሰው የሚመጡ ገጸ-ንባባት ናቸው። (ገጽ 7፣ 11፣12፣ 16፣ 28፣ 29፣ 34) ስለዚህም በይነ-ቴክስታዊነትን በጉልህ በመጥቀስ መፍጠራቸውን መመልከት እንችላለን።

3.2.1.2 መጽሐፍ ቅዱስን የማስታከክ በይነ-ቴክስታዊነት

ተራኪው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮችን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን ምስል ለመከሰቻ፣ ለማነጻጸሪያ፣ በዜና መዋዕሉ ውስጥ የሚተረከውን ተረክ ለማጉላት የሚጠቀምበት ነው። በአጠቃቀም ወቅትም በቀጥታ ምንጩን ሊጠቅስም ላይጠቅስም ይችላል። ሆኖም የሚያነሳቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ወይም ጥቅሶችን የሚያውቅ አንባቢ በቀላሉ ከየትኛው ታሪክ ጋር እንደሚገናኙ መረዳት የሚችል ሲሆን ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስን የማያውቅም ቢሆን ደግሞ በዘይቤ አገላለጽ ከሌላ ታሪክ ውስጥ ተስበው መግባታቸውን ለመረዳት ያን ያህል የሚከብዱ አይደሉም።

በዚህ መልኩ በይነ-ቴክስታዊነትን በሚፈጠሩ የተረኩ ክፍሎች ውስጥ የሚጠቀሱት ጥቅሶች ለባለታሪኩ /ለዐምደ ጽዮን/ እንዲሁም ለተቃዋሚዎቹም መግለጫ ሆነው ነው እንዲቀርቡ የሚደረጉት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጥፋት እና በትእቢት የተነሱ የውድቀት ታሪኮችን ለዐምደ ጽዮን ተቀናቃኞች እንዲሁም በአወንታዊ ደረጃ የሚጠቀሱ ታሪኮችን በአብዛኛው ለባለታሪኩ የመጥቀስ ዝንባሌን በግልጽ እንመለከታለን። ይሔም የተራኪው መሰረታዊ የትረካ አላማን ተንተርሶ የሚከናወን በመሆኑ ዋነኛው የመባያ መንገዱ መሆኑን እንረዳለን።

በዚህ መሰረትም ዐምደ ጽዮንን ከሙሴ (ገጽ 34፣36)፣ ከሶምሶን (ገጽ 5)፣ ከዳዊት (ገጽ 5፣31)፣ ከሚካኤል (ገጽ 38)፣ ከገብርኤል (ገጽ 38)፣ ከኢየሱስ (ገጽ 30፣38) ጋር ሲነጻጸር ሲወዳደር እናያለን። በአንጻሩ ደግሞ የዐምደ ጽዮን ተጻጻራሪ ሆነው የሚመጡትን ደግሞ በአሳች ነቢይ (ገጽ 5)፣ አይሁድ (ገጽ 8)፣ ፈርኦን (ገጽ 24)፣ ሰናክሬም (ገጽ 25) በመመሰል ወይም በማነጻጸር ይገልጻቸዋል።

ካነሳነውና ከምንተነትነው ነጥብ አንጻርም ከላይ የተመለከትናቸው የመመሰያ መንገዶች በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ላይ የሚመሰረቱ እና የሚያስታክኩ በመሆኑ በይነ-

ቴክስታዊነት እንዳላቸው እናምናለን። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በምን አይነት መንገድ ታሪክን ከታሪክ ጋር ተራኪው እንደሚያስተሳስር አንድ ምሳሌ እንመለከት።

> እግዚአብሔር ለገብረ መስቀል ያደረገው ድንቅ ሥራ ልዩ ነው። በሙሴ ቀኝ እጅ ግብፅን በባህር ውስጥ አሰጠማቸው። በገብረ መስቀልም ዕጆች ወንጀለኞችን በምድር ውስጥ አሰጠማቸው። ለሙሴና ለእስራኤል ደመናን ጋረደላቸው። ግብፅንም በማየት እንዳይፈሩ ሰወራቸው። ገብረ መስቀልና ሠራዊቱንም በታላቅ ተራራና (እንደ መጋረጃ) መጋረጃ አምሳል ሰወራቸው። ወንጀለኞችን በማየት እንዳይፈሩ። ወንጀለኞች ግን በዚያ ተራራ በቀኝ በኩል መጡ። እርስ በእርሳቸውም አልተያዩም። (ገጽ 36)

ይህን ተረክ የምናገኝበት የተረኩ ስፍራ በዜና መዋዕሉ ውስጥ ከተደረጉት ትልቁ ጦርነቶች መካከል ስለአዳሉ ጦርነት እና ድል የሚተርከው ክፍል ነው። በተረኩ ላይ እንደምናየው ዐምደ ጽዮን እንደሙሴ ህዝቡን በአዳል በረሃ ይዞ የሚጓዝ አለቃ ነው። በዚህ በረሀ ውስጥ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ሰዓት በሚነሳ ጦርነት ውስጥ ዐምደ ጽዮን የኤርትራን ባህር ከፍሎ እስራኤልን እንዳወጣ እንደሙሴ ያለ ባህሪን ይጎናጸፋል። አምሳለ ሙሴነቱን ሲያረጋግጥም ሙሴ በባህር ውስጥ ፈርዖንና ሠራዊትን ሲያሰጥማቸው ዐምደ ጽዮን ደግሞ በበርሐ አሸዋ ውስጥ ጠላቶቹን ያሰጥማል። ሙሴ በደመና ሲጋረድ ዐምደ ጽዮን በተራራ ይጋረዳል። የሙሴ ታሪክን ከዘጸአት 14÷16-31 ወስዶ ከርሱ ንጉሥ ገጠመኝ ጋር ያቆላልፈዋል።

እንግዲህ በዚህ መልኩ ነው በቀደመው ታዋቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ መደገፊያነት ምስልን ከስቶ ለማስረዳት ተራኪው የሚደክመው። ለማስረዳት ብቻ ግን አይደለም የዐምደ ጽዮንንም ትክክለኛ መደብን ለማሳወቅ ጭምር እንጂ። እንደው ተራ ተርታ ሳይሆን ቦታው ከነሙሴ ከነዳዊት ወገን ነው ለማለትም ጭምር ነው ማመሳሰል ማወዳደሩን የሚያከናውነው።

### 3.2.2 በይነ-ቴክስታዊነት ከገድላት ጋር

በዚህ ክፍል ከዚህ ቀደም የነበሩ አጥኚዎች ዜና መዋዕላቱ ገድላዊ ባህሪ አለባቸው ሲሉ ወደዚህ መዳረሻ ሊያንደረድሯቸው የሚችሉት ነጥቦች ምንድን ናቸው? የሚለውን ነጥብ እንመረምራለን። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ዜና መዋዕላቱ ከገድላቱ ጋር ያላቸው አግድሞሻዊ /አውዳዊ/ በይነ-ቴክስታዊነት ነው። ምክንያቱም ሁለቱም አንዱ ከአንዱ የሚገለብጡ ሳይሆን በዘመን የተቀራረቡ በመሆናቸው የመተረኪያ እና የመባያ መንገዶቻቸውን የሚጋሩ ዘመነኞች ናቸውና። በሌላም መንገድ ሁለቱም ቀጥተኛውን በይነ-

### 3.2.2.1.1 አጀማመር በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል

የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ተረኩ የሚጀምረው በዚህ መልክ ነው። ይህን የአጀማመር መንገድ በማየት ፋይዳዎቹን እና መሰል ጉዳዮችን ለመመርመር እንሞክር።

> ለኢትዮጵያ በነገሠ የመንግሥቱም ስም ገብረ መስቀል በተባለ፣ በዐምደ ጽዮን ዕጀች፣ በዐስራስምንተኛው ዓመተ መንግሥቱ በ517 (በሺህ ሦስት መቶ አስራ አምስት) ዓመተ ምህረት እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ሃይልንና ድንቅ ሥራን ማቸነፍንም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አጋዥነት እንጽፋለን። (ወይም ይህንን መጽሐፍ በሺህ ሶስት መቶ አስራ አምስት ዓመተ ምህረት እንጽፋለን)። የሚረዳ አብንና የሚያረጋጋ ወልድን የሚመራ መንፈስ ቅዱስንም አምነን። ከልዩ ሦስት (ሦስትነት ካጸናችላቸው አካላት) አጋዥነትን እየሻን። ጥበብን ያጣት ሰው ቢኖር በለጋስነት ለኑሉ ከሚሰጥ ከማይገዳደርም ከሰጭ እግዚአብሔር ዘንድ ይለምን፣ ብሎ ያዕቆብ ሐዋርያ እንደ ተናገረ። እኛም ከአብና ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስም ዘንድ አጋዥነትን እንሻ፣ ለዘለዓለሙ በእውነት ይረዳን ዘንድ (ገጽ 1)

ይህ የዜና መዋዕሉ መግቢያ መረጃዎችን ማለትም ባለታሪኩ ማን እንደሆነ እና ስለተጻፈበት ዘመን በሁለት የዘመን አቆጣጠር በማስረገጥ ይተርክልናል። አንደኛው የጊዜ መግለጫ መንገዱ ዓመተ ንግሥ ሲሆን ሁለተኛ መግለጫው ዓመተ ምህረት ነው። ተራኪው ስለምን በቀጥታ በአንዱ መጠቀም አልፈለገም ጊዜውንስ ለምን አነባብሮ በተለያየ መንገድ መጠቀስ አስፈለገው? ብለን መጠየቅ እንችላለን። ወይም በተለያየ አቅጣጫ ጊዜውን መግለጽ ለአጠቃላይ ለታሪኩ የሚያበረክተው ፋይዳ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት እንችላለን።

በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ሁለት አይነት አገላለጾች ቀጥታና አሻሚነት በሌለው መንገድ መቼነቱን ለማስረዳት ተራኪው የተጨነቀ መሆኑን በቅጡ ያስረዳሉ። ማለትም ተራኪው የታሪኩን ውስን መቼነት ለመግለጥ ተጠቅሞበታል ልንል እንችላለን። ሆኖም እንዲህ በማለት ብቻ ለተረኩ ያበረከቱትን አስተዋፅዖ መግለጽ አይበቃም። በሁለቱም የጊዜ አገላለጽ ተራኪው መግለጹ ቢያንስ ከመቼነቱ በዘለለ የባለታሪኩን ማህበራዊና ስነልቦናዊ ደረጃ መገመት እንድንችል እድል ሰጥቶናል። ይህ ማለት ዐምደ ጽዮን ከነገሠ በስንተኛው አመቱ የተጠቀሱትን አስገራሚ እና አስደናቂ የታሪክ ሂደቶች ውስጥ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች ተጋፈጠ? ወይም ባለታሪኩ ያጋጠሙትን ተግዳሮቶች ለመቋቋም የሚያስችል ልምድ ነበረው ወይ? በማለት ብንጠይቅ ለመልስ ማመላከቻ አሊያም በዘመኑ የነበረው ማህበረሰብ ስለሱ ሊኖረው ስለሚችለው ግምት እና ቦታ ፍንጭ ወይም መላምት እንድናገኝ

መንገድ ሊሰጠን ይችላል፡፡ በመሆኑም ተራኪው በመግቢያነት ካነሳቸው ጉዳዮች አንዱ ጊዜን መግለጽ ሲሆን ከላይ ላየናቸው ፋይዳዎች ሲውሉ በመቻሉ ጊዜን ከመግለጽ በላይ ለሆነ አላማ መግቢያውን ተጠቅሞበታል ለማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፤ ቦታ ቅድምና ሰጥቶ ካነሳቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ታሪኩ ወይም ባለታሪኩ የት ቦታ ነው ታሪኩን የሚጀምረው ለሚለው ተረካዊ ጥያቄ መልስ ሰጥቶ ነው የሚነሳው፡፡ ይሔም ከጊዜ ጋር በተዛማጅነት ሊመለስ የሚገባውን የየት ጥያቄን ይመልሳል፡፡ በመሆኑም መቼቱ ቁልጭ ባለ መልኩ በአጀማመር ክፍሉ ላይ እንደገለጸልን እንረዳለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ የመግቢያ ክፍሉ ላይ ተራኪው ተረኩን ሲጀምር ከሚነግረን ነገሮች መካከል የባለታሪኩ ማንነት አንዱ ነው፡፡ ማን ነው ባለታሪኩ? ለሚለው ዐምደ ጽዮን፤ የኢትዮጵያ ንጉሥ በማለት ማንነቱን እና ማኅበራዊ ደረጃውን ገልጾ ነው የሚንደረደረው፡፡

"የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ተረክ" በአጀማመሩ ላይ ካካተታቸው ጉዳዮች መካከል አጠቃላይ የተረኩ ምንነት አንዱ ነው፡፡ ይህም ማለት ዜና መዋዕሉ ሲጀምር ገና የባለታሪኩን ምን አይነት ታሪክ ሊተረክልን እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ይህንኑም በዐምደ ጽዮን ዕጆች እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎችን እና ማሸነፎችን ሊነግረን መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ስለዚህ መግቢያው ከላይ ያነሳናቸውን የጊዜ ቦታ እና ባለታሪክ /ገጸባህሪን/ ገለጻ ብቻ ሳይሆን የታሪኩን ምንነትንም አካቶ እንደሚይዝ ያሳየናል፡፡

ከዚህ በኋላ ደግሞ የጸሐፊውን ርዕዮተ ዓለም መመልከቻ መንገድ ከሆኑት ነጥቦች መካከል አንዱን ማለትም ስመ አምላክን በማንሳት እርሱንም በመስበክ በማመላከት ታሪኩን ይጀምራል፡፡ ይህም ለአንባቢ የተራኪውን ርዕዮተ ዓለም ከመጠቆም በተጨማሪ የመተረኪያው መባያ መንገድ እንግዳ እንዳይሆን ከወዲሁ ያመቻቸዋል፡፡ በሌላ አገላለጽ የመለኮታዊ እገዛና ምስክርነት ሲጀምር ታውጀና ተሰብኮ መጀመሩ በኋላም ተራኪው ለሚያነሳቸው አመክንዮች ከወዲሁ እንድንዘጋጅ ያደርገናል፡፡ ከላይ ያነሳናቸውን ነጥቦች ተንተርሰን የዜና መዋዕሉ የአጀማመር መንገድ በአጠቃላይ አምስት መሰረታዊ ነጥቦችን አካቶ እናገኛለን፡፡ ባለታሪኩን፣ ጊዜን፤ ቦታን፣ የተራኪውን ርዕዮተ ዓለምና የመባያ መንገዱን ጠቋሚ፡፡

### 3.2.2.1.2 የተረኩ ዋና አካል (ታሪክ) በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል

"የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" አተራረክን ስንመለከት በመግቢያው ላይ ያየናቸውን ጉዳዮች ካነሳ በኋላ በቀጥታ የሚሸጋገረው እጅግ ከፍ ወዳለ ግጭት /ጡዘት/

ነው። አስቀድሞም በመግቢያው ላይ ፍንጭ እንደሰጠን ከዐምደ ጽዮን ጦራዊ ገድል ወይም ማሸነፎች መካከል አንዱን በማንሳት ይተርክልናል። እዚህ ላይ ተራኪው የዐምደ ጽዮንን የህይወት ታሪክ ሊነግረን አይደለም የተነሳው። ስለዚህም ከመወለዱ ከማደጉ እና ከንግሥና አወጣጡ አንጻር የሚያነሳው ጉዳይ የለም። በመሆኑም ትኩረቱ ሁሉ ከላይ የገለጽነው ጦረኝነቱና ማሸነፉ ብቻ ነው። በታሪኩ ሂደት ውስጥ እንኳን በምልሰት የሚነግረን ታሪኮች የድል አድራጊነቱን ዜናዎች ብቻ ናቸው። ከዚህም በመነሳት አጠቃላይ የዜና መዋዕሉ ፍሬ ነገር አንድ ነገር ላይ ያተኮረ መሆኑን ልብ እንላለን።

ይህ የድል አድራጊነት ተረክ በሚተረክበት ወቅት ከአንድ መነሻ ታሪክ መጀመሩ ግድ ቢሆንም ተራኪው የመረጠው ንጉሡ ከነበረበት መናገሻ ካስወጣው የግጭት ታሪክ ነው። ባጠቃላይም ታሪኩ የሚያጠነጥነው አንጼ ሰብረዲንን ለመዋጋት የወጣ ንጉሥ በየሔደበት እየተጋደለ እያሸነፈ ደግሞ ሌላ ጦርት ውስጥ እየገባ ከዓመት በኋላ ተመልሶ ወደመናገሻ ከተማው ሲገባ ይጠናቀቃል።

ዜና መዋዕሉ በተረኩ ጊዜ የሚከተለው ሰንሰለት የምክንያትና ውጤት ትረካን ሳይሆን ጊዜን እና ገጠመኝን ትኩረት ያደረገ ነው። ይህ ሲባል ግን የምክንያትና ውጤት ጉዳዮች በተረኩ ሂደት ላይ ፈጽሞ የለም ማለት አይደለም። ሆኖም ተራኪው አስቀድሞ በመግቢያው ላይ እንዳወጀው የዐምደ ጽዮንን ተጋዳይነትና አሸናፊነት ሊነግረን ስለተነሳ የእያንዳንዱን ጦርነቶች ምክንያት ከመንገር በዘለለ የመጀመሪያው ጦርነት ለሚቀጥለው ጦርነት ምክንያት እንደሆነ ሲያስረዳ ወይም ሲያመካኝ አናገኘውም። ተረኩ ከአንዱ ግጭት ወደሚቀጥለው ግጭት ሲያመራ ሰንሰለታዊ ግንኙነቱ እና ትስስሩ የሳሳ ነው። ስለዚህም አጠቃላይ ታሪኩ ውስጥ የሚገኙት ግጭቶች በጊዜ ቅደም ተከተል እና በአጋጣሚዎች አወራረድ የሚተረኩ የተበጣጠሱ ታሪኮች ሆነው ይሰሙናል። ሁሉንም እንዲያያይዙ የሚያደርጉ ነጥቦች የንጉሡ ጉዞ እና የገዢነቱ ስልጣንን ለማረጋገጥ የሚያደርጋቸው ውጊያዎችና ቅጣቶች ናቸው።

ስለዚህም እማኝነት ከሰብረዲን ድል በኋላ ወደአዳል ምድር በሚጓዝበት ወቅት የሚያጋጥሙት ግጭቶች እንዲሁም የአዳሉ ጦርነት ከዛም በኋላ በመልስ ጉዞው ውስጥ የሚያጋጥሙት ግጭቶች እርስ በእርሳቸው አንዱ ለአንዱ ምክንያትና ውጤት ሲሆኑ አናይም። ሆኖም አንዱ የአንዱ ቅደም ተከተል መሆኑን በጥንቃቄ ተራኪው ሲተርክ እናስተውላለን። ስለዚህም የታሪኩ አደራደር አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ. . . በሚል አይነት ተደርድሮ እናገኛለን።

በሌላ በኩል በተወሰነ የተረኩ ክፍል ውስጥ ለማስረጃ እና ለተለየ አላማ በምልሰት የሚነሳ ታሪክ ይገኛል። ይህም ከላይ ያነሳውን የቅደም ተከተል አደራደር ላይ የሚኖር የተለይነት /exceptional/ ነው። ይህም ትርክት ዐፄ ዐምደ ጽዮን ከሰብረዲን ጋር ግጭት በገባበት ወቅት ለሰብረዲን ዘለፋ እና እንቢተኝነት ቁጣና ዛቻውን ሲገልጽ ወደኋላ መለስ ብሎ ከርሱ /ከሰብረዲን/ አስቀድሞ የነበሩትን የሰብረዲን ወገኖችን እንደምን አድርጎ ድል እንዳደረጋቸውና እንደቀጣቸው ታሪኩን ይተርካል። በዚህ ምልሰት ውስጥ የምናገኘው ተረክ የንጉሡን ባለድልነትና ኃያልነት የሚያስረዳ ነው። ከጊዜ አንጻር ታሪኩ የተተረከልን ሲሆን ምናልባት በሰብረዲን ልቆ መታየትና በዐምደ ጽዮን መካከል ያለውን የተቋቋሚነት ደረጃ ሚዛናዊ ለማድረግ ይችል ይሆናል። ከዚህ ውጪ ወደኋላ ተመልሶ የሚነግረን ነገር ብዙም አንመለከትም።

በሌላ በኩል አተራረኩ ከቅደም ተከተላዊ የታሪክ ጊዜ ውጪ ለታሪኮቹ መፈጠር መከናወን አነሳሽ ምክንያት ሆኖ ተደጋግሞ የሚነሳው አያያዥ ጉዳይ ሃይማኖት ነው። ነገር ግን የሁሉም ውጊያዎች መሰረታዊ ምክንያት ሃይማኖታዊ ይምሰል እንጂ በጥልቀት ስንመረምረው ግን በገዢዎችና በአፈንጋጮች መካከል የሚነሱ የስልጣን እና የጥቅም ግጭቶች ሆነው እናገኛቸዋለን።[9] ሆኖም ንጉሡ ግዛቱን ለማስጠበቅና የበላይነቱን ለማቆየት ሲጋደል የፖለቲካዊ አቋሙን ማንተራሻና መደገፊያ በማድረግ የቤተ-ክህነቱን ርዕዮት ይገለገላል። ተራኪውም የንጉሡን ኃያልነት በመደገፍ የርዕዮተ አለሙ መሰረት የሆነውን የቤተ-ክህነቱን አስተምህሮ በማግዘፍና የንጉሡን ድል የእምነቱ ድል በማድረግ ያስተሳስረዋል። በዚህም ላይ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤትን ትሩፋትን ጸሎትን እንዲሁም ስብከት እና ተአምራትን በተረኩ ውስጥ በማስገባት መታመንን ለማግኘት ይጥራል። ተራኪውም ይሔ መደጋገፍ እስከመጨረሻው የታሪኩ መቋጫ ድረስ በመቀጠል

---

[9] ጉዳዩ ሃይማኖት ላለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎችን ማንሳት የሚቻል ሲሆን ለማሳያ ያክል ዐምደ ጽዮን አምጸብኛል ብሎ የዘመተበትን ወይም የቀጣውን ሰው ከሥልጣኑ ካስወገደ በኋላ መልሶ በቦታው የአጥፊውን ወንድም ወይም ሌላ ሙስሊም ሲሾም እንጂ ከክርስቲያን ወገን ሲሾም ወይም እምነቱን ሲያስለውጥ አናይም፡፡ ለዚህም በሰብረዲን ፋንታ ወንድሙ ግማለዲን የብልዛቁር እስላም ንጉሥን አስወግዶ ወንድሙን ነስረዲንን ሲሾም እንመለከታለን፡፡ በግልጽም ሰብረዲን እጅ ሰጥቶ በንጉሥ ፊት በሚመረመርበት ጊዜ የተነሳበት ክስ እጅ መንሻዬን ከለከልክ (ግብር)፣ ነጋዴዎችን መንገድ ከለከልክ አሰርክ እና መንግሥቴን ለመቀማት አሰብክ የሚል ነበር፡፡ በሰብረዲን ምትክ የተሾመው ግማለዲንም ሆነ በአዳሉ ጦርነት የተሳተፉ የንጉሡ ወታደሮች የንጉሡ ተገዢ መሆናቸውን በማረጋገጥ በንግድ እና በግብር ግዴታቸውን ለመወጣት ቃል ሲገቡ እናስተውላለን፡፡ በመሆኑም የዘመቻውም አላማ ፖለቲካዊ እንጂ ሃይማኖታዊ አለመሆኑን ይበልጥ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በማሕበራዊ ማንነታቸው ያለው ክፍፍል ሁለት መሆኑ (እስላም እና ክርስቲያን) እንዲሁም ይህን ተንተርሶ የኃይል የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ፍትጊያዎች በተረኩ ውስጥ በጉልህ ይታያሉ፡፡ ይሔንን የማህበራዊ ክፍፍሉን ተንተርሶ ተራኪው በማህበራዊ መደቡ ማንነት ላይ ተመስርቶ እንዲሁም የራሱን ርዕዮት እና እውቀት ተንተርሶ የሚተርክ በመሆኑ የትግሉን አቅጣጫ ድንበር እያዘለለ ሲያቀላቅለው እናያለን፡፡ በሌላም በኩል በዚህ ዘመን በቤተ ክህነቱ እና ቤተ መንግሥቱ መካከል የነበረ ከፍተኛ የስርአት ፍጥጫን ስንመለከት (አምሳሉ1976፣ 55) በተረኩ ላይ የምናየው የግጭት ሁኔታ በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል ያለ ግጭት አለመሆኑን እናስተውላለን፡፡

ይቋጨዋል። በመሆኑም ይህን አጠቃላይ የትርክት መዋቅሩን ስንመለከት መውጣት መጋደል ባለድል መሆን መመለስን በዋነኝት የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን።

### 3.2.2.1.3 አፈጻጸም[10] በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል

"የዐጼ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ሲጠናቀቅ ተረኩን ሲጀምር ቃል የገባልንን የንጉሡን አሸናፊነት ታሪክ መንገሩን አረጋግጦልን ነው የሚዘጋው። እዚህ ላይ ታሪኩ አስቀድመን ለመግለጽ እንደሞከርነው ንጉሡ አንጼ ከሰብረዲን ጋር ለመዋጋት ከተጉለት ወጥቶ ግዛቴ ባለው ምድር ላይ በሐድያ አድርጎ ካመጸው ከሰብረዲን ጋር ተባብሯል ያለውን የዳውሮ ሹም ሓይደራን በማሰር በ"[ኦሮሞ]"[11] ሐገር አድርጎ የአዋሽ ባህርን በመሻገር ሞራ (ገሞራ) የምትባል ከተማን አልፎ ሌሎች ነገሥታት ወደማይደርሱበት ወደ አዳል በመጓዝ ከአዳል ንጉሥ ጋር በመዋጋት ድል ያደርጋል። ከዛም በመጣበት ሳይሆን በሌላ መንገድ እንደተለመደው እየተዋጋና እየቀጣ ዚባ፣ ተረክ፣ ዘስ፣ አበልጊ፣ ተለግ፣ መርጉብ፣ ዐራቴ፣ ብቁልዘር፣ ዋዝ፣ ድልሐያ፣ ደጉ አደርጎ ዳዋሮ ተመልሶ በመግባት በባህላ አቋርጦ ወደመናገሻ ከተማው ይመለስና ታሪኩን ይቋጫል። ሆኖም ዋናው ጉዳያችን ተረኩን እንደምን ባለ ሁኔታ ይፈጽማል የሚለው ነጥብ ነው። በዚህ ተረክ ውስጥ ተራኪው መጨረሹን የሚገልጽበት መንገድ አለው።

> በመዓልትና በሌሊት በእስላሞች ምድር ጉሉ በንጉሥና በሠራዊት ላይ ከተደረገው፣ ብዙ ኾኖ ይጻፍ ከነበረው ፀብ (ጦርነት) ጥቂቱን ተናገርን። አልጨመርንም ነገር እንዳይበዛ ለሚሰማውም ድንጋጤን እንዳይሆን።
>
> ንጉሥ ዐምደ ጽዮን ግን እንደ ሙሴና እንደ ዳዊት ገር ነው፣ ትሑት ነው፣ ፈራጅም ነው፣ ይቅር ባይም ነው፣ ዕጉሥ ነው፣ ሽማግሎችን እንደ አባቱ ይወዳል። ጎልማሶችንም እንደ ወንድሙ። ባልቴቶችንም እንደ እናቱ። ካህናትና መነኮሳትንም እንደ ጌታው ይወዳል። ንጉሥም ሲኾን ራሱን ለሁሉ እንደ ድሓ ያዋርዳል (ዝቅዝቅ ያደርጋል)። ምጽዋትንም ለድሖችና ለጾም ዐዳሮች ለባልቴቶችም ለሙት ልጆችም ይሰጣል። [. . .] ወርቅንና ብርንም ለአብያተ ክርስቲያን መግቢያ (መባእ) አድርጎ እንደ ደንግያ ይሰጣል። ልብሶችንም እንደ ቅጠል ይሰጣል።

---

[10] እዚህ ላይ አፈጻጸም ስል አከዋወን፣ አሰራር የሚለውን የትርጉም እንዳይዝብኝ ሰጋሁ። በመሆኑም አፈጻጸም ስል መጨረስ፣ ማጠናቀቅ ለሚለው ሀሳብ አቻነት የተጠቀምኩት መሆኑ ይታወቅልኝ።
[11] የዚህን ዘመን የአጠራር ስርአት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ በስሙ ላይ ለውጥ ተደርጎበታል።

እግዚአብሔርም በምድር ስለ ተፈጸመለት ስለ ኹነለት ነገር ኁሉ ፈንታ ሰማያዊ ክብርን ይስጠው፡፡ ዘመኑንም በምድር ላይ ያብዛ፡፡ ከድንገት ሞትም ያድነው፡፡ መንግሥተ ሰማያትንም ከቸሮች ነገሥት ጋር ለዘለዓለሙ ያውርሰው፡፡

ይችንም የጻፍኊት ኃጥእ በደለኛ የኾንኹ እኔን በጸሎታችኹ ጊዜ አትርሱኝ፡፡ እግዚአብሔር ከታናሻችኹ ዠምሮ እስከ ታላቆችኑ ድረስ ዘመናችኑን ያርዝም፡፡ ለአውራጃችሁም (ለወገናችሁም) ድኅነትንና ፍቅር አንድነትን ያድርግ፡፡ ንጉሣችኑም ኃይልንና ጠላቶቹን ድል መንሣትን ይስጠው፡፡ ለገዢቻችሁም በጎ ምክርን ይሰጥ (ይግለፅ)፡፡ ስለ እናንተ የክህነት ሥራን የሚሠራ (የሚያገለግል) የጳጳሳችሁን ጸሎት ይስማ፡፡ ለካህናታችሁም ንጽህናን ይስጣቸው፡፡ ለመነኮሳታችሁም ትዕግሥትን ይስጣቸው፡፡ ክብርንም ለሽማግሎቻችሁ፡፡ ማደግንም ለልጆቻችኑ፡፡ ፅናትንም ለጎልማሶቻችኑ፡፡ ክብርንና ሃይማኖትንም ለሴቶቻችኑ (ለባልቴቶቻችኑ)፡፡

መሠረትንና መዋቅርንም ለአብያተ ክርስቲያናችሁ ይስጣቸው፡፡ ብዛትንም ለድልባችሁ፡፡ መጠበቅንም ለመንጎቻችሁ ይስጣቸው፡፡ አምላክን በወለደች በእመቤታችን ፀሎትና ኃያላን በኾኑ በየስሞቻቸው በተጠሩ በመላእክት አለቆችና በመላእክት ፀሎት በሁላቸው በቅዱሳንና በሰማዕታትም ፀሎት ለዘለአለሙ በእውነት ይስጣቸው፡፡ አሜን (ገጽ 46 - 47)

ከላይ እንደተገለጸው ተራኪው የተነሳበትን አላማ መንገሩን እንደውም አጋኖ አለመጨመሩን ይልቁንም ለሰሚ በማሰብ እንደተወ በማስረዳት ንጉሡን ከጀግንነት ውጪ ያለውን ስነልቦናዊና ሞራላዊ ማንነቱን በአንድ አንቀጽ ይገልጣል፡፡ ቅድስናውን ካወጀ ካብራራ በኂላ ባለታሪኩን አስቀድሞ ይመርቃል፡፡ በመቀጠልም ለራሱ ጸሎት እንዲደረግለት ይለምናል፡፡ ከዛም ምርቃን ከህዝብ እስከካህናትና ቤተ-ክርስቲያናት ድረስ ከመረቀ በኂላ በምልጃ ትረካውን ይጨርሳል፡፡

እንግዲህ እነዚህ በመዝጊያነት የተጠቀመባቸው ታሪክን ማጽናት፣ ባለታሪክን ማድመቅና መመረቅ፣ ለራስ ለህዝብ ለቤተ-ክርስቲያን መጸለይና መማለድ ለተራኪያችን 'የመጣሁበትን አላማ ጨርሻለሁ ስለዚህ እንለያይ' የማለት ያክል መሰናበቻ ናቸው፡፡

### 3.2.2.2 የታሪክ ተፋሰስ (story line) በይነ-ቴክስታዊነት

እንግዲህ ከላይ የዜና መዋዕሉን የታሪክ ተፋሰስ መልክ ካየን ከገድላት ጋር በምን አቅጣጫ ወይም በምን አይነት ሁኔታ ነው የሚናበቡት የሚለውን መመልከት ዋና ግባችን ነው፡፡

በገድላት አጻጻፍ ውስጥ ተለይተው እንደመባያ ከሚቆጠሩ የታሪክ ተፋሰስ አላባዎች መካከል መግቢያው አንዱ ነው። በገድላት የመግቢያ ቅርጽ ላይ ከሚስተዋሉ ባህርያት መካከል ተራኪዎቹ ስመ እምላክን /በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ/ ማንሳታቸው እና አስጀምሮ እንዲያስጨርሳቸው መማለዳቸው አንዱ ነው። ከላይ የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕልን መግቢያ በተመለከትንበት ጊዜ ይሔው ነጥብ ተካቶ ተመልክተናል። በተጨማሪም ባለታሪኩን አስቀድሞ ማንሳት እና ማስተዋወቅ ሌላው የገድላቱም የመግቢያ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ ሌላ ልናነሳው የሚገባን ከዜና መዋዕላቱ ጋር ያለ በይነ-ቴክስታዊነት መልክ ከላይ የተራኪው ርዕዮተ ዓለም በማለት ለማስረዳት የሞከርኩት ነጥብ በገድላት ውስጥ የተራኪውን የእምነት መሰረት የሚያጸናበት ሚስጢረ ሥላሴ አሲያም ነገረ መለኮት በመግቢያው ላይ በብዛት ተካትቶ መገኘቱን ነው። በመሆኑም የዜና መዋዕላቱ እና የገድላቱ የመግቢያ ይዘት በይነ-ቴክስታዊ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል።

ከመግቢያው ክፍል በመሻገር በገድላቱ ተረክ ውስጥም የተጋጻሲውን አጠቃላይ ተጋድሎ የሚያካትት እና ይሔም ተጋድሎ በመውጣት ጀምሮ በተአምራት እና በድል በፊውስ እየታጀበ ተግባሩን እስኪፈጽም ይጓዛል።[12] በዜና መዋዕሉ ውስጥ ማየት እንደቻልነው ተረኩ ባለታሪኩ ከነበረበት ስፍራ በመውጣት ጀምሮ በታላቅ ተጋድሎ ውስጥ በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት እየተረዳ በተአምራት እና ፈውስ ታጅቦ ለመጨረሻው ድል ይበቃል። ዋናው የተረኩ አካልም ይሔንን በመያዝ ዋና ተራኪው የተነሳበትን አላማ ከግብ በማድረስ ይቋጫል።

በማጠቃለያው ላይም አብዛኞቹ ገድላት የቅዱሱን ሰው ረድኤትና በረከት በመመኘት ስለራሳቸውና ስለህዝቡ በመማለድ እንዲሁም አስጀምሮ ላስጨረሳቸው አምላክ ምስጋናን በማቅረብ ያጠቃልላሉ። እንዲሁ ከላይ ባየነው መሰረት ከአጠቃላይ የተረኩ መቋጨት በኋላ በዜና መዋዕሉ ውስጥም እነዚህኑ ነጥቦች እናገኛለን።

በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ በአጠቃላይ ከቅርጽ አንጻር (በተለይ የታሪክ ተፋሰስ) ዜና መዋዕላቱ እና ገድላቱ በይነ-ቴክስታዊነት አላቸው ማለት እንችላለን። በተጨማሪም በየቅርጻቸው ውስጥ በሚይዙት የታሪክ ተፋሰስ ይዘቶች ህብር ይፈጥራሉ። ሆኖም ይህ መናበብ ፍጹም አንድ አይነት ነው፣ አንዱ የአንዱ ግልባጭ ነው ማለት አይደለም። ይልቁንም ሁለቱም እንደየ ተነሱበት አላማ በየመስመራቸው ጉዳያቸውን ያካትታሉ እንጂ።

---

[12] ቢያንስ ይሄን ለመረዳት የቴዎድሮስ ገብሬን "የመባያ ጉዳዮች በገድለ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ" የሚለውን ጥናት መመልከት ይቻላል (ቴዎድሮስ 2001) ።

### 3.2.2.3 ተአምራዊነት

ተአምራዊነት ስንል በሌላ አባባል ልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ማለታችን ነው። ከዚህ አንጻር በዜና መዋዕላቱ ውስጥ የታዩ በሰው አቅም ሊደረጉ የሚከብዱ ይልቁንም በአምላክ እገዛና ድጋፍ እንደሆኑ የሚታመኑ ወይም ተራኪው በዚህ ደረጃ የገለጻቸውን ነጥቦች በጥቂቱ እናያለን።

በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ውስጥ በሰው ኃይል መደረጋቸውን ለማመን የሚከብዱ በርካታ ተረኮችን ማግኘት ይቻላል። በእያንዳንዱ ጦርነት ውስጥ ንጉሡ የሚጋፈጣቸው ግብግቦች ንጉሡ ካለበት ሁኔታ አንጻር ታአምራዊ ሆኖ የሚቀርቡ ናቸው። በጥቂት ወታደሮች ከብዙ ሠራዊት ጋር ተጋጥሞ እስከማሸነፍ ሲልም ሙሉ የጠላት ጦርን ለብቻ ተዋግቶ እስከማባረር የሚደርሱ ተአምራዊ ሁነቶችን እናገኛለን። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ደግሞ የዜና መዋዕሉ ታላቅ ድል ሆኖ በተተረከው የአዳል ጦርነት ውስጥ በቀጥታ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤትን እንመለከታለን።

ከላይ ደጋግመን እንደተመለከትነው ይህ ጦርነት ሲካሄድ ዐምደ ጽዮን በጣሙን የታመመና ከአልጋ ላይ እንኳን ለመነሳት የሚያስችል ጉልበት አልነበረውም። ከዚህም በተጨማሪ አሉኝ የሚላቸውን ሠራዊቶች ወደሌላ ተግባር አርቆ የሰደደበት ጊዜ ነበር። ንጉሡን ሊዋጉ የመጡ የአዳል ሠራዊት ከባህር አሸዋ ከሰማይ ከዋክብት የበዛ መሆኑን ዜና መዋዕሉ ይተርካል። በዚህ ተስፋ አስቆራጭ ሰአት ከዚህ መአት እና ጥፋት ዐምደ ጽዮንንና ተከታዮቹን የሚያድናቸው በዮርዳኖስ ጸበልና እምነት አማካይነት የልዕለ ተጥሮ እገዛ ወይም ተአምር ነው።

> የቀትር ጊዜ ሲኾንም የፍርድ ሞት ወደ ወንጀለኞች ፊት ተመለሰ። ድንጋጤም ከእግዚአብሔር ታዝዞ በላያቸው ላይ ወረደ። ታላቅም ዐውሎ ነፋስ ወደ መካከላቸው ገባ የምድር ትቢያንም አለበሳቸው። ያን ጊዜ ዐይኖቻቸው ጨለሙ፣ ኃይላቸውም ደከመ ዕጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ታሰሩ። ንጉሥ በምድር ላይ በፊታቸው ያሰረጫት የዮርዳኖስ ወሐን ማለፍ ተሳናቸው ዐመፀኞች ያባረራቸው ሳይኖር ወደ ኋላቸው ሸሹ። የጸናች ዕጅ አጠፋቻቸው። ከፍከፍ ያለችም ክንድ የተሰወረችም ቀኝ ዕጅ በአንድ ጊዜ አጠፋቻቸው። የዐመፀኞች ወገኖች በገብረ መስቀል ዕጅ እንደ ዐይን ጥቅሻ ፈጥነው በአንዲት ቀን በምድር ጉድጓድ ሰጠሙ። (ገጽ 37)

በዚሁ የጦርነት ክፍል ውስጥ ተአምርን የምናየው የዮርዳኖስ ጸበል እና እምነት "የጠላትን" ኃይል ሲመታ ብቻ አይደለም። ይልቁንም የዐምደ ጽዮንን ህመም ከመፈወስም በላይ ኃይልን በማልበስ ጭምርም እንጂ። ከአልጋው እንኳን መነሳት የማይችል በሽተኛ ጸበሉን ተክለ ጽዮን በተባለ ቄስ ከተጠመቀ በኋላ ፈውስን ያገኛል። "በተጠመቀም ጊዜ ህማሙ ከእርሱ ተወገደ። ድካሙም ራቀ። ኃይልንም ከላይ ለበሰ" (ገጽ 31) ይለናል ተራኪው። ይሔ የፈውስ ተአምር የተደረገለት ዐምደ ጽዮን አሁንም በጦርነት ውስጥ ሌላ አስደናቂ ተአምራዊ ገድሎችን ሲያከናውን እንመለከታለን።

> ንጉሥም የወንጀለኞች ብዛት ወዳለበት በግራ በኩል ገባ። ወደ ኋላውም አላፈገፈገም። ፍላጻም በላዩ ላይ እንደ ዝናም ሲዘንም፣ የብረት ዘገርና የብረትና የእንጨቶች ጦሮች እንደ በረድ በላዩ ሲዘንሙ ዝርባውን አልመለሰም (አልቀለሰም)።
>
> ሰይፎችንም ይዘው ሊከቡት መጡ። እርሱ ግን ፊቱን እንደ ድንጋይ አጸና። ልቡንም (ሰውነቱንም) ለሞት አስጨከነ። የወንጀለኞችንም ከተማ ሰነጠቀ። <u>አንዱንም በወጋው ጊዜ ሑለተኛውን ወጋው። ሑለቱንም ጉሉ እንደ አንድ አካል መጠን በእግዚአብሔር ኃይል በአንዲት ጦር ወጋቸው።</u> (ገጽ 32፣ አጽንዖት ከራሴ)

በአንድ ጦር ሁለት ሰዎችን ደራርቦ እስከመጣል ያለ ተአምራትን እንመለከታለን። ይሔንንም እንደምን ሊሆን ቻለ ብለን ስንጠይቅ በእግዚአብሔር ኃይል መሆኑን ያስረዳል ተራኪው። በመሆኑም የልዕለ ተጥሮ ረድኤት በዜና መዋዕሉ ውስጥ ከሚታዩ ጉዳዮች አንዱ ሆኖ እናገኘዋለን።

በርካታ አጥኚዎች ገድላት እና ተአምራት እጅግ የበዛ ተአምራትን እና የተጋነኑ ድርጊቶችን በተረኮቻቸው ውስጥ እንደሚያካትቱ ይገልጻሉ (አምሳሉ 1976፡ 39)። እነዚህ ድርጊቶች እና ሁነቶች በልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት የሚደረጉ ናቸው። ይህ የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት እንደመባያ በገድላት ውስጥ በስፋት የሚነሳ ነጥብ ነው (ቴዎድሮስ 2001፡ 109)። ይህም ልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ከሰው አቅም እና ግምት ውጪ የሚከሰቱ በመሆኑ ተአምራት እንላቸዋለን። በመሆኑም እነዚህ ነጥቦች በዜና መዋዕላቱ ውስጥም ተካተው የምናገኛቸው በመሆኑ ተአምራዊ ድርጊቶች ብለን በዚህ ትንተና ስር ተመልክተናቸዋል። በባህርይ ደረጃም በሁለቱም የሥነ-ጽሑፍ ዘሮች ማለትም በዜና መዋዕላቱና ገድላቱ ውስጥ በጋራ የምናገኘው አንዱ ነጥብ ተአምራዊነት በመሆኑ በይነ-ቴክስታዊነት አላቸው ብለን መናገር እንችላለን።

### 3.2.2.4 ጸሎት/ ምልጃ

በዜና መዋዕላቱ ውስጥ በስፋት ከምናገኛቸውና ከገድላቱ ጋር በይነ-ቴክስታዊነትን ከሚከስቱ ጉዳዮች መካከል ጸሎት/ምልጃ አንዱ ነው። ጸሎት በዜና መዋዕላቱ ውስጥ በበርካታ ሁኔታዎች፣ በተለያየ መንገድ ተገልጾ እናገኛለን። በመሆኑም ለዜና መዋዕላቱ መንፈሳዊነት መላበስ የራሱን አስተዋጽዖ አበርክቷል። በሌላም አኳኋን ስለተረኩ ዘመን ማህበረሰባዊ እና ስነልቦናዊ አቋም መረጃ እንዲኖረን ያደርጋል።

በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ውስጥ ጸሎት በተለያየ ጊዜና ለተለያየ አላማ ሲካሄድ እንመለከታለን። አንዳንዶቹን ጸሎቶች/ምልጃዎች ባለታሪኩ ሲጸልይ የምናይ ሲሆን ሌሎቹን ደግሞ በካህናቱ በኩል ሲጸለዩ እንመለከታለን። በሌላም በኩል በዜና መዋዕሉ ውስጥ ጸሎት ለተለያዩ ጉዳዮች ግልጋሎት ላይ ሲውል እንመለከታለን። ለምሳሌ ለምስጋና፣ ለልመና፣ ለምልጃ ሲከወን እናያለን። ይህም የሚወሰነው እንደታሪኩ ይዘትና እንደሚገጥመው ሁኔታ ነው።

ዐምደ ጽዮን እጅግ አስጨናቂ በሆኑ ጉዳዮች መካከል ሲገባ በጸሎት ተራዳኢነትን ከእግዚአብሔር ይጠይቃል። ከነዚህ ሁኔታዎች መካከል የሰብረዲንን ማምለጥ በሰማ ጊዜ አዳራሽ ወደ ምትባልም ድንኳን /ቤተ-ክርስቲያን ወይም የጸሎት ቤት/ ውስጥ በመግባት ጠላቱን ይከተል ዘንድ ሲለምን እናያለን (ገጽ 8)። ወደ አዳል ምድር በሚያደርገው ጉዞ መካከል በገጠመው ጦርነትም ላይ ጦርነቱ ውስጥ ከመግባቱ አስቀድሞ ስለራሱ መዳን ሲጸልይ እናደምጣለን (ገጽ 15)። ከዚህ በተጨማሪ በአዳሉ ጦርነት ወቅት እንዲሁ በጸሎት የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤትን ሲለምን እናያለን። ጸሎቱም እንደ አንዱ የመዋጊያ ሰይፍ ሆኖም ተተርኳል።

> ንጉሥ ግን በእግዚአብሔር አምኖ ጸና። ሕማሙንና ድካሙንም ረሳ። አንደበቱ ሑለት የኾነ ሰይፍንም ታጠቀ፣ ይኸውም ጸሎት ነው። ድል የመንግሥት ልብስ የኾነ፤ ደረትን የሚሠውር ፅሩንም ለበሰ። ይኸውም ፍጹም ሃይማኖት ነው። እንዲህም አለ የሙሴና የኣሮን አምላክ ርዳኝ (አለ)። ካህናትንም እንዲህ አላቸው ምህላ ያዙ ማለት ተሰብሰባችኁ እግዚአብሔርን ለምኑ። በጸሎታችኹም ጊዜ አትርሱኝ (አላቸው) (ገጽ 28)።

በሌላም ሁኔታ ራሱ ከሚጸልያቸው ጸሎቶች በተጨማሪ ሌሎች እንዲጸልዩለት እና እንዲማልዱለት የሚያደርግባቸው የተረኩ ክፍሎች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ንጉሡ የሐድያን ንጉሥ ተባብሯል በሚል የዳውሮን ሹም ሐድራን ከያዘ በኋላ ለሐገሩ ካህናት

በላከው የምስራች ውስጥም እንዲጸልዩለት ምህላ እንዲያደርጉለት ይጠይቃል (ገጽ 12)። ይህ ጸሎት ለተደረገለት እና ለድሉ ምስጋና እና ለቀጣዩም ዘመቻ መቃናት የሚደረግ የምልጃ ጸሎት ነው። በሌሎች ሰዎች ስለንጉሡ ከሚደረጉ ምህላዎችና ጸሎቶች መካከል በአዳል ጦርነት ወቅት እንደተደረገው አይነት ምህላና ጸሎት በዝርዝር የተገለጸ አይገኝም። በሰፊ ከመተረኩም በተጨማሪ ራሱ ንጉሡን ጨምሮ ንግሥት ሦገ መንግሥት እና ካህናት ተሳታፊ ሆነው ነው የምናገኛቸው። ይህ ጸሎት የህይወትና የሞት ጉዳይ በገጠማቸው ሰአት የሚደረግ በመሆኑ እጅግ መሪር እና ጥልቅ ነው። አመድን በላያቸው ላይ እስከመነስነስ የደረሰ ምልጃን ነበር ያደረጉት። ካህናት ታቦት ገልብጠው ነው መሪር ጩኸት ያሰሙት። ከዚህ በኋላም ንጉሡ ስለርሱ ያይደለ ስለህዝቡ መዳን ሲማልድ እና ሲጸልይ እናያለን (ገጽ 28-30)። የእነዚህ ጸሎቶች ምላሾችም ፈጣን እንደሆኑ እመለከታለን። ወዲያውም የልመናው ጸሎት በምስጋና ጸሎት ይተካል።

በገድላት ላይ ጸሎት ዋንኛ መባያ መንገድ መሆኑ ግልጥ ነው። ተጋዳሊው መንፈሳዊነቱን ከሚነግሩን እንዲሁም የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ምክንያት ሆኖ ከሚገለጸው እንዲሁም የቅዱሱ ሰው የብቃት ደረጃ ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል ጸሎት አንዱ ነው። በመሆኑም በዜና መዋዕሉ ተረክ ውስጥም ጸሎት ጉልህ ስፍራ አግኝቶ ተመልክተናል። ስለዚህም ሁለቱም ሰነዶች በጋራ ከሚቀዷቸው ወይም በይነ-ቴክስታዊነት ከሚታይባቸው ጉዳዮች መካከል ጸሎት አንዱ ሆኖ እናገኘዋለን።

## 3.ሰ. "የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል"

## 3.2 አተኩሮ "በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ውስጥ

"በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ውስጥ ያለውን አተኩሮ ከማየታችን አስቀድሞ ተረኩ የሚቀርብበትን የጊዜ አውድ ማወቁ ጠቃሚነት ይኖረዋል። የዜና መዋዕሉ አተራረክ በአብዛኛው በ"አሁን" ጊዜ ክዋኔ የሚገለጽ ሳይሆን በአለፈ ጊዜ የሚጠቀስ ነው። በመሆኑም ተራኪያችን አጠቃላይ ታሪኩን የሚነግረን በ"ነበር" አገላለጽ ነው። የሚሰጠን መረጃም ባየውና በሰማው ላይ ተንተርሶ ከመዘገብ ያለፈ የርሱ ተሳትፎ በጉልህ የማይታይበት በመሆኑ ውጫዊ አተኩሮ /ተራኪ/ External focalization/ን የተከተለ ነው ማለት እንችላለን።

### 3.2.1 አንጻር (ተራኪው፣ መደብ እና የዕይታ አቅጣጫ) ፦

ተራኪው ተረኩን የሚገልጽበት የመመልከቻ አቅጣጫ ሁለተኛ መደብ የመተረኪያ አንጻርን (ዳረኛ አተኩሮ /ተራኪ/ External focalization)ን ነው። በትረካው ላይም ራሱን በታዛቢነት እና በተመልካችነት ማኖሩን ደጋግሞ ይነግረናል። የተለያዩ ክንዋኔዎችና ሁነቶችን በሚተርክበት ጊዜ ይሄንን ሲባል ሰምቻለሁ ግን አላየሁም በማለት ነው ተረኩን የሚያስኬደው። ለማስረጃም ዘርዐ ያዕቆብ የቀጣው ቢተወደድ ኢሳያስ የት እንደደረሰ ሲተርክ፣ "ቀስት ወደምትባል በአማራ ምድር መጋዙን በጆሮዬ ሰምቻለሁ በአይኔ ግን አላየሁም አልነበርሁም። የወሰዱበትን ቦታ አላውቅም" በማለት ነው የሚነግረን። በሌላም በኩል በአጠቃላይ የታሪኩን ፍጻሜ ከመተረኩ አስቀድሞ "ከአምደ ሰይጣን በኋላ በብትህወደድነት የተሾመ አላገኘሁም" ይለናል (ገጽ 50)። ከዚህም በተጨማሪ ለሚሰጠው መረጃም እንዲሁ የርሱ ምስክርነት መታመንን የጠበቀ እንዲሆን ሲጠነቀቅ "ሥጋ ጠጅ የማይጠጡ ስሞቻቸውን ያላወቅሁ ሌሎችም አሉ" በማለት ይገልጻል (ገጽ 53)። ይህ አገላለጽ የሚታመን መረጃ ከማቀበል የዘለለ የተራኪውን ማንነት እና ከታሪኩ አንጻር የርሱን ድርሻ እና ደረጃ እንዲሁም የመተረኪያ አቅጣጫውን ለይቶ ለማስረዳት ይጠቅማል። በመሆኑም ተራኪያችን ከላይ ባነሳናቸው ምሳሌዎች መሰረት ለድርጊቶቹና ክንውኖቹ ቅርብ የነበረ መሆኑን እንደመጀመሪያ ተመልካች አይን የምንቆጥረው ሲሆን በርሱው አገላለጽ ደግሞ ተንተርሰን ደግሞ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ታዛቢ ወይም መረጃ አጠናቃሪ ሆኖ እናገኘዋለን።

የተራኪያችን የመተረኪያ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን፣ ታሪኩ ማንን ማዕከል በማድረግ ነው የሚተረክልን የሚለውን ነጥብ በማንሳት ለመመልከት ስንሞክር ከመጀመሪያው ነጥብ አንስቶ እስከመዳረሻው ድረስ ማዕከላዊ የትኩረት አቅጣጫው ዘርዐ ያዕቆብ መሆኑን

እናስተውላለን። በዚህ ዜና መዋዕል የሚነሱ ማንኛቸውም ተረኮች ባጠቃላይ ትኩረታቸውና ማዕከላዊ ነጥባቸው ንጉሡ ነው። በኋላ በጥልቀት የምንመለከተው ጉዳይ ቢሆንም በዚህ ዜና መዋዕል ውስጥ ተራኪው አንዱን ታሪክ በሁለት መንገድ ተርኮት እናገኛለን። ከነዚህ ሁለት የመተረኪያ መንገዶች መካከል በሁለተኛ ደረጃ በተጠቀመበት በምዕራፍ የመከፋፈል ትርክት ውስጥ በአራት መሰረታዊ ነጥቦች ላይ እንደሚያተኩር ተራኪው ከምዕራፍ አከፋፈሉ መረዳት ይቻላል። እነዚህም ጽድቅና ሃይማኖት፣ ቅብዐ መንግሥት፣ ሥርዐተ ሲመት፣ የስብቀት ጥፋት ናቸው። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ታሪኩ ሲሽከረከር የተራኪው አይን በምንም አይነት ከዘርዐ ያዕቆብ ላይ ተነስቶ አናይም። ስለዚህም የተራኪው አትኩሮ በዘርዐ ያዕቆብ ላይ ነው ማለት እንችላለን።

### 3.2.2 ርዕዮተ ዓለም

በዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ላይ የተራኪውን ርዕዮተ ዓለም ለማወቅ ከላይ እንደተመለከትነው የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል በጣም ቀላል አይደለም። ለዚህም ምክንያት የሚሆነው ተራኪው በቀጥታ ታሪኩን በሚያቀርብበት ወቅት የተከናወነውን ድርጊትና ሁነት በገለልተኝነት ከመተረክ በዘለለ የራሱን ሀሳብ ወይም አስተያየት ሲሰጥ አለማድመጣችን ነው። ሆኖም ባንዳንድ የአተራረክ ሁኔታዎች ውስጥ አልፎ አልፎ የሚገልጽበትን ድምጸት እና የዝንባሌውን መጠን በማየት በከፊልም ቢሆን የተራኪውን ርዕዮት መገመት ይቻላል።

ከዚህ አንጻር ከፍ አድርገን እንደተመለከትነው ተራኪ በመለኮት ከአሊነት፣ በቤተ-ክርስቲያን ሥርዐት መጠበቅ ላይ ያለው ዝንባሌ የጎላ መሆኑን ማየት ይቻላል። ዓለምን የሚረዳው ከክርስትናው አስተምህሮ አንጻር መሆኑን በተረኩ ውስጥ ለሚከሰቱት ግጭቶች አልፎ አልፎም ቢሆን በሚሰጠው ፍርድ መመልከት ይቻላል። ለምሳሌ ከንጉሥ ጋር ተጋጭቶ በሞት እንዲቀጣ የተፈረደበትን አምደ መስቀልን ስመ አጠራሩን ለውጦ "አምደ ሰይጣን" በማለት ይጠራዋል (ገጽ 49)። ተራኪው ስለአምደ መስቀል ሐጥያት ሲነግረን "በስውር ያደረገው ያልተገለጠ" ነው ይለናል። ሆኖም በግልጽ አደረገ ተብሎ የተከሰሰበት ጉዳይ ያገባች ሴትን ለሌላ ሰው አሳልፎ በመስጠት ማጋባት እንደሆነ ይነግረናል። በዚህ ምክንያት ከንጉሥ የተጣላ ሰውን በተራኪ ፍትህ ከማየት ይልቅ ሐጥያቱን አትልቆ ለማሳየት "በስውር ያደረገው አይነገርም" ሲል ነው የሚያከፋው። ሁለቱን ነጥቦች በመውሰድ፤ አንደኛ ተራኪው ወንጀሉን ስለምን አክብዶ ማሳየት አስፈለገው? ሁለተኛም ስለምን ስሙን መለወጥ አሰኘው? የሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ስንመልስ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተራኪውን ርዕዮተ ዓለም ማወቅ እንችላለን።

በመሆኑም ንጉሡ ብትወደድ አምደ መስቀልን በድንጋይ ተወግሮ እንዲሞት ሲደረግ ክሱን ከፍ አድርጎ የሚያሳይ ነጥብ ያስፈልጋል። ለዚህም ትክክለኛውን ምክንያት አስቀምጧል ሆኖም ፍርዱ እስከሞት የሚያደርስ መሆኑን ያመነበት አይመስልም። በዚህም ንጉሡን ተሳስቷል ማለት አልፈለገም ብሎ መገመት ይቻላል። ስለዚህ ተጨማሪ የከበደ ጥፋት ያስፈልጋል። ያ ጥፋት ይህ ነው ሲባል አልተፈለገም፣ ስለዚህ በስውር ግን ሌሎች ያጠፉቸው ስህተቶች ሳይኖሩ አይቀሩም እኔ ባላውቅ ነው የሚል የሚመስል አተራረክ መንገድን ተከተለ። እዚህ ላይ ዋናው ጉዳይ የተራኪው ርዕዮተ ዓለም ነው። ተራኪው ንጉሥ ፍትህ አዋቂ ነው፣ ለፍርዱ ስህተት የለውም ብሎ ያምናል። ስለዚህም ጥርጣሬ ሲኖረው እንኳን እኔ የማላውቀው ሌላ ኃጥያት አለ ሲል ንጉሡን ይከልላል።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የስም ለውጡ ለምን መጣ ብለን ላነሳነው ጥያቂ መልስ እንስጥ። በዚህ የተረክ ክፍል ውስጥ ጥፋትና ኃጥያቶቻቸው ተዘርዝሮባቸው የተጋዙ፣ አንዳንዶቹም ተወግረው የሞቱ ሰዎች አሉ። ከነዚህ ሰዎች መካከል ብዙ ሰዎችን በሐሰት ያስገደለው ዘርዐ ጽዮን አንዱ ነው። ይህ ሰው እና ግብረ አበሮቹ የንጉሥ ልጆችን ሳይቀር እንዲገረፉ ያስደረጉ ብዙዎችን ያስገደሉ ሰዎች ናቸው። በዚህም ወንጀላቸው የተነሳ ተግዘዋል። ሆኖም ስማቸው ሲቀየር አናይም (ገጽ 49)። አምደ መስቀል ከሌሎች ተከሳሾች አንጻር ስንመለከተው ለዙፋኑ ቅርብ ሆኖ የሚገኝ እርሱ ነው። ለዚህም ማሳያ የሚሆነን ከርሱ በኋላ ከንጉሡ ልጆች በቀር በብትህወዳድነት የተሾመ አለመኖሩን ስንመለስት ነው። በመሆኑም ይህን ሰው ንጉሡ ከፋኛ ከቀጣው ተራኪያችንም የአቀጣጡን ያክል ጥፋት እና ኃጥያት ሊነግረን ይገባል። ለዚህም የባዕድነት መገለጫ በቅዱሱ የመስቀል ስም ከመጥራት "ሰይጣን" ማለቱ የበለጠ የተሻለ መሆኑ አንዱ መላምት ሲሆን ሌላው ደግሞ ያልተገለጠውን ኃጥያቱን ለማግዘፍ እና ለማተለቅ የስሙ ለውጥ የሚጫወተው ሚና ቀላል ባለመሆኑ ነው። ስለዚህም የተራኪያችን ርዕዮተ ዓለም ንጉሥ ያለስህተት የሚኖር መሆኑን የሚቀበል እንዲሁም "እንደንጉሡ ያጎንብሱ" እንደሚባለው አይነት ከንጉሥ ሀሳብ ጋር የመቆም ነው ልንል ይቻለናል።

ይሔን እምነታችንን የሚያጠናክርልን በሌሎች ውጊያዎች ላይ ለንጉሡ ጠላት ሆነው የሚያገኛቸውን ሰዎች ቅጥያ ስም ሲሰጣቸው ስናይ ነው። ከሐድያው ገገር ጋር በተጣላ ወቅት የወቅቱን የሐድያ ገገር በድላይህን "አውሬው" እያለ ነው የሚገልጸው (ገጽ 63)። ይህ የስም አጠራሩ ብቻ አይደለም የተራኪያችንን ርዕዮተ ዓለም የሚያመላክተን። የበድላይህን ሽንፈት እና የሠራዊቱን መጥፋት ሲተርክ እንደማንም ድል ተደረገ ከማለት ይልቅ "እንደ ትምክህታቸው መጠን ተከፍሏቸዋል" ሲል ነው የሚፈርድባቸው (ገጽ 59)። ይህም እንደላይኛው ሁሉ ለንጉሡ እና ለክርስትናው ያለውን ታማኝነት የሚገልጽ በመሆኑ የተራኪውን የመመልከቻ እና የመፍረጃ ሚዛን ያስረዳል። በዚህም ርዕዮተ ዓለሙን መረዳት እንችላለን።

### 3.2.3 አላማ

“የዘርዐ ያዕቆብን ዜና መዋዕል” ተራኪ አላማ ለይቶ ለማወቅ አስቀድሞ አጠቃላይ ዜና መዋዕሉ በምን አይነት ነጥቦች ላይ አትኩሮ ይተርካል የሚለውን ነጥብ ለይቶ መመለስ ያስፈልጋል። ከዛም ውስጥ ባነሳቸው ነጥቦች ዝንባሌና እያስረገጠ ሊነግረን በሚፈልጋቸው ነገሮች ምንነት ላይ በመንተራስ መሰረታዊ አላማውን ልንለይ እንችላለን። በመሆኑም የተራኪያችንን የትኩረት አቅጣጫዎች በመሰብሰብ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን በጥንካሬ መንገርን አላማ አድርጓል ማለት ይቻላል፤ የዘርዐ ያዕቆብ አቃቤ ሥርዐትነት እና ቀናኢ ሃይማኖት።

#### 3.2.3.1 አቃቤ ሥርዐት

አቃቤ ሥርዐት ስንል ሥርዐት እና ህግን የመጠበቅ ዝንባሌን ነው፤ ሥርዐትን የመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ሥርዐትን ማበጀትን ያካትታል። ዘርዐ ያዕቆብ ነባሮችን ሥርዐቶችን በመጠበቅ፣ የተረሱትን በማድመቅ፣ አዲሶችን በማስተዋወቅ ላይ አትኩሮ እንደኖረ በተለያየ መንገድ ተራኪው ይናገራል። እነዚህ ሥርዐቶች ደግሞ ሥርዐተ መንግሥት እና ሥርዐተ ሃይማኖትን አደባልቀው የያዙ እንጂ ሁሉም አንድ መልክና አቅጣጫን የተከተሉ አይደሉም። በሥርዐተ መንግሥት ውስጥ ነባሩን ሥርዐት ከመጠበቅ አንስቶ በዘመኑ ያለውን የመንግሥትና የአስተዳደር መዋቅር ማደራጀትን እንዲሁም የችሎት እና የቤተመንግሥትን አስተዳደር እና አኳኋን ያካተተ ነው። በአንጻሩ ሥርዐተ ሃይማኖት ስንል እንዲሁ ከቅዳሴው ሥርዐት አንስቶ እስከሚነበቡ እና እስከሚጸለዩ ጸሎቶች፤ የክህነት ደረጃ፣ የጥምቀት (ለፊውስ የሚደረገውን) ሥርዐት እና የታቦት ብዛት፣ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ቀኖናዎችን፣ ጥንቆላን እስከ መዋጋት ድረስ ያሉ ሥርዐቶችን ከማጽናት አዲስ እስከማውጣት ድረስ ይደርሳል።

ሥርዐተ መንግሥት፡- ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከነባሩ ሥርዐት ጠብቆ ወደስልጣኑ እንደመጣ በትክክልም ከርሱ የቀደሙ አባቶች /እንደ ሰለሞናዊ ስርወ መንግሥት/ በአክሱም ጽዮን የሚደረገውን ሥርዐተ ንግሥና እንዳደረገ ያንንም ሥርዐተ ንግሥና ነባሩን በማጽናት ላይ ያተኮረ እንደሆነ ተራኪው ይነግረናል። የትግራይ ገዢ እና ንቡረዕድ እንደ ህጋቸው የወይራ ለበቅ እየከለከሉ በቀኝ እና በግራ መቆማቸውን ጨምሮ፣ ለለጽዮንም ክብር ለአክሱም የሚሆን ሌሎች ነገሥታት ይሰጡት እንደነበረው እጅግ የበዛ የወርቅ ስጦታ መስጠቱን እንዲሁም በቅጥሯ ውስጥ በሚገኝ የመንገሻ ድንጋይ መቀመጫ ላይ በመቀመጥ እንደነባሩ ሥርዐት ንግሥናውን መቀበሉን በጥልቀት ይነግረናል (ገጽ 60)። የዚህ ተረክ መሰረታዊ አላማ ዘርዐ ያዕቆብ ሥርዐትን ጠብቆ የነገሠ ንጉሥ መሆኑን ማስረገጥ ነው።

ከላይ ካየነው በተጨማሪ አነጋገሱን ብቻ ሳይሆን ሚስጥራዊ በሆነ የተነጠለና በበዛ ሥርዐት ውስጥ ያለውን አኗኗር፣ አወጣጥ እና አገባቡን እንዲሁም የቤተ መንግሥት አገነባብ እና በውስጥጡ ያለውን ሥርዐት በዝርዝር ይተርክልናል፡፡ በዚህ ትረካው ውስጥ የግቢውን አገነባብ በልኬት ስንት ክንድ እንደሆነ ከመግለጽ አንስቶ ከምን ቁስ እንደተሠራና እንዴት እንደተሠራ ጭምር ይዘረዝራል (ገጽ 54-55)፡፡ ከዚያም ያልፍና በውስጡ እነማን በየትኛው ስፍራ ለምን ግልጋሎት እንደሚገኙ እና እንደምን ባለ ሥርዐት እንደሚያገለግሉ በዝርዝር ያብራራል (ገጽ 56)፡፡ ይህ ሰፊ ገለጻ የንጉሡን መውጫ መግቢያ ሳይቀር ይተርካል (ገጽ 52-53)፡፡ ንጉሡን መቅረብ እና በቀላሉ ማየት አለመቻል፣ ከሰው ዐይን መከለልና እነማን በቅርበት እንደሚያገለግሉት አገልግሎታቸውም እንደምን እንደሆነ ይገልጻል (ገጽ 52)፡፡

> የጉዞውንም ሥርዐት ንጉሡ ሲፈቅድ ከድንኳኑና ከቤቱ ሲወጣ ከፍ ያለ ግርማ መነዋወጥ ይሆን ነበር፡፡ ሰዎች ሁሉ ከፊቱ ይሸሹ ነበር በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ፊጽሞ ይርቁ ነበር፡፡ ቁጥራቸው ሶስት የሆነ ድባብ ተሸካሚዎች ግን ቀርበው ይይዙለት ነበር እነሱም ታላላቆች ነበሩ፡፡ መነሳንስ የሚይዙት እንደነሱ ወደ ንጉሡ ቀርበው ይሄዱ ነበር፡፡ ሻማ ያገሮችም በግርዶሽ ሁነው ከሩቅ ይጓዙ ነበር ንጉሡን ከበው፣ በፈረሱ ተጭኖ በጉዞ ቀን ያለ ፈረስ በቅሎ ላይ አይጫንም ነበር፡፡ እንቢልተኞችና ነጋሪት መቾች በፊት በኋላ ሁነው እጅግ ርቀው በየሥርዐታቸው ነጋሪት ይጎሽሙ ከበሮ ይመቱ ነበር፤ ንጉሡ ሲወጣና ሲገባ ምስር ቃናውን የሚመቱ ብዙዎች ነበሩ፡፡ (ገጽ 59)

ከላይ እንደምንመለከተው የንጉሡን የክብር ጉዞ ላይ ያለውን ሥርዐት በዝርዝር ይተርካል፡፡ ይሔን በመንተራስ የተራኪውን የመተረክ አላማ መመርመር እንችላለን፡፡ ከላይ እንዳነሳነው በመጀመሪያ ደረጃ ለሥርዐት የተለየ ትኩረት እንዳለው ወይም ባለታሪኩ የራሱ የሆነ ሥርዐት ማስፈን የቻለ እንደሆነ በተጨባጭ ያሳያል፡፡ ከዛም ሻገር ካልንም የባለታሪኩን ባይተዋርነት /የተነጠለ የተሸሸገ/ አኗኗር መውደድን ያመላክታል፡፡

በሌላም አቅጣጫ በተራኪው ትኩረት ተደርጎ ከተተረኩ የባለታሪኩን አቃቤ ሥርዐትነት ከሚያስረዱ ነጥቦች መካከል ለመንግሥት አወቃቀሩ ትኩረት በመስጠት ደጋግሞም እየተመላለሰ የሚያነሳው መሆኑ አንዱ ነው፡፡ ይሔም ንጉሡ ያቋቋመው የአገዛዝ ሥርዐት እንዴት እንደሆነ በነማን ላይ የቱ ኃላፊነት እንደወደቀ በዝርዝር ይተርካል (ገጽ 50፣59)፡፡ ሌላው ቀርቶ በዐምደ ጽዮንም ዘመን እንደተገዳዳሪ የሚነሱት የሐድያ እና የአዳል ሙስሊሞችን በዘርዐ ያዕቆብ ጊዜም ጉልህ ስፍራ አላቸው፡፡ ይህንንም

ከግምት ባስገባ ሁኔታ በአገዛዝ ሥርዐቱ ስር የሚደረገውን ማሽጋሸግ እና የሚወስደውን አጸፋ እንዲሁ ይተርክልናል (ገጽ 51)። በመሆኑም ንጉሡ ሥርዐተ መንግሥትን በተመለከተ አቃቤ ሥርዐትነቱን አጎልቶ ተራኪው ሊነግረን አላማ እንዳለው እንረዳለን።

ሥርዐተ ሃይማኖት፡- የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ዜና መዋዕል በትኩረት ስንመለከት ተራኪው ስለ ባለታሪኩ ሊነግረን ከሚጥራቸው በርካታ ጉዳዮች መካከል ንጉሡ ለሥርዐተ ሃይማኖት ያለውን አተኩሮ ነው። አንዳንዴም ንጉሡ ንጉሥ መሆኑን ረስተን የሃይማኖት ሰባኪ ወይም ጳጳስ የሆነ እስኪመስለን ድረስ በርካታ ሃይማኖዊ ውሳኔዎችን ሲያስተላልፍ እና ሲሰብክ እናየዋለን። የንግሥናው መብት ከሚሰጠው ግብር የማብላት ሥርአት አንስቶ በአጠቃላይ አገልግሎቱ ውስጥ ለማን በቤተ-ክህነት ደረጃ ውስጥ ቅድምና እና የበለጠ ክብር ሊሰጥ እንደሚገባ ይደነግጋል (ገጽ 53-54)። መላው ህዝብም ጣኦትን አለማምለኩን የሚያረጋግጥ ጽሑፍ በክንዱ ላይ እንዲነቀስ ህግ ያወጣል (ገጽ 48)። አብያተ ክርስትያናት ከሚተዳደሩበት ሥርዐት አንስቶ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ በሚያጋጥሙ ጉዳዮች ላይ ወሳኝ እና ደንጋጊ ሆኖ እናገኘዋለን። ለምሳሌ የመንፈስ ልጅነትን ከሚያሰጠው ጥምቀት በዘለለ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ ለፌውስ እና ጸላዔ ሰናያትን ለማስወገድ የሚደረገውን የጥምቀት ሥርዐት ከተረሳበት አንስቶ እንዲስፋፋ እንዳደረገ ይነግረናል። ተራኪያችን ለሥርዐቱ መጀመር በእማኝነት የሚያቀርበውም ራሱ ዘርዐ ያዕቆብ የደረሰውን መጽሐፍ ነው።

> ንጉሡ ራሱ እንዲህ ብሏል በመጽሐፉም ተጽፎ አለ። ክፉዎች ሰዎች በሚቀመጥበት መደኃኒት እንዳደረጉበት በምንገድም ሲሄድ፤ የጥምቀትንም ሥራ በእሁድ ቀን እንደ ጠፉ የጥምቀት ሥርዐት ሁሉ በደብረ ብርሃን ከተፈጸመ በኋላ (እንደ ጠፉ) እኒህን ሁሉ ሟርተኞችን እግዚአብሔር እንደ ሻረለት በግልጥ ተናግሯል በሥላሴ ስም የታመነ የእስራኤል ወገን የሚሆን ንጉሣችን ዘርዐ ያዕቆብ ጽፏል። ያ የጥምቀት ሥራ እንደ ተሻረ ንጉሡ በሰማ ጊዜ ፈጥኖ አዘዘ በቤተ ክርስቲያኑ ዓጸድ ውስጥ ጉድጓድ እንዲቆፍሩ ሠራተኞች ጉድጓዱን እንዲሠሩ የከተማው ሰዎች ሁሉ ወንዱ ሴቱ ውሃ ቀድተው በፍጥነት በጉድጓዱ እንዲመሉ አዘዘ። እንደ ቃሉም ሆነ ተደረገ እግዚአብሔር ያሰበውንና የተመኘውን ፈጸመለት በዚያች ቀን በዚያ ተጠመቀ እስከ ዕለተ ዕረፍቱም ድረስ ብዙ ዓመታት ተጠምቋል። በጠበሉ ላይ ሰቀላ ሠርተው በጥጉ ቁልፍ ቆለፉት ይህም ማየ ጸሎት ለበሽተኞች መድኃኒት ሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱ በተቃጠለችበት ቀን እሳት እስኪያቃጥለው ድረስ። ከዚያ ቀን ዠምሮ በቤተ ክርስትያን በቀኝ በኩል ቀረብ አድርገው ጥምቀትን እንዲያደርጉ ንጉሡ አዘዘ። እንዲህ ብሎ በቤተ ክርስቲያን ክልል ውስጥ በደብረ

ሊባኖስ ማየ ጥምቀት አግኝተናል ብሎ (አዘዘ)፡፡ ቀድሞም በሐንጉግ በትግሬ ምድር ንጉሥ ገብረ መስቀል ባሳነፀው ቤተ መቅደስ ማየ ጥምቀት አይተን ነበረ፡፡ ዳግመኛም በቤተ ክርስቲያን በቀኝ በኩል ጥምቀት እንዲደረግ በመጽሐፈ ኪዳን አግኝተናል ከዛሬ ዠምሮ በየቦታችሁና በየአገራችሁ የክርስቲያን ወገኖች ሁላችሁ የእግዚአብሔር ሕግ እንዲፈጸም አድርጉ የሰይጣን ሥራ ጥንቆላም እንዲጠፋ ይህን ሁሉ ባይሰሩ እንዲቀጡና ቤታቸው እንዲወረስ አዘዘ፡፡ (58)

ንጉሡ እኒህን ሥርዐቶች የሚያወጣው ከአዳዲሶቹ አብያተ ክርስትያናት እስከ ነባሮቹ እነአክሱም ጽዮን ድረስ ነው፡፡ ለማስረጃም ያክል በአክሱም ጽዮን ቀድሞ ያልነበረ የሰዓታትን ጸሎት ሥርዐት እንዲያደርጉ አዞ ነበር፡፡ በዛም የአክሱም መነኮሳት ማህበርንና የእልቅናን ሥርዐት ሁሉ እንዳደረገ ዜና መዋዕሉ ይተርካል (ገጽ 60)፡፡

ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ከሥርዐት አንጻር ጸሎትና ሥርዐቱን ያወጀበትን ታሪክ እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ስብከት ማድረግ ስለመገባት መደንገጉ የተራኪያችንን ጉልህ ትኩረት ካገኙ ነገሮች መካከል ይገኛል (ገጽ 69)፡፡ ንጉሡ ስለመሐላ ሳይቀር ምን ተብሎ መማል እንዳለበት ሲደነግግ እናያለን፡፡ የሚከበሩ 33ቱን "የእመቤታችን" እና ሌሎች ሊከበሩ ስለሚገባቸው በአላት ሥርዐት እንደጻፈ ከዚህም በተጨማሪ ስለቀዳሚት ሰንበት አከባበር ሥርዐት መደንገጉም ይነግረናል (ገጽ 67)፡፡ እንዲሁም በአንድ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ስንት ታቦት መኖር እንዳለበት የደነገገው ህግም ለዚህ አይነት ሃይማኖታዊ ሥርአት ያለውን ቅንአት ያመላክታል (ገጽ 68)፡፡

በአጠቃላይ በዘርዐ ያዕቆብ የዜና መዋዕል ላይ ተመስርተን የዜና መዋዕሉ ተራኪ ሊነግረን የተነሳበትን አላማ ከሥርዐት አንጻር ስንመለከት ከላይ ያየነውን ይመስላል፡፡ ምናልባትም በአንዳንድ በተለይም በሥርዐተ መንግሥት እሳቤው ላይ በሌላ አተያይ ተራኪው 'ንጉሡን ነጥሎ እና አግዝፎ ማሳየት መፈለጉ ከላይ በዐምደ ጽዮን ላይ ያየነውን አይነት ልዕለ ሰብዕናን የመገንባት ሌላኛው መንገድ አድርገን ልንወስደውም እንችላለን፡፡

### 3.2.3.2 ቀናዒ ሃይማኖት

ከላይ በአቃቤ ሥርዐት ሁለተኛው ክፍል መመልከት እንደቻልነው ተራኪያችን ባለታሪኩን ከድንበር የዘለለ ከንጉሥነት አልፎ የሃይማኖቱ ሥርዐት አስጠባቂ እስከመሆን የደረሰ ሰብዕናን ማላበሱን ተመልክተናል፡፡ ንጉሡ በሃይማኖቱ በኩል ለሚመጡ ተግዳሮቶች የሚሰጣቸው ምላሾችን ስንመለከት ያለውን የሃይማኖት ቀናዒነት ደረጃ ያሳየናል፡፡ በዜና መዋዕሉ ውስጥ በጉልህ ከሚተረኩ ሃይማኖታዊ ተግዳሮቶች መካከል

ጣዖት፣ ጥንቆላ፣ ኑፋቄ ልናነሳቸው የሚገቡ ናቸው። በዚህ ክፍል የምናነሳቸው ነጥቦችም አስቀድመን በተነተንነው "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ላይ መንፈሳዊ ብጽዕና የሚለውን ሊተካልን ይችላል።

"የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ተረክ ሲጀምር የሚነሳው በጠንካራ ግጭት ነው። ይህ የጡዘት ምክንያት ደግሞ ሃይማኖት ነው። ተረኩም ሲጀምር "በንጉሣችን በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ከፍ ያለ ድንጋጤና እንቅጥቅጥ በኢትዮጵያ ሰው ሁሉ ላይ ሆነ።" በማለት ነው። ምክንያቱ ደስኮ ለሚባል ጣዖትና ለዲያቢሎስ ሰገድን የሚሉ ሰዎች መገኘታቸውን በመስማቱ ንጉሥ "ስለእግዚአብሔር ቀንቶ" እነዚህን ሰዎች በመቅጣቱ ነው። ከቀጣቸው ሰዎች ውስጥም የገዛ ልጆቹ ሳይቀሩ ነበሩበት፤ "ያን ጊዜ በደራሽ አዋጅ ተነገረ እንዲህ ተብሎ የክርስቲያን ወገኖች ሆይ ሰይጣን እንደሚያስተመረው ሁሉ ሁላቸውን ሰዎች ጣኦት ከማምለክ ለዲስክ ከመስገድ ለዲኖ ከመስገድ ባስተውናችው ጊዜ ዛሬማ ወደ ቤታችን ገባ" (ገጽ 48)። በማለት ለህዝብ መተዛዘቢያ እንዲሆኑ በአደባባይ እንዲታዩ አስደረገ። ለህዝቡም አዲስ ህግ እንዲወጣ ማስደረጉን እንዲህ ይተርክልናል።

> በፊታቸው የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ነን እያሉ እንዲጽፉ፤ በቀኝ አጆቻቸውም ላይ አምላክ በሆነ በክርስቶስ አምኜ ዲያቢሎስን ክጂዋለሁ ብለው እንዲጽፉ በግራ እጃቸውም ዓለምን ሁሉ የፈጠረ የክርስቶስ እናት የማርያም አገልጋይ እኔ የተረገመ ደስክ ጣዖትን ክጂዋለሁ ብለው እንዲጽፉ አዘዝዋቸው። ይህን ያላደረገ ቤቱ ይወረስ፣ ሥጋው ይቀጣ ብሎ ንጉሡ በዓለም ሁሉ አዘዘ። (ገጽ 48)

አስገራሚው ነገር ግን ብዙዎች እንዲገደሉ ይሔን የውሸት ወሬ ያስወሩ ሌሎች ነበሩ። እነዚህንም ንጉሡ ኋላ ላይ በሞት እና በግዞት ሲቀጣቸው እንመለከታለን።

በሌላ አንጻር እንዲሁ ስለሃይማኖት የሚደረግን መቅናት የሚያሳየንን ታሪክ በዚሁ ዜና መዋዕል ውስጥ እናገኛለን። ይህም ታሪክ ከደቂቀ እስጢፋ ጋር የነበረውን የእምነት ክርክር የሚዘግብ ነው። ይሔ የእምነት ክርክር የሚያጠነጥነው ደቂቀ እስጢፋዎች ለማርያም እና ለመስቀል አንሰግድም የሚል አቋም መያዛቸው እንደነበረ ተራኪው በግልጽ ያስቀምጣል። ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ በበኩሉ ሊቃውንት ይዞ እንደተከራከራቸውና እንደረታቸው ያትታል። ሆኖም ደቂቀ እስጢፋዎች ግን ይዘውት የነበረውን አስተምህሮ ሳይለቁ በመጽናታቸው ችሎት ሰይሞ እንዳስፈረደባቸው እና ሞትን ጨምሮ አፍንጫና ምላሳቸውን እየቆረጡ እንደቀጧቸው ይተርካል።

ንጉሡ ለሃይማኖቱ ያለውን ቅንአት በዚህ መልኩ ስንመለከት ላደረገው ቅጣትና ለትክክለኝነቱም ምስክርነት ከሰማይ ብርሃን እስከመውረድ ይደርስለታል። ይሄም የብርሃን መውረድ "ለብዙ ቀን ያህል ሆነ" ይለናል ተራኪው። ስለዚህም ለንጉሡ እምነት ትክክለኛነት ሰማያዊ የምልክት እማኝ በማኖር ያጸናል (ገጽ 65 - 66 )።

የእምነት ቀናኢነትን ከሚያስረዱ ነጥቦች መካከል ከላይ የተመለከትነው ሥርአተ ቤተ-ክርስቲያንን የመሥራት እና የማጽናት ጉዳይ አንዱ ነው። ከርሱ ጋር በተያያዘ ንጉሡ በአጠቃላይ በተንቀሳቀሰባቸው አካባቢዎች ሁሉ ላይ አብያተ ክርስቲያናትን ሲሠራ እንመለከታለን። አንዳንዱን ቤተ-ክርስቲያን ለመሥራት ከዘርዐ ያዕቆብ አስቀድሞ አባቱ ሞክሮ የነበረ ቢሆንም እርሱ ወደተግባር የለወጣቸው እንደሆነ ተተርኳል (ገጽ 57)። በዚህም አንጻር ዘርዐ ያዕቆብን ከጠቢቡ ሰለሞን ጋር በአቻነት ያነጻጽረዋል። አባቱ ጀምሮ /አቅዶ/ እርሱ የጨረሳቸውን ጨምሮ በዜና መዋዕሉ ውስጥ ከ10 ያላነሱ ቤተ-ክርስቲያናትን እንዳሳነጸ ይገልጻል።

በሌላም በኩል ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከሃይማኖት አኳያ ያለውን አቋም ሊያመላክቱ ከሚችሉ ነጥቦች መካከል በርካታ መጽሐፍትን መጻፉ ነው። እነዚህም በአብዛኛው የሃይማኖት ሥርዐት መጽሐፍት ናቸው። በዚህም መሰረት "ጦማረ ትስብት፣ መጽሐፈ ብርሀን፣ መጽሐፈ መዕላድ፣ ክህደተ ሰይጣን፣ እግዚአብሔር ነግሠ (መልክዐ ጉባኤ) እኒህን ሁሉ እየሠራ እየፃፈ በደብረ ብርሀን ፲፪ ዓመት ኖረ" ሲል ተራኪው ይነግረናል (ገጽ 67)።

በመሆኑም በዚህ ዜና መዋዕል ውስጥ የተራኪውን መሰረታዊ አላማዎች ለይተን ስንመለከት ከላይ ያነሳናቸው ነጥቦች ከሌሎች አላማዎች በጠነከረ ሁኔታ ጎልተው ወጥተዋል። በመሆኑም የተራኪው ዋንኛ አላማ የዘርዐ ያዕቆብን አቃቤ ሥርዐትነት እና ቀናዒ ሃይማኖት ለማወጅ ነው ማለት እንችላለን።

## 3.3 በይነ-ቴክስታዊነት በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ውስጥ

### 3.3.1 ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር

የዐፄ ዘርአ ያዕቆብን ዜና መዋዕል ከበይነ-ቴክስታዊነት አንጻር ስንመረምረው በተወሰነ ደረጃ የምናገኝበት ቢሆንም አስቀድመን ከመረመርነው የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል አኳያ በይነ-ቴክስታዊነትን የሚፈጥርበት ድግግሞሻዊ መጠኑ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል። የዚህም ዋንኛ ምክንያት ተራኪው በተረኩ ውስጥ የሚሰጠው አስተያየት ውስንነት ያለው በመሆኑ እንዲሁ በቀጥታ ያገኛቸውን ታሪኮች "ሆነ"፣ "ተደረገ"፣ "ሆኖ ነበር" እያለ የሚጽፍ መሆኑ እንደ አንድ ምክንያት ልናነሳ እንችላለን። በሌላም አኳኋን

ተራኪው በተረኩ ውስጥ ያለው የተሳትፎ ደረጃ እጅግ በጣም ውስን በመሆኑ ከዘገባ የተለየ የአተራረክ መንገዶችን እንዳልተከተለ ልብ እንላለን። ያም ቢሆን በተወሰኑ የተረኩ ክፍሎች ውስጥ በአብዛኛው የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፎች ላይ የበይነ-ቴክስታዊነት አሻራውን ያሳረፈው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥላን በተረኩ ውስጥ ማግኘት እንችላለን። እዚህም ላይ በይነ-ቴክስታዊነትን የሚያከናውንበት መንገድ በሁለቱ አቅጣጫዎች ሆኖ እናገኘዋለን። በጠቃሽ እና ማስታከክ በይነ-ቴክስታዊነት።

### 3.3.1.1 መጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሽ በይነ-ቴክስታዊነት

በዜና መዋዕሉ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተያያዥ ሆነው ከምናገኛቸው መካከል የንጉሡ ቤተመንግሥት ጸበል በሚረጭበት ጊዜ ካህናቱ በጸሎትነት ከሚያነቡት ንባብ መካከል የመዝሙረ ዳዊት ክፍል የሆኑትን ክህደተ ሰይጣን እና እግዚአብሔር ዘነግሠ የሚሉትን ጠቅሶ ማግኘታችን አንዱ ነው (ገጽ 54)። ተራኪው ይሔንን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ሲያነሳ በቀጥታ የዳዊት መዝሙር የመጽሐፍ ክፍል መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን ለዘይቤ ማዳበሪያነት አሲያም ሽፍኖ ያነሳው ባለመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሽ በይነ-ቴክስታዊ ነው ማለት ይቻላል።

በሌላም በኩል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን በቀጥታ ባለበት ሁኔታ ተራኪው የንጉሡ ቃል አድርጎ ሲጠቀምበት እናገኛለን። ይሔም የዜና መዋዕሉ ክፍል ንጉሥ የዳውሮን ገገር ሊወጋ በዘመተበት ጊዜ የንጉሥ መካሪ የሆነ ሰው ንጉሡን 'ያለህ የጦር ኃይል ከጠላት ጋር አይመጣጠንም እና ሠራዊትህ እስኪደርስ ድረስ ወደጦርነት አትግባ' ብሎ ለመከረው ምክር መልስ በሚሰጥበት ወቅት የምናገኘው ቃል ነው። በቀጥታም ንጉሥ በገለጻው ላይ ቃሉ የርሱ እንዳልሆነ ይልቁንም የነቢዩ ዳዊት ቃል መሆኑን በመጥቀስ "ነቢዩ ዳዊት የተናገረውን አልሰማህምን ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም። ኦርበኛም በኃይሉ አልዳነም። የፈረስም ብዛት አያድንም። በፍፁም ጥናቱ አያመልጥም" (ገጽ 59) የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል በይነ-ቴክስታዊት ሲፈጥር እንመለከታለን።

ከፍ ብዬ ለማስረዳት እንደሞከርኩት ተራኪው ታሪኩን የሚነግረን ባለፈ ጊዜ እንደ መሆኑ በአብዛኛው የተራኪው ሚና የውጫዊ ተመልካችነት ነው። በዚህም "የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ተራኪ ባሳየው መጽሐፍ ቅዱሳዊ በይነ-ቴክስታዊነት ልክ ስንመለከተው "የዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ስስ ነው ማለት እንችላለን። ይህም የተራኪዎቹ የትረካ መደብ በይነ-ቴክስትን ከመፍጠር አኳያ ሊኖረው የሚችለውን ሚና ሊያመላክት የሚችል ነጥብ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

### 3.3.1.2 መጽሐፍ ቅዱስን የማስታከክ በይነ-ቴክስታዊነት

በዚህ ዜና መዋዕል ውስጥ በይነ-ቴክስታዊነት ከሚፈጠርባቸው መንገዶች ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በታሪኩ ውስጥ በማስታከክ ማለትም የጥቅሱን ቦታ በቀጥታ ሳያነሱ ሆኖም ለዘይቤ መግለጫነት ተጠቅመው ማካተት አንዱ ነው። ከዚህም አኳያ "የዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" በተወሰነ ደረጃ ይሔኑ መንገድ ሲጠቀምበት እናስተውላለን።

ገና ዜና መዋዕሉ ሲጀምር በመግቢያው ክፍል ውስጥ ለልብነ ድንግል ለመጸለይ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሆነ ታሪክ በማሳያ ወይም ምስል ለመከሰቻ በማንሳት ሲጠቀም እንመለከታለን። "በአፍራስ መንፈስ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ በኤልያስ ያደረ መንፈስ በደቀ መዝሙሩ በኤልስዕ ዕፅፍ ድርብ ሆኖ እንዳደረበት" (ገጽ 46) ይለናል። ይህ ታሪክ ኤልያስ በሰረገላ ወደሰማየ ሰማያት ያረገበት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ነው /2ነገሥ 2 ÷1-12/።

በሌላም በኩል በቀጥታ በመጥቀስ ሳይሆን ከነባሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ በመውሰድ የታሪኩ አካል ሆኖ የተገለገለበትን አገላለጽ እናገኛለን። ይህም "ሴት አያውቁም ነበር (በግብር ስጋ) በንጉሡ ትዕዛዝ ካልኮነ (ካልሆነ) በቀር ጠጉራቸውን አይላጩም ነበረ። ኀስቋላ ያደፈ ልብስ አይለብሱም ነበር" (ገጽ 47) ይህን ቃል ተመልክተን ወዲያው ወደህሊናችን የሚመጣው የማኑሔ ልጅ የሶምሶን ታሪክ ነው። ሶምሶን በዚህ አይነት ክልከላ ውስጥ ናዝራዊ ሆኖ ያደገ እንዲሁም ለአምላክ የተመረጠ ብርቱ አገልጋይ ነበር። (መ.መሳ. 3÷4) ዘርዐ ያዕቆብም እንደ መለኮት ሁሉ ለራሱ የተመረጡትን ናዝራዊ ያደርጋል። ይሔንንም በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማንሳቱን አውጆ ሳይሆን ወደራሱ ውስጥ በራሱ መንገድ አካቶት ነው የምናገኘው። በመሆኑም በይነ-ቴክስታዊነቱ ቀጥታዊ ጠቃሽ ሳይሆን ባህሪውን በዘይቤ በመውረስ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በይነ-ቴክስታዊነት በዜና መዋዕሉ ውስጥ በሌላም መንገድ ተካትቶ እናገኛለን። በዚህ መናበብ ውስጥ የምናየው ማነጻጸርን ሲሆን በሌላ መንገድ ግን ባህሪን ማዋረስም ጭምር ነው ማለት እንችላለን። ዐፄ ዳዊት ጀምረውት የነበረውን ቤተመቅደስ ዘርዐ ያዕቆብ በእግዚአብሔር ፍቃድ እንደፈጸመው ያስረዳል ታሪኩ፤

ምኞቱን አልፈጸመለትም እንጂ የእግዚአብሔርን መቅደስ በዚያ ሊሠራ በልቡ አስቦ አባቱ ንጉሥ ዳዊት የሠራው ነበረ። ቀዳማዊ ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤት ሊሠራ ባሰበ ጊዜ እንዳልሆነለትና ያለ ልጁ ያለ ሰለሞን እንዳልተፈጸመለት ሁሉ ጊዜው አልደረሰም ነበርና። ለአባቱ ያልተቻለውን በዚያች ደብር ምዕራብ ወገን የእግዚአብሔርን መቅደስ ለመሥራት ንጉሡ ዘርዐ ያዕቆብ ሁላቸው ድኖችና

ባለጠጎችን ድንጎችን እንዲሸከሙ አዘዘ ሹማምንቱም ሁሉ በፍጥነት ሠሩ። እጅግ እስኪሰፋ ድረስ ቦታውን አበጃጁ በዚያ ላይ ሁለት አብያተ ክርስቲያን ሠራ። (ገጽ 61፣ አጽንዖት ከራሴ)

እንደምንመለከተው በአንደኛው አቅጣጫ ዘርዐ ያዕቆብ የአባቱን /ቀዳማዊ ዐፄ ዳዊት/ ምኞት እውን ያደረገበትን ሒደት ሰሎሞን የዳዊትን ምኞት ካሳካበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ ጋር (መ.ነገ. 6 ÷1- 2ኛ ዜ.መዋ. 3 ቁ.1) ያስተያየ ሲሆን በሌላም ሁኔታ የዘርዐ ያዕቆብ ደረጃውና መጠኑ እንደ ሶሎሞን መሆኑ ሲያመላክተን ይታያል።

### 3.3.2 "የዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" በይነ-ቴክስታዊነት ከገድላት ጋር

#### 3.3.2.1 የታሪክ ተፋሰስ/ story line

"የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብን ዜና መዋዕል" ተረክ የታሪክ ተፋሰስ (story line) ስንመለከት በመሰረታዊ ደረጃ በዐምደ ጽዮን ላይ ያስቀመጥናቸውን የአተራረክ መንገዶችን የተከተሉ ናቸው። እነዚህም መግቢያ፣ የተረኩ ዋና አካል (ታሪክ) እና አፈጻጸም ናቸው። እነዚህን ክፍሎች ለያይተን ለመመልከት እንድንችል ዜና መዋዕሉ እንዴት ይጀምራል? የሚለውን ነጥብ በማስቀደም እንመለከት።

##### 3.3.2.1.1 አጀማመር

በክብርና በንግሥ የተካከሉ በሶስቱ አካላት በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ ቆስጠንጢኖስ የተባለ የጌታችን የንጉሣችን የዘርዐ ያዕቆብን ሥርዐቶች ሁሉ እኔ አንብቤ እጽፍ ዘንድ እገርምራለሁ። በተዋህዶ የከበረ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ልቡ እንደሚወደውና እንደሚሻው ሁሉ ጽድቁንና መንግሥቱን እንዲወርስ ያድርገውና፤ በአፍራስ መንፈስ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ በኤልያስ ያደረ መንፈስ በደቀ መዝሙሩ በኤልሳዕ ዕፅፍ ድርብ ሁኖ እንዳደረበት፤ የበዛ ክብርና ባለሟልነትን ለማግኘት የኢየሱስ ጸጋ ረድዔት በሐዲስ ልጁ በልብነ ድንግል ላይ ዕፅፍ ድርብ ሁኖ ይደርበትና ዘመኑንም ሰማይ ከምድር እስኪያልፍ ድረስ በውነት ይብዛለትና። (ገጽ 48፣ አጽንዖት ከራሴ)

ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው በዜና መዋዕሉ መግቢያ ላይ የምናገኛቸው ከገድላት ጋርም የሚመሳሰለው (በይነ-ቴክስትታዊ) ነጥብ ስመ እምላክን አስቀድሞ በመጥራትና በርሱ በማመን እና በመለማመን መጀመር ነው። የመለኮት ስም አጠራር ላይ ሁሌ ከሚተኮርባቸው ነጥቦች መካከል እንደተራኪው ፍላጎት ዝርዝሩ የሚወሰነው ሚስጥረ

ሥላሴን መግለጽ ነው። በዚህም መሰረት እዚህ መግቢያ ላይም ሶስቱ አካላት በክብርና በንግሥና የተካከሉ መሆናቸውን በማወጅ ነው የሚጀምረው። አብ ወልድን እና መንፈስ ቅዱስን ማመኑን በመግለጽ ታሪኩን መጻፍ ይጀምራል።

በመቀጠልም የሚተረከው ተረክ የማን እንደሆነ አስረግጦ ይነግረናል። "የዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" መግቢያ ላይ ከተነሱ እና ትኩረት ከተደረገባቸው ነገሮች መካከል የንጉሡ ስም አንዱ ነው። ሁለት አይነት አጠራር እንዳለው ይጠቅሳል፤ ቆስጠንጢኖስ እና ዘርዐ ያዕቆብ። ከላይ በተመለከትነው የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ላይ አትኩሮ ከተደረገባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ይሔው የስም ጉዳይ ነበር።[13]

በመቀጠል የምናየው የመግቢያ ርዕስ ጉዳይ የታሪኩ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ስለዘርዐ ያዕቆብ ምን ሊተርክልን ነው የሚለውን መረጃ ፍንጭ የሚሰጥበት እና ከየት አምጥቶ እንደሚጽፍ የሚያስረዳበት ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ዜና መዋዕሉ የሚያተኩረው ንጉሡ ስለሠራቸው ሥርዐቶች በመናገር በመተረክ ላይ እንደሆነ ያስረዳል። ከዚህም በመሻገር እነዚህን ሥርዐቶች ሲተርክ የተጻፉትን በማንበብ መሆኑን መረጃ ያቀብለናል። በመሆኑም ተራኪው መረጃዎችን ተደግፎ እንጂ የሚተርክልን ከምናቡ በማፍለቅ ብቻ አይደለም ማለት ነው ብለን እንድናምን መንገድ ይጠርግልናል።

በዚህ ዜና መዋዕል መግቢያ ላይ ከምናስተውላቸው ጉዳዮች መካከል ለባለታሪኩ የሰማያት ጽድቅና መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርስ ተራኪው መመኘቱን ነው። ከዚህ ነጥብ መረዳት የሚቻለው ተራኪው የሚተርክለት ባለታሪክ በህይወት /በአጸደ ስጋ/ የሌለ መሆኑንን ነው። ይህም በተለምዶ በቤተ-ክርስትያን ውስጥ በቁም ላለ ሰው በዚህ አኳኋን እና መንገድ ምልጃ የማይቀርብ በመሆኑ ነው። ይህም ለጳጳስ ወይ ለንጉሥ ሲጸለይ በህይወት ካለ 'ጠብቀው' እንጂ 'መንግሥትህን አውርስ' ተብሎ አይጸለይምና። ይሔንኑ ነጥብ የሚያጠናክርልን ነጥብ በዚሁ የመግቢያ ክፍል ላይ እናገኛለን። ይኸውም ለባለታሪኩ ልጅ ለልብነ ድንግል የበዛ ክብርና ባለሟልነትን ለማግኘት "የኢየሱስ ፀጋ ረድኤት ዕፅፍ ድርብ ሆኖ" እንዲያድርበት ተራኪው ይመኛል። በመሆኑም ይሔኛው ሰው ከአባቱ ይልቅ በህይወት መኖሩን በግልጽ ከአገላለጹ መረዳት ይቻላል። ስለዚህም ተራኪያችን ተረኩን የተረከው በልብነ ድንግል ዘመን ዘርዐ ያዕቆብ ካረፈ በኋላ ነው ማለት ነው።

---

13 ዐምደ ጽዮንም በተረኩ ውስጥ ተደጋግሞ የሚነሳ ገ/መስቀል የሚባል ስም ነበረው፡፡ ይሔም ስሙ በተረኩ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ሲነሳ እናገኛለን፡፡ በዘርዐ ያዕቆብ መግቢያ ላይ ቆስጠንጢኖስ የሚለው ስም የተነሳ ቢሆንም በተረኩ ውስጥ ይህ ስም አንድም ቦታ ዳግመኛ ሲነሳ አናይም፡፡

በመሆኑም በዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል መግቢያ ላይ በመሰረታዊነት የምናገኛቸው ነጥቦች ስመ አምላክና ተማጽኖ፣ የታሪኩን የማንነት፣ የታሪኩን ምንነት፣ተረኩ የተተረከበትን ዘመን ሁኔታ የሚያሳይ ነው ማለት ይቻላል።

### 3.3.2.1.2 የተረኩ ዋና አካል (ታሪክ) በ "ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል"

በዚሁ ዜና መዋዕል ውስጥ ከምመለከታቸው አበይት ክፍሎች ውስጥ አንዱ የተረኩ ዋና አካል (ታሪክ) ነው። ተራኪያችን በአጠቃላይ ሁኔታ ስንመለከተው ፍሰቱን በጠበቀ ሁኔታ ማለትም በድርጊቶች ዘመን ቅደም ተከተል ሳይሆን የሚተርከው በርዕሰ ጉዳያት ከፋፍሎ ነው። ተረኩ በሚጀምርበት ክፍል ላይ የሚነሳው እጅግ ከከፍተኛ ጡዘት ላይ ነው። ተራኪውም ሲገልጸው "በንጉሣችን በዘርዓ ያእቆብ ዘመን ከፍ ያለ ድንጋጤና እንቅጥቅጥ በኢትዮጵያ ሰው ሁሉ ላይ ሆነ" (ገጽ 48) ብሎ ነው የሚጀምረው።

ይሔንን ታሪክ በጥልቀት ከተረከና ከቋጨ በኋላ ሌላ ርዕሰ ጉዳይ በማንሳት እርሱ ላይ በማትኮር ይተርካል። ስለቀጣቸውና ስላጋዛቸው ሰዎች፣ ስለመንግሥቱ አወቃቀር፣የሐድያና የአዳል ውጊያ፣ የቤተመንግሥት ግንባታና ሥርዐት፣የጥምቀት ሥርዐትና ሌሎች ሥርዐቶች፣ ሥርዐተ ንግሥና፣ የቤተ-ክርስቲያናት ግንባታ፣ የዳውሮ ጦርነት፣ የደቂቀ እስጢፋ ክርክር፣ የተላላፊ በሽታ፣ አስተምህሮ እና የሥርዐት መጽሐፍት የሚሉ ርዕሰ ጉዳያትን እያነሳ ይተርካል። አንዱ ከአንዱ ያለው የጊዜ ቅደም ተከትል ያን ያህል የተጠበቀ አይደለም። ከዚህ ሁሉ በኋላም ተረኩን ጨርሶ ዳግመኛ መከለስ ይጀምራል። በዚህ ክለሳው ላይም አስቀድሞ የተረካቸውን ትርክቶች በማደራጀት በእየ ርዕሰ ጉዳያቸው ለያይቶ መልሶ ይተርካል። በዚህ መሰረት ስለ ፃድቅና ስለሃይማኖት (ገጽ 68፣) የቅብአ መንግሥት ታሪክ (ገጽ 69)፣ ስለ ኢትዮጵያ ሹመቶች ሥርዐት (ገጽ 72)፣ ዌዛዝሩ (መኳንንቱ) ሌሎችም ሰዎች እንደተገደሉና እንደተቀጡ (ገጽ 73) የሚሉ አከፋፈሎችን በመጠቀም ዳግም ይተርካል።

በርግጥ በአብዛኛው ከፋፍሎ ባስቀመጣቸው ርዕሶች ስር ለርዕሱ ተመጣጣኝ የሆኑ ትረካዎችን የያዙ ቢሆንም በአንዳንዶቹ በተለይም "የቅብአ መንግሥት ታሪክ" በማለት በከፈለው ርዕስ ከርዕሱ መሰረተ ሀሳብ ያለፉ ጉዳዮችን አካቶ እናገኛቸዋለን። ለምሳሌም የአብያተ ክርስቲያናት ግንባታ እና የዐፄ ዳዊትን አጽም ማፍለስ፣ የዳውሮ ጦርነት፣ የደቂቀ እስጢፋ የሃይማኖት ሙግት እና ቅጣት እንዲሁም የበሽታ ዘመኑን ታሪክ ሁሉ በዚሁ ክፍል ውስጥ ተቀላቅለዋል።

በመሆኑም የዐዌ ዘርዐ ያዕቆብን አተራረክ ስንመለከተው በታሪኩ አከዋወን ቅደም ተከተል የተደረደረ ሳይሆን በየርዕስ ጉዳዩ የተቀመጠ እንዲሁም አስቀድሞ የተረከውን ተረክ በሌላ መልኩ አደራጅቶ የሚከልስ እንደሆነ ልብ እንላለን፡፡

### 3.3.2.1.3 አፈ.ጻጸም[14] በዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል

የዘርዐ ያዕቆብ ተረክ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሁለት ጊዜ ነው የሚተረከው፡፡ ስለዚህም በሁለቱም ጊዜ ታሪኩ ሲጠናቀቅ ተራኪው ታሪኩን ማጠናቀቁን ያውጃል፡፡ በመሆኑም በአጠቃላይ ዜና መዋዕሉ ውስጥ ሁለት ጊዜ መዝጊያ ወይም አፈጻጸምን እናገኛለን ማለት ነው፡፡ የመጀመሪያው ተረክ ሲጠናቀቅ በዚህ አይነት መልኩ ተረኩን ማጠናቀቁን ተራኪው ያሳውቃል፡፡

> እኒህን ሁሉ እየሠራ እየጸፈ በደብረ ብርሃን ፲፪ ዓመት ኖረ፡፡ ሁለቱን ዓመት ግን ወደ ፈረጎ ምድር እየሄደ ወደ ደብረ ብርሃንም እየተመላለሰ ወደ ደብረ ምጥማቅ ወደ ሌሎችም አውራጃዎች ሲሄድም ሲመለስም በዚህ ሁኔታ በደብረ ብርሃን ኖረ፡፡ ሙላው ዘመን ፲፬ ዓመት ነበረ፡፡ ከዚህ ወዲያ ዕረፍቱ ሆነ፡፡ ቸርነቱ ብዙ የሆነ እግዚአብሔር ጽድቅ ለዚህ ለንጉሣችን ለዘርዐ ያዕቆብ ሰማያዊ መንግሥትን ሁለተኛ ያድለው፤ ፀሃይና ጨረቃ እንዲያበሩላት የማትሻ አገር ኢየሩሳሌምን ያውርሰው፡፡ ከሁላቸው ከነብያትና ሐዋርያት ደቀ መዛሙርቱ ጋር በደስታ ወደርሷ እንዲገባ ከሙላቸው ጻድቃንና ከሰማዕታት ጋር ልጁን ልብነ ድንግልንም ይጠብቀው፡፡ በመንግሥቱም ያኑረው በመለኮቱ ኃይል ስለ ሕያዋንና ስለሙታን ለመፍረድ አመጣጡ ከሰማይ እስኪሆን እስኪደረግ ድረስ፡፡ ሙላቸው ጠላቶቹንም ከምድር ገጽ ያጥፋለት ድንግል ንጽሕት ስለሆነች ስለ እናቱ እመቤታችን ማርያም ብሎ ዘወትር እየለቱ እየሰዐቱ የታደለ ደስታ ቃልን ይነጋገረው በውነት፡፡ ሕዝብ ሁሉ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይሁን ይደረግ ይበል፡፡ (ገጽ 67-68፤ አጽንዖት ከራሴ)

ይህ የመጀመሪያው ትርክት ሲጠናቀቅ ባለታሪኩ በደብረ ብርሃን የቆየበትን ዘመን አንስቷል፡፡ ይህም የአፈጻጸሙ መጠቅለያ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ዜና መዋዕል የዘርዐ ያዕቆብን የአወላለድ እና አነጋገስ ታሪክ በተመለከተ ምንም ዝርዝር ነገሮችን ባይዝም ሞቱን ግን በማወጅ ያጠናቅቃል፡፡ በማስከተልም ትኩረት የሚያደርገው ስለባለታሪኩ መማለድ ላይ ሲሆን ሰማያዊ ኢየሩሳሌምን ይመኝለታል፣ ይለምንለታል፡፡ በመጨረሻም ለሟች እንደጸለየ ሁሉ ለቋሚው ለልብነ ድንግል በመለኮት ጥበቃ እንዲደረግለት ጸልዮ ያጠናቅቃል፡፡

---

[14] እዘህም ላይ "አፈ.ጻጸም" ስል ከላይ በተነተንኩት "የዐዌ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ትንታኔ" ላይ ያለው ትርጓሜ እንደተጠበቀ ይሁንልኝ፡፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ታሪኩን ጀምሮ ሲጨርስ ደግሞ ከላይ ካየነው በተለየ ሆኖም መሰረታዊ ይዘቱን ባላጓደለ መልኩ ትረካውን ይዘጋል።

ይህን ሁሉ አስተምሮ ሐዲሳት መጻሕፍትን አስጽፎ ንጉሣችን ዘርዐ ያዕቆብ በነገሠ በ፴፫ ዓመት በደብረ ብርሃን በሰላም ዐረፈ (ሞተ)

የተመረጡ ጻድቃን ወገን የምዕመናን መሠረት የሆነ የንጉሣችን የዘርዐ ያዕቆብን ታሪክ እጽፋለሁ። እግዚአብሔር በሰማያዊት ቦታ ውስጥ ያኑረው ልቡ በሚወደውና በሚሻው ለልጁ ለልብነ ድንግልም ዘመኑን ያርዝምለት የሰማይና የምድር ማለፍ ጊዜ እስኪሆን ድረስ ዕድሜውን አያጉድልበት በውነት

ለዚህ ለንጉሣችን ለዘርዐ ያዕቆብ መመስገኛው የሆነች ኢየሩሳሌምን ያድለው በውነት ፍፁም ምስጋና የሚገባው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐተታንና ወቀሳን ሳያደርግ ያውርሰው ወንጀለኞችን ሁሉ ለማጥፋት ለልጁ ለልብነ ድንግልም ኃይልን ይስጠው መንግሥቱንም ይባርክ። ሥጋውንና ነፍሱን ለዘለአለሙ ከኃጢአት ሁሉ ይጠብቅ በውነት። (ገጽ 75 አጽንዖት ከራሴ)

ከላይ እንደምንመለከተው አስቀድሞ በመዝጊያው ላይ ባለታሪኩ የሠራውን ዘክሮለት፣ "ይህን ሁሉ አስተምሮ መጻሕፍትን አስጽፎ" በማለት ጠቅሶ ነው ለማጠናቀቅ የሚንደረደረው። በማስከተልም ምን ያሕል ዘመን በዙፋን እንደኖረ በመንገር ያረፈበትን ቦታ ጠቅሶ ተረኩን ወደመቋጨት ይንደረደራል። ከዛም አስቀድሞ ለባለታሪኩ የነፍሱን ማረፊያ ተማጽኖ ለልጁም ረዥም ዘመንን በመመኘት ያጠናቅቃል። በመሆኑም "የዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" አፈጻጸም ከላይ እንዳየነው የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል የራሱ መዝጊያ ያለው ሲሆን የተረኩን አላማ ፍሬ ሐሳብ፣ ለንጉሡ ምልጃና ለወራሹ ጸሎት በማድረግ ይጠናቀቃል ማለት ነው።

### 3.2.2.5 የታሪክ ተፋሰስ (story line) በይነ-ቴክስታዊነት

ከላይ ማየት እንደቻልነው በዜና መዋዕሉ የታሪክ ተፋሰስ (የተረክ አደራደር) በበርካታ ገድላት ላይ ያለውን አደራደር የተከተለ ነው። በመግቢያው እና በአፈጻጸሙ ላይ ያየናቸው ሀሳቦች እንደተጠበቁ ሆኖ በተረኮቹ ርእስ ጉዳይ የባለታሪኩን ተረክ አደራጅቶ ማቅረብ እንዲሁ በገድላት ውስጥም የሚታይ አታተራረክ ነው።

በሌላም አከዋኋን በዜና መዋዕሉውስጥ ያሉ የሃይማኖት እና የሃይማኖታዊ ሥርዐቶች በገድላት ውስጥ ካሉት የተጋዳሊነት ሚና አለመራቃቸው ብቻ ሳይሆን ፍጹም

መንፈሳዊ ሆነው መቅረባቸው በሁለቱ መካከል ያለውን በይነ ቴክስታዊነት ያጠናክረዋል። ከቅርጽ አንጻር ግን ከላይ "በዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ላይ ማየት እንደቻልነው ከገድላት የታሪክ ተፋሰስ ጋር በይነ-ቴክታዊነቱ እጅግ የጎላ ነው ማለት ይቻላል።

### 3.3.2.2 ተአምራዊነት

"በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል" ውስጥ በጉልህ ከሚታዩ ነጥቦች መካከል ተአምራዊነት አንዱ ተጠቃሽ ነጥብ ነው። በአጠቃላይ ዜና መዋዕሉ ከምናገኛቸው ተአምራዊ ክስተቶች መኃል የደቂቀ እስጢፋ የሃይማኖት ክርክርን ተከትሎ ንጉሥ ለወሰደው ቅጣት እንደበጎነት ማረጋገጫ ወይም የመለኮት ስምምነት እንዳለው ለማስረዳት የመጣው ብርሃን አንዱ ነው። በተረኩ ላይ እንደምናየው ደቂቀ እስጢፋዎች "ለማርያም እንዲሁም ክርስቶስ ለተሰቀለበት መስቀል አንሰግድም" ብለው ያስተምራሉ። ይሔም ዜና ንጉሥ ዘንድ ይደርስና ምሁራንን ሰብስቦ ጉባኤ መስርቶ ክርክር ያደርጋል። እንደተራኪያችንም አባባል ንጉሥ ይረታል (ያሸንፋል)። እናም ሁለተኛ እንዲህ ብለው እንዳያስተምሩ ያዛቸዋል።

ሆኖም ደቂቀ እስጢፋዎች ይሔንን ግብራቸውን ሳያቆሙ ይቀራሉ። አሁን ግን ንጉሥ ጉባኤ ሳይሆን የሰበሰበው ችሎት ነው። እናም እማኞችንና ፈራጆችን ጋብዞ ይፈርድባቸዋል። በዛም መሰረት የተገደሉ ብዙ ናቸው። ምላስ አፍንጫቸውን የተቆረጡም ብዙ ነበሩ። እንግዲህ ከዚህ ፍርድ በኋላ ነው ተአምሩ የሚመጣው። ያኔም በደብረ ብርሀን ከተማ ላይ ለብዙ ቀን የቆየ ብርሀን ወረደባት ይለናል ተራኪው። በቅዳሴም ጊዜ ይኸው ብርሀን የወረደ መሆኑንም ያስረዳል። የዚህ ሁሉ ተአምር ምክንያት የንጉሡን ፍርድ እና የክሱ መሰረት የሆነውን የንጉሡን አቋም መንፈሳዊ ወይም መለኮታዊ ይሁንታን ምስክርነት እንዳለው ማስረገጥ ነው።

ከዚህ በተለየ መልኩ ከምንመለከታቸው የዜና መዋዕሉ ተአምራዊ ተረኮች መካከል በደብረ ብርሃን ከተማ ላይ የተከሰተው የተስቦ በሽታ የተወገደበት ተአምር ነው። በዚህ ተረክ ላይ ንጉሡ በደብረ ብርሃን በመኖሩ የተነሳ ህዝብ ቁጥሩ በመጨመሩ ተስቦ እንደመጣ ይነግረናል። ከዚህም የተነሳ ሰው ቀባሪ እስኪያጣ ድረስ ሞት ችግር ሆኖ ነበር። በመሆኑም ንጉሥ አንድ የፈውስ ርምጃ ወሰደ።

ይህ እርምጃ እግዚአብሔር ለቅዱስ ቁርቀስ "ቤተ መቅደስህን ወደሠራው የችነፈር በሽታ አይምጣ። የውሀ ችግር የእህል ጥፋት በቤቱ ውስጥ አይሁን።" ሲል የገባለትን ቃል ኪዳን ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ አስቦ የቁርቀስ ቤተ-ክርስቲያንን ያንጻል። በዚህም መሰረት ወዲያውኑ በሽታው ከሐገር ይጠፋል። ድኅነትም በደብረብርሀን ይሆናል። ንጉሥም በቁርቀስ ስም ካልሆነ በሌላ በማንም ህዝቡ እንዳይምል ትዕዛዝ ያወጣል።

አብዛኛዎቹ አጥኚዎች እንደሚስማሙት በገድላት ውስጥ ከሚታዩ ዋንኛ ነጥቦች መካከል ተአምራት ወይም ልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት ተጠቃሹ ነው (ቴዎድሮስ 2001፡ 109)። እንግዲህ በዚህ መልክ ነው ዜና መዋዕሉ ተአምራዊነትንም በመያዝ ከሱ አንጻር የምንመለከታቸውን ገድላትን በበይነ-ቴክስታዊነት የሚያገናኛቸው።

### 3.3.2.3 ፀሎት/ ምልጃ

በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ላይ በስፋት ከምናገኛቸው ጉዳያት መካከል ጸሎት እና ምልጃ አንዱ ነው። በዜና መዋዕሉ ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ ጸሎትን የምናገኘው ንጉሥ እንደምን ባለ ሁኔታ እና መንገድ ጸሎት እንደሚያደርግ የሚዘግበው ክፍል ነው። ይህም ቅዳሴን ከነማን ጋር እንደሚሳተፍ እንደምን ባለ ሁኔታ ወደቤተ-ክርስቲያን እንደሚገባ የሚያሳየው ተረክ ነው (ገጽ ገጽ 53-54)። ከዚህ በተጨማሪ በቀጥታ በጦርነት ውስጥ በሚገባ ወቅት በተለይም በሐድያው ጦርነት ወቅት ካህናቱ እንዲጸልዩለት ሲጠይቅና ያየውን ራዕይ ምንነት በአንድ ላይ እንመለከታለን።

> ከዚህ በኋላ መጥቅ መትተው ብዙዎች መነኮሳትና ካህናት ተሰበሰቡ በየቤተ ክርስቲያናቸው ምህላ እንዲያደርጉ አዘዝዋቸው ብዙ ዕጣን በመስጠት ለነዳያን ለምስኪናን ልብስ በመስጠት፤ ከጸሎቱ ፍጻሜ በኋላ በዚያች ቀን ራእይ አየሁ ብሎ ንጉሣችን ዘርዐ ያዕቆብ ለቅዱሳን ነገራቸው (ራዕዩም ይህ ነው) ያን ዐመጠኛ በጥኑ ገመድ አስረው ወደኔ አመጡት በፊቱም ጣሉት እመቤታችን ድንግል ማርያም እንዲህ አድርጋ በሕልሜ በዚች ሌሊት አሳየችኝ ተገለጠችልኝ። ይህ ሕልሜ እንዲፈጸምልኝ ወደ ፈጣሪዬ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ ለምኑልኝ። (ገጽ 51)

ይህ የጸሎት አዋጅ የንጉሥን ራዕይ እውን ማድረግ እና ጦርነቱን በድል ለማጠናቀቅ በንጉሡ አዋጅ የሚጸለይ ጸሎት እንደሆነ ልብ እንላለን። ውጤቱም የታየውን ህልም/ራዕይ እውን የሚያደርግ ሆኖ እናገኘዋለን። እንደ ራዕይውም ጦርነቱን ንጉሡ ያሸንፋል።

ይህ ዜና መዋዕል ካለው የመንፈሳዊነት ዝንባሌ አኳያ ጸሎትን በግብሩ ብቻ ሳይሆን ጸሎትን በአስተምህሮት ደረጃ ትኩረት ሰጥቶት ጭምር ነው የምናገኘው። ማለትም እንደምን ባለ ሁኔታ እና እንዴትና ምን ተብሎ መጸለይ እንዳለበት የሚያስተምር መመሪያን ሁሉ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን (ገጽ 75)። በመሆኑም በዜና መዋዕሉ ውስጥ ጸሎት አንዱ አብይ ጉዳይ በመሆኑ በትኩረት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው።

## ምዕራፍ አራት

### ማጠቃለያ

ከላይ በትንተና ክፍል ላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በሁለቱ ዜና መዋዕሎች ውስጥ ያሉ የመተረኪያ ቴክኒኮችን ለማየት ሞክረናል። በዚህ ጥናት ውስጥ የአተራረክን ቴክኒክ ለመመልከቻ የመረጥናቸው የስነ ተረክ ማጥኚያዎች አተኩሮ እና በይነ-ቴክስታዊነት ነበሩ። በዚህ መሰረት በመሰረታዊ ደረጃ አንዳንድ ነጥቦችን አይተናል።

ሁለቱ ዜና መዋዕላት በየራሳቸው የተራኪያቸው ሁኔታ ይለያያል። የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ተራኪ በአጠቃላይ ታሪኩ ውስጥ ተሳታፊና የታሪኩ አካል የነበረ መሆኑን በጉልህ ከዜና መዋዕሉ አተራረክ መረዳት ይቻላል። የዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ተራኪ በአንጻሩ በታሪኩ ዘመን ውስጥ እንደኖረ በጥቂት መረጃዎች ማወቅ የሚቻል ቢሆንም ለታሪኩ ግን ቅርብ ያልነበረ ይልቁንም መረጃዎችን ተንተርሶ መጻሕፍትን አገላብጦ ንጉሡ ከሞተ በኋላ የተረከው እንደሆነ ከአተራረኩ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ከዚህ ሁኔታ በመነጨ ወይም በሌላ ምክንያት የአተራረክ ቴክኒካቸው መለያየት የሚስተዋልባቸው ሲሆን ከመሰረታዊ የመተረኪያ መንገድ እና ዘልማድ የተነሳ ደግሞ አንድነት ይታይባቸዋል። በሌላ አባባል ዜና መዋዕላቱ ንጉሡ በህይወት እያለ አሊያም ካለፈ በኋላ በሚጻፍበት ጊዜ የአንጻር መለያየት፣ የታሪክ ጊዜ ቅደም ተከተል አሊያም በይነ-ቴክስታዊነት የሚፈጥሩበት ሁኔታ ሊለያይ ይችላል። በመተረኪያ ዘልማድ አኳያ ደግሞ የታሪክ ተፋሰሱ (ይፋዊ የሆነ መግቢያ፣ የተረክ ክፍል፣ እና መደምደሚያ መኖር)፣ በይነ-ቴክስታዊነትን መፍጠርንና ቋንቋን በመሰሉ ጉዳያት ላይ አንድነት ይስተዋልባቸዋል።

በዚህም መሰረት በሁለቱም ዜና መዋዕላት ላይ አተኩሮን በተመለከተ ዋና ማዕከላዊ ጉዳያቸው እና ባለ ታሪካቸው ነገሥታቱ ናቸው። ያም ቢሆን ከላይ በጠቀስኩት ለታሪክ እና ባለታሪክ ቅርብ የመሆን ያለመሆን ምክንያት የመተረኪያ አንጻራቸው ይለያያል። በሁለቱም ዜና መዋዕላት ላይ ያሉ ተራኪዎች ርዕዮተ ዓለም መነሻው የክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ መሆኑን ማረጋገጥ የቻልን ሲሆን ለንጉሥ ያላቸው ዕይታም ከመለኮት የተቀባ የአምላክ እንደራሴ ነው የሚል ነው።

የዜና መዋዕሉ ተራኪዎች በየአንጻራቸው የሚነሱበት መሰረታዊ አላማ ያላቸው ሲሆን "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል" ተራኪ ሁለት አላማ በዋነኝነት እንዳለው አረጋግጠናል። ከላይ በትንተና ክፍሉ ውስጥ ለመመልከት እንደሞከርነው እነዚህ አላማዎች ምድራዊ ልዕልና ማግዘፍ እና ሰማያዊ ብጽዕናን ማጎናጸፍ ናቸው። ሁለቱም

አላማዎች በየራሳቸው የሚቆሙ ቢሆኑም አንዱ አንዱን የሚደገፍም ነው፡፡ በመቀጠል የተመለከትነው የዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ተራኪ እንደዐምደ ጽዮን ሁሉ ሁለት መሰረታዊ አላማዎች አሉት፡፡ አንደኛው የንጉሡን ሥርዐት ጠባቂነትና ሥርዐት ሠሪነት ማሳየት ሲሆን በዚህ አላማው ውስጥም የምድራዊውን የንግሥና፣ ሀገር የማስተዳደር እና የመምራት ሥርዐትንና የመንፈሳዊ ሥርዐትን ጠባቂነቱንና ሠሪነቱን የመንገር አላማውን አካቶ ይዟል፡፡ በሁለተኛነት የዜና መዋዕሉ ተራኪ አላማ ዘርዐ ያዕቆብ ለሃይማኖት ያለውን ፍቅርና ቅናት ማሳየት ነው፡፡ ሁለቱንም ዜና መዋዕላት ተንተርሰን ስንመለከት የነገሥታቱን ምድራዊ ተግባር ከሌሎች አልቆ መስበክና በአምላክ ሥራ እና አሠራር ውስጥ ያላቸውን ሚና ማሳየት በጋራ የሚጋሩት አላማ ነው ማለት እንችላለን፡፡

በሁለተኛነት ደረጃ ሁለቱንም ዜና መዋዕላት ለመመርመር የተጠቀምነውን በይነ-ቴክስታዊነትን ስንመለከት ዜና መዋዕላቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከገድላት ጋር በተለያየ መንገድ በይነ-ቴክስታዊነትን ይፈጥራሉ፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተራኪው ያነሳቸውን ጭብጦች ለማጽኛትና ለማረጋገጥ የሚከውነው ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ለማነጻጸሪያነት እና ምስል ለመከሰት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በይነ-ቴክስታዊነትን ይፈጥራል፡፡ እዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ በይነ-ቴክስታዊነት ላይ አንድ ነጥብን በንጽጽር በማንሳት እንመልከት፡- የዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ተራኪ ከዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ተራኪ በተለየ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በርካታ ጊዜ ሲናበብ እንመለከታለን፡፡ ምናልባትም ተራኪው በትክክለኛው ሰአትና ጊዜ ውስጥ በመኖሩ በእያንዳንዱ የተረክ ቅንጣት ላይ ስሜት በተሞላበት ሁኔታ የሚተርክ ስለሆነ መመሰል፣ ማነጻጸር እና ማዋረስን እንደ ስሜቱ መግለጫ በመጠቀሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በይነ-ቴክስታዊነትን እንዲፈጥር ገፍቶታል ብለን መገመት እንችላለን፡፡

በአንጻሩ ከገድላቱ ጋር ዜና መዋዕላቱ የሚያደርጉት በይነ-ቴክስታዊነት ከላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንደሚፈጥሩት አይነት ሳይሆን በአተራረክ ቴክኒክ እንዲሁም በተረክ ይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በገድላት ላይ እንደሚስተዋለው ያለ የታሪክ ተፋሰስ (መግቢያ፣ የተረክ ክፍል፣ እና መደምደሚያ ወይም አፈጻጸም) እንዲሁም በነዚህ ቅርጻዊ ክፍሎች ውስጥ ያለው ይዘት እንዲሁ በዜና መዋዕላቱ ውስጥም የሚታይ ነጥብ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ በገድላት እና ዜና መዋዕላቱ መሐል ያለውን በይነ-ቴክስታዊነት መረዳት ችለናል፡፡

በሌላ መልኩ በገድላት ይዘት ውስጥ በመባያነት የሚነሳው ተአምራት እንዲሁ በዜና መዋዕላት ውስጥም የሚታይ መሆኑ ዜና መዋዕላቱ ከገድላቱ ጋር ያላቸውን በይነ-

ቴክስታዊነት ያሳያል፡፡ በሁለቱም ዜና መዋዕላት ውስጥ ተአምራት ተደጋግሞ የሚመጣ መሆኑ ለገድላቱ ብቻ ሳይሆን ለዜና መዋዕላቱም መባያ ነው ማለት እንችላለን፡፡ በመጨረሻም ዜና መዋዕላቱ ከገድላቱ የሚገናኙበት ነጥብ ጸሎት ነው፡፡ በዜና መዋዕላቱ ውስጥ ጸሎት በእኩል መጠን ተደጋግሞ የሚታይ ሲሆን በጋራ በዜና መዋዕላቱ ውስጥ የሚገኝ ይዘት በመሆኑ አንዱ መባያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በገድላት ውስጥም ይኸው ነጥብ የማይዘለል መባያ በመሆኑ በዜና መዋዕላቱ እና በገድላቱ መካከል እንዳለ በይነ-ቴክስታዊነት ልንመለከተው እንችላለን፡፡

ስለዚህም የዜና መዋዕላቱ አጠቃላይ ተረካዊ ባህሪይ የሚወሰነው በተራኪው ማንነት እና አውድ ላይ የሚያተኩር ሲሆን ተረኩን ለመመርመሪያነት የተጠቀምናቸው ሁለቱ መመርመሪያ አቅጣጫዎች አተኩሮ እና ተናበባዊትን ስንመለከት እንረዳለን፡፡ አትኩሮቱ ይዘቱን እና የመተረኪያ መንገዱን ይወስናል፡፡ ተናበባዊነቱ ደግሞ የተራኪውን ቀደም እውቀት እና ተጋልጦ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ዜና መዋዕላቱ ገድላዊ ነው አይደለም ለሚለው ነጥብ እንደማስረጃ ከማገልገሉ በተጨማሪ በምን መንገድ እና ሁኔታ ነው የሚመሳሰሉት የሚለውን ነጥብ ለይቶ ማስረዳት ይቻላል፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት


ስርግው ገላው፤ "የንጉሥ ተክለሃይማኖት ታሪክ በመጻሐፈ ስንክሳር" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ መጽሔት፤ ቁ.11፣ ገጽ 1-28፣ 1993፡፡

ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን፤ የዐፄ ሰርጸ ድንግል ዜና መዋዕል፤ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1999፡፡

ባርትኒስኪ አንድርዜይ እና ዮዓና ማንቴል-ኒየችኮ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ትርጉ. አበበ አለማየሁ 2003፡፡

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፤ ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤ አዲስ አበባ፣ 2002፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፤ በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፤ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 2001፡፡

አምሳሉ አክሊሉ፣ "አጭር የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ታሪክ" (ያልታተመ) አ.አ.ዩኒቨርስቲ፣1976፡፡

ከበደ ሚካኤል፤ ታሪክ ምሳሌ 1ኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፋያ፣ 1999፡፡

ዕምባቆም ቃለ ወልድ አረአ፤ "የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብና የዐፄ በእደ ማርያም ታሪክ መጽሐፍ በአማርኛ" (ያልታተመ)፡፡

ዘሪሁን አስፋው፤ የስነጽሁፍ መሰረታውያን፤ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1992፡፡

__________ "የዜና መዋዕል አጻጻፍ ስልት ናሙናዊ ምልከታ" የኮተቤ መምህራን ኮሌጅ የመጀመሪያው የቋንቋዎች አውደ ጥናት፤ አዲስ አበባ፣ ሰኔ 11-12 1984፡፡

የኢትዮጵያ መጸሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ መጸሐፍ ቅዱስ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1962፡፡

የኩኖ አምላክ፤ "የዐፄ ዐምደ ጽዮን ዜና መዋዕል በአማርኛ" (ያልታተመ)፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993፡፡

ደስታ ተክለወልድ፤ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡.

ዳኛቸው ወርቁ፤ የጽሑፍ ጥበብ መማሪያ፤ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1977፡፡

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፤ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎች፤ አዲስ አበባ፣ አ.አ.ዩ. ፕሬስ፣ 2002.

Abrams, M.H. A Glossary of Literary Terms. 7th ed. USA: Earl McPeek, 1999.

Allen, Graham. Intertextuality. New York: Routledge, 2000.

Bahru Zewde. "Evolution of professional Historiography in Ethiopia", What is "zemenawinet"?- perspective on Ethiopian Modernity. 30 - 37 Addis Ababa, Fredrich Ebert-Stiftung, 2012.

Baldick, Chris. The Concise Oxford Dictionary of Literary Terms. New York: Oxford University Press, 2001.

Bauman, Richard. A world of others' words: cross-cultural perspectives on intertextuality Australia, Blackwell Publishing, 2004.

Bautnan, Richard and Charles Briggs. "Genre, Intertextuality, and Social Power." Journal of Linguistic Anthropology 2.2 (1992): 131-172.

Becker- Leckrone, Megan. Julia Kristeva and Literary Theory. New York: Palgrave Macmillan, 2005.

Belete Mered. Historical and Philological Analysis of the Chronicles of Iyasu I (1682 - 1706) MA april, 2008

Bennett, Andrew and Nicholas Royle. An Introduction to Literature, Criticism and Theory. Great Britain: Pearson Education Limited', 2004

Briggs, Charles, and Richard Bauman. 1992. "Genre, Intertextuality, and Social Power". Journal of Linguistic Anthropology 2: 131-172.

Caplan, Jay. Framed Narratives. Minneapolis: University of Minnesota Press, 1985.

Childs, Peter and Roger Fowler, The Routledge Dictionary of Literary Terms. New York: Routledge & Kegan Paul Ltd, 2006.

Coste, Didier. Narrative as Communication. Vol. 64. Minneapolis: University of Minnesota Press, 1989.

Culler, Jonathan. Literary theory: a very short introduction. New York: Oxford University Press Inc, 1997.

Eperem, Eshete. "The Narrative Techienic of Three Ethiopian Hagiography". n.d.

Gross, Sabine. "Surveying Narratology." Monatshefte 100.4 (2008): 534-559.

Habib, Rafey. A History of Literary Criticism: from Plato to the present. United Kingdom, Blackwell Publishing Ltd, 2005.

Heinen, Sandra and Roy Sommer. Narratology in the age of cross-disciplinary narrative research. New York: Walter de Gruyter, 2009.

Herman, David. The Cambridge companion to narrative. New York: cambridge university press, 2007.

Herman, Luc and Bart Vervaeck. Handbook of narrative analysis. London: University of Nebraska Press, 2005.

Horstkotte, Silke. 2005. "The Double Dynamics of Focalization in W. G. Sebald's *The Rings of Saturn*". In: Jan Christoph Meister (ed.). *Narratology Beyond Literary Criticism. Mediality, Disciplinarity.* Berlin/New York: de Gruyter, p. 25-44.

Hühn, Peter, Wolf Schmid, Jörg Schönert /ed/. Point of view, perspective, and focalization : modeling mediation in narrative. Berlin, Walter de Gruyter, 2009.

Huntingford, G.W.B. The Glorious Victories of Amda Seyon King of Ethiopia. Great Britain: Oxford at the Clarendon Press, 1965.

Joachimsen, Kristin. Identities in Transition. Boston, Martinus Nijhoff Publishers and VSP, 2011.

Kaplan, Steven. "Hagiographies and the History of Medieval Ethiopia." History in Africa (1981): 107-123.

Kindt, Tom and Hans-Harald Müller. What Is Narratology? Berlin: Walter de Gruyter, 2003.

Kristeva, Julia. Revolution in poetic language.. New York,Columbia University Press, 1984.

Mengestu Kebede. A Historical and Philological Analysis of the Chronicles of Emperor Sarsa Dingil (1563 - 1597) MA November 2007

Moi, Toril (ed) The Kristeva reader. New York, Columbia University Press, 1986

Molvaer, Reidulf K. "The Tragedy of Emperor Libne-Dingil of Ethiopia (1508-1540)." Northeast African Studies V.5.No.2 (1998): 23-46.

Monika, Fludernik. "History of Narratology: A Rejoinder." Poetics Today 24.3 (2003): 405-411 .

–. "The Diachronization of Narratology." Narrative 11.3 (2003): 331-348 .

Pankhurst, Richard k. The Ethiopian Royal Chronicls. Addis Ababa: oxford University press, 1967.

Prince, Gerald. "Classical and/or Postclassical Narratology." l'esprit createur 48.2 (2008): 115-123.

Punday, Daniel. Narrative Bodies: Toward a Corporeal Narratology. New York: PALGRAVE MACMILLAN™, 2003.

Quinn, Edward. A Dictionary of Literary and Thematic Terms, 2nd. USA: An imprint of Infobase Publishing, 2006.

Tadios Sisay. "A Study of Narrative Techniques in the Chronicle of Yohannes I (?aəlaf Sägäd)" MA October, 2009

Trask, R.L. Key Concepts in Language and Linguistics. New York, *Routledge is an imprint of the Taylor & Francis Group,1999.*